# ካይሮስ ኦራል ባይብል

www.oralbibles.org

# ካይሮስ ኦራል
# ባይብል

## መግቢያ

ከዚህ ቀጥሎ የሚ ኘዉ የካይሮስ ኦራል ባይብል ጽሐፍ ነ ው፡ ፡ ይህ ጽሐፍ የተወሰደዉ ከአደሱ መደበኛ ትርጉምና በ 1980 ቀለል ባለ አማርኛ ከታተመዉ መጽሐፍ ቅዱስ ነ ው፡ ፡
የካይሮስ ኦራል ባይብል ጽሐፍ በቃል ለሚማሩ ተማሪዎች ወይም ሰዎች አጠቃላይ ሀሳብ የማስጠት ዓላማን አንግቦ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ካሉት 70 ታሪኮችን ይይዛል፡ ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ የሚ ኙ ሁሉም ታሪኮች በዚህ ጽሐፍ ወስጥ አልተካቱም፤ ነ ገ ር ግን ማእከላዊ መጽሐፍ ቅዱስ ትረካን የያዙ ታሪኮችና የመጽሐፍ ቅዱስን የድነ ትንና የዕርቅን ዋና ሜልዕክት የሚወክሉ ታሪኮች ተካተዉበታል፡ ፡ በዮሓንስ 8፡ 31 ኢየሱስ ሲናገ ር "እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእወነ ት ደቀ ማዛመሮቴ ናችሁ::" ይላል፡ ፡ ስለዚህ የዚህ ኦራል ባይብል ጽሐፍ ዋና ዓላማማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ሰዎች የእግዚአብርን ቃል በቃላቸዉ አጥንተዉ የጌታችን የኢሱስ ክርስቶስ ደቀመዛመሮ እንደሆኑ ለማገ ዝ የተዘጋጀ ነ ው፡ ፡
በዓላማእነ ዚህ 70 ታሪኮች እንደ ጅማሬ ተደርጎ ነ ዉ የተዘጋጁት፡ ፡ ሌሎች ሰዎች እነ ኚን ታሪኮች መሠረት በማድረግ ይህንን ጽሐፍ ሰፋ ልያደርጉ ይሻሉ፡ ፡ ይህ ሀሳብ ተቀባይነ ት አለው፡ ፡ በዚህ በኦራል ባይብል ወስጥ የሚ ኙ ታሪኮች መጽሐፍ ቅዱስን በቃል ለሚማር ሰዉእየ ደጋገ መለመናገ ር እንድያመቸዉ አጠር ተደርጎ ተዘ ጋጀ፡ ፡ ለምሳሌ በሶስት ምእራፍ የተጻፈ የኖህ ታሪክ ከግማሽ ገ ጽ በታች አጥሮ እናገ ኛለን፡ ፡ ይህ ደግሞ የኖህን ታሪክ በበለጠ ማነ ገ ድ ለመናገ ር እንድንማር ያስችለናል፡ ፡ ነ ገ ር ግን ሁሉንም ጽሐፍ ከወሰደን ታሪኩን ረዥም በማድረግ አሳቡን እንደንይዝ ያደርገ ናል፡ ፡ ታሪኮቹ ብያጥሩም ምንም የተቀየ ረ ወይም የተጨመረበት ሀሳብ የለም፡ ፡ እንዲሁም ከይዘቱ የተቀነ ሰ ሀሳብ የለም፡ ፡ ታሪኮቹ እንዳሉ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው፡ ፡ ከታሪኮቹ ጥቂቶቹ በአራቱ ወንጌላት ወስጥ የሚ ኙ የታሪክ ስብስቦች ናቸው፡ ፡ የኢየሱስ ማጠምቅ፤ ሉቃስ ብቻ የጠቀሰዉ በመጥመቁ ዮሐንስና ልጠምቁ በማጡሰዎች መካከል የተደረገ ንግግር፤ ማቴዎስ ብቻ ለይተዉ ያስቀመጠዉ የኢየሱስ ከገ ሊላ መጥጦ በዮርዳኖስ ወንዝ ማጠምቅ፤ ሆኖም ዮሐንስ ብቻ የጠቀሰዉ ዮሐንስ 1፡ 29 "እነ ሆ የእግዚአብሔር በግ የአለምን ኃጥአት የሚያስወግድ" የሚሳሰሉ ታሪኮችን ያካትታል፡ ፡ ስለዚህ ካይሮስ ኦራል ባይብልን ለማዘጋጀት እነ ኝ አራቱን ስብስቦች ግምት ወስጥ በማስገ ባት አድማጮች ሙሉ የሆነ ሜልዕክት እንድያገ ኙ ተደርጓል፡ ፡ ይህ ጽሐፍ በአንደበት ደጋግሞ መናገ ር ተደርጎ ስለተዘጋጀ፤ አንዳድ ጊዜ ተለዋጭ ስሞች ተተከአቸዉ ወደ ሆኑ ወደ ዋናዉ ስሞች ተለወጦ እናገ ኛቿለን፡ ፡ ይህ ደግሞ ለአድማጮች ግልጽ እንድሆን ስለተፈለገ ነ ው፡ ፡ በቀደመዉና በተሰጠዉ ታሪክ መካከል ማሻጋገ ሪያ ድልድይ ሆኖ እንዲያገ ለግሉ ወይም ቅድመ ሁኔ ታን በተማለከተ ፍንጭ እንዲሰጡ በታሪኮቹ መጀመሪያ ላይ መግቢያዎች ተሰቷል፡ ፡

የ 70 ታሪኮች ስብስብ ታሪክ አጠር ባለ ሜልክ ብዘጋጅም የቅዱሳት መጽሐፍን አጠቃላይ እይታ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ተማሪዎች ለማስጠት በቂ ነ ው፡ ፡ ከዚህም በላይ የካይሮስ ኦራል ባይብል ፍላጎት በቂ የታሪክ ስብስቦችን በእንግልዝኛ ቋንቋ በማዘጋጀት ከዚያም ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም መቻል ነ ው፡ ፡ ዛሬ በዓለማችን ወንጌል ያልደረሳቸዉ ስልሳ አምስቱ ፐርሰንት ሕዝብ መጻፍና ማንበብ የማያ ችሉ ናቸው፡ ፡ መቼም የነ ሱ የሆነ ብቸኛዉ መጽሐፍ ቅዱስ ሰምቶ በልባቸዉና በአይምሯቸዉ ወስጥ ልያኖሩት የሚቻላቸዉን ብቻ ነ ው፡ ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል የሰዉን ሕይወት ለማለወጥ ሐይል እንዳለዉ ይነ ግረናል፡ ፡ ምናልባት ኦራል ባይብል በዓለም ዙሪያ ይሰራል ከዚህም የተነ ሳ ወንጌልን ያልሰሙ ሰዎች እግዚአብሔርን በማመን እንደ ቃሉ ኖራሉ ብለን እናምናለን፡ ፡

# መዉጽጫ

## ብሉይ ኪዳን


| | |
|---|---|
| ፍጥረት | 7 |
| አዳምና ሕዋን | 7 |
| ሰዉወድቀት | 8 |
| ቃይንና አቤል | 9 |
| ኖኅ | 9 |
| ሴጣንና የዚህ ዘለምመናፍስት | 10 |
| አብራም | 11 |
| ሣራና አጋር | 11 |
| ኪዳንና የይስሃቅ ወልደት | 12 |
| አብራሃምና ይስሃቅ | 12 |
| ያዕቆብና የተሰረቀዉበረከት | 13 |
| ያዕቆብና ዔሳዉ ታረቁ | 14 |
| ህልመኛዉዮሴፍ | 15 |
| ዮሴፍ ገዥሆነ | 16 |
| ሙሴና የሚቃጠለዉየእሾህ ቁጥቋጦና ፈርዖን | 17 |
| ፋሲካና ቀይ ባህርን መሻገር | 18 |
| 10 ትዕዛዛት | 18 |
| ሰላዮች | 20 |
| እስራኤላዊያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ | 21 |
| ኢያርኮ | 21 |
| ዳዊትና ጎልያድ | 22 |
| ዳዊት ሳኦልን መግደል ተወ | 23 |
| ኤልያስ | 24 |
| የመበለቷ ዘይት | 25 |
| ንዕማን | 25 |

የምሳሩ ብረት---------- 26

ዮናስ ---------- 26

ዳንኤል---------- 27

ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ---------- 28

ነህምያ ---------- 29

## አዲስ ኪዳን

የኢየሱስ ትውልድ---------- 30

የኢየሱስ ማጥመቅ---------- 31

የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙር --------ት---------- 32

ኢየሱስ ሽባ ፈወሰ ---------- 32

የዘሪው ምሳሌ---------- 33

ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ ---------- 33

አጋንንት ያደረበት የጌርጌሴኖን ሰው---------- 33

ኢያኢሮስ ---------- 34

ደጉ ሳምራዊ---------- 34

እጁ የሰለለ ሰው---------- 35

የፈሪሳዊያን ግብዝነት---------- 35

ኒቆዲሞስ ---------- 36

ኢየሱስ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛት ሴት---------- 36

አንተ ክርስቶስ ነህ---------- 37

አልዓዛርና ባለ ጠጋው ሰው---------- 37

ፈሪሳዊውና ቀራጩ ሰው---------- 38

ሀብታሙ ወጣት ገዥ---------- 38

አባካኙ ልጅ---------- 39

ይቅርታ ማድረግ---------- 39

ዘኪዎስ ---------- 40

በርጠሜዎስ ---------- 40

በክብር መግባት------------------------------------------------ 41

ሜሪያምኢየሱስን ቀባች------------------------------------------------ 41

የጌታ እራት------------------------------------------------ 41

የኢየሱሰስ ሞዝና መከሰስ------------------------------------------------ 42

የኢየሱስ መስቀል------------------------------------------------ 43

ትንሳኤ------------------------------------------------ 44

በዓለ ኀምሣ------------------------------------------------ 45

ሜልካምበሜኡአት በመቅደስ ደጅ የተደረገ ፈዉስ------------------------------------------------ 45

ጴጥሮስና ዮሐንስ በክስ ላይ------------------------------------------------ 46

ሐናንያና ሰጲራ------------------------------------------------ 47

እስጢፋኖስ------------------------------------------------ 47

ጦንቐዉስምኡን------------------------------------------------ 48

የኢትዮጵያ ጃንደረባ በኢየሱስ አሜ ------------------------------------------------ 48

ወደ ደማስቆ የሚወስድ መንገድ------------------------------------------------ 49

ጴጥሮስና ቆርኔልዎስ------------------------------------------------ 49

የፍልጳስዩስ እስረኛ------------------------------------------------ 50

ለሚይታወቅ አምላክ------------------------------------------------ 51

ራዕይ------------------------------------------------ 52

# ብሉይ ኪዳን

ፍጥረት ዘፍ 1

1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። 2 ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም
ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።

3 እግዚአብሔርም፦ ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ። 4 እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ
ብርሃኑንና ጨለማውንም ለየ። 5 እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፥ ጨለማውንም ሌሊት አለው።

6 እግዚአብሔርም፦ ሰማይን ፈጠረ፤ 9 ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገለጥ አለ
እንዲሁም ሆነ። 11 እግዚአብሔርም፦ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ
ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ። 12 እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።
14-16 እግዚአብሔር ፀሓይን፣ ጨረቃንና ኳክብትን ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ
ዘንድ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ ዘንድ ፈጠረቸው፡ 20 እግዚአብሔርም አለ፡- ውኃ
ሕያውነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፥ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ። 21
እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። 22 እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው፦ ብዙ ተባዙም
የባሕርንም ውኃ ሙሉአት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ።

25 እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የሜዳ
ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።

26 እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥
እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። 27 እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ
ፈጠረ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። 28 እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥
ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፡

29 እግዚአብሔርም አለ፡- እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል
ሁሉ፥ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ፡ 30 ለምድርም አራዊት ሁሉ፥ ለሰማይም
ወፎች ሁሉ፥ ሕያውነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችም ሁሉ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁንላቸው
እንዲሁም ሆነ። 31 እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም
ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን።

**አዳምና ሕዋን** ዘፍ 2

1 ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። 3 እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም ሊያደርገው ከፈጠረው
ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና።

7 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው
ነፍስ ያለው ሆነ። 8-14 እግዚአብሔር በዔድን ገነትን ለማቋት ደስ ከሚያሰኘው፥ ለመብላትም መልካም ከሆነው ዛፍ ሁሉና
ወርቅ ጋር ተከለ። ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር፡ በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥
መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ።

15 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው። 16 እግዚአብሔር አምላክም
ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፡ ፡ 17 ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ
አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።

18 እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።
19 እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከሜሬት አደረገ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ
ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ ። 20 አዳምም ለእንስሳት
ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው፡ ፡

ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። 21 እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን
ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዷት አጥንትን ወስዶ 22 ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት።

23 አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።
24 ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። 25 አዳምና ሚስቱ ሁለቱም
ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።

## **የሰዉ ወድቀት** ዘፍ 3

1 እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አወሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር
ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት። 2 ሴቲቱም ለእባቡ አለችው። በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን
3 ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።

4 እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም 5 ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም
መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። 6 ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ
ሆነ ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ
ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። 7 የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ
የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ።

8 እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ወስጥ ሲመላለስ ሰሙ አዳምና ሚስቱም
ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።

9 እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። 10 እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ ዕራቁቴንም
ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። 11 እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ
ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?

12 አዳምም አለ፦ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ። 13 እግዚአብሔር አምላክም
ሴቲቱን፦ ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፦ እባብ አሳተኝና በላሁ።

14 እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፦ ይህን ስላደረግህ የተረገምህ ትሆናለህ በሆድህም ትሄዳለህ፥ አፈርንም
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ። 15 በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ
እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኩናውን ትቀጠቅጣለህ።

16 ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም
ገዥሽ ይሆናል።

17 አዳምንም አለው። የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ
የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ 19 ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ
ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። 20 አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም

አወጣ፥ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና። [21] እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥
አለበሳቸውም። [22] እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አሁንም
እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር [23] ስለዚህ
እግዚአብሔር አምላክ ከዔደን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን ሜሬት ያርስ ዘንድ።

## ቃይንና አቤል ዘፍ 4

[1] አዳምም ሚስቱን ሐዋንን አወቀ ፀነሰችም፥ ቃየንንም ወለደች፡ ፡ [2] ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች። አቤልም በግ
ጠባቂ ነበረ ቃየንም ምድርን የሚያርስ ነበረ። [3] ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን
አቀረበ፡ ፡ [4] አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፡ ፡
[5] ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።

[6] እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? [7] መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ
አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ
ንገሥባት።

[8] ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥
ገደለውም። [9] እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ፦ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው
እኔ ነኝን? [10] አለውም፦ ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል። [11] አሁንም የወንድምህን
ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። [12] በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ
ትሆናለህ።

[13] ቃየንም እግዚአብሔርን አለው፦ ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት። [14] የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።
[15]እግዚአብሔርም ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት። [16] ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡ ፡

## ኖኅ ዘፍ 6-9

6፡[1] ሰዎች በምድር ላይ መብዛት ጀመሩ [5] እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም
ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። [6] እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።
[7] እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ
ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።

[8] ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ። [9] ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ። አካሄዱንም ከእግዚአብሔር
ጋር አደረገ። [10] ኖኅም ሦስት ልጆችን ሴምን ካምን ያፌትንም ወለደ። [13] እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፦ የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ
በፊቴ ደርሶአል ከእነርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና እኔም እነሆ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ። [14] ከጎፈር
እንጨት መርከብን ለአንተ ሥራ በመርከቢቱም ጉርጆችን አድርግ፥ በውስጥም በውጭም በቅጥራን ለቅልቃት። [15] የመርከቢቱ
ርዝመት ሦስት መቶ ክንድ፥ ወርድዋ አምሳ ክንድ፥ ከፍታዋ ሠላሳ ክንድ ይሁን።

[19] ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሥጋ ካለው ከሕያው ሁሉ ሁለት ሁለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ ተባትና
እንስት ይሁን። [20] ከወፍ እንደ ወገኑ፥ ከእንስሳም እንደ ወገኑ፥ ከምድር ተንቀሳቃሽም ሁሉ እንደ ወገኑ በሕይወት
ይኖሩ ዘንድ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ አንተ ይግቡ። [21] ከሚበላውም መብል ሁሉ ለአንተ ወስድ፥ ወደ አንተም
ትሰበስባለህ እርሱም ለአንተም ለእነርሱም መብል ይሆናል። [22] ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ።

[7፡ 1-4] እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፦ ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ሁለት
ሁለት ተባትና እንስት፥ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ
ለአንተ ትወስዳለህ። ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁና የፈጠርሁትንም
ፍጥረት ሁሉ ከምድር ላይ አጠፋለሁና። [5] ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ አደረገ።

[11] በኖኅ ዕድሜ በስድስተኛው መቶ ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በአሥራ ሰባተኛው ዕለት፥ በዚያው ቀን የታላቁ ቀላይ
ምንጮች ሁሉ ተነደሉ፥ የሰማይም መስኮቶች ተከፈቱ [12] ዝናቡም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ሆነ። [13] በዚያውም
ቀን ኖኅ ወደ መርከብ ገባ፥ [16] እግዚአብሔርም በስተ ኋላው ዘጋበት። [17] ዝናቡም ለአርባ ቀን ዘነበ፡ ፡ [19] ውኃውም
በምድር ላይ እጅግ በጣም አሸነፈ ከሰማይም በታች ያሉ ታላላቆች ተራሮች ሁሉ ተሸፈኑ። [23] በምድር ላይ የነበረውም ሁሉ
ተደመሰሰ ከምድርም ተደመሰሱ። ኖኅም አብረውት በመርከብ ከነበሩት ጋር ብቻውን ቀረ። [24] ውኃውም መቶ አምሳ ቀን
በምድር ላይ አሸነፈ።

[8፡ 1] እግዚአብሔርም በምድር ላይ ነፋስን አሳለፈ፥ ውኃውም ጎደለ [5] የተራሮቹም ራሶች ተገለጡ። [13-14] በኖኅ ዕድሜ
በስድስት መቶ አንድ ዓመት በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውኃው ከምድር ላይ ደረቀ፡ ፡ በሁለተኛውም ወር
ከወሩም በሀያ ሰባተኛው ቀን ምድር ደረቀች።

[15] እግዚአብሔርም ለኖኅ እንዲህ ብሎ ነገረው። [16] አንተ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ
ውጣ። [18] ኖኅም ልጆቹንና ሚስቱን የልጆቹንም ሚስቶች ይዞ ወጣ [19] አራዊት ሁሉ፥ ተንቀሳቃሾች ሁሉ፥ ወፎችም ሁሉ፥
በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ሁሉ በየዘመዳቸው ከመርከብ ወጡ። [20] ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠዊያውን ሠራ፥ ከንጹሕም
እንስሳ ሁሉ ከንጹሐን ወፎችም ሁሉ ወሰደ፥ በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ።

[9:1] እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው፦ ብዙ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት። [8፡ 22] በምድር ዘመን
ሁሉ መዝራትና መከር፥ ብርድና ሙቀት፥ በጋና ክረምት፥ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም። [9፡ 3] ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ
መብል ይሁናችሁ ሁሉን እንደ ለምለም ቡቃያ ሰጥኋችሁ። [4] ነገር ግን ነፍሱ ደሙ ያለችበትን ሥጋ አትብሉ [5] ነፍሳችሁ
ያለችበትን ደማችሁን በእርግጥ እሻዋለሁ ከአራዊት ሁሉ እጅ እሻዋለሁ ከሰውም እጅ፥ ከሰው ወንድም እጅ፥ የሰውን
ነፍስ እሻለሁ። [6] የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና። [7] እናንተም
ብዙ፥ ተባዙ በምድር ላይ ተዋለዱ፥ እርበቡባትም።

[12] እግዚአብሔርም አለ፦ በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥ ለዘላለም
የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው [16] ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው
በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘላለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ።

**ሴጣንና የዚህ ዘለም መናፍስት** ኢሳ 14፡ 12-15፣ ሕዝ 28፡ 12-19

***መግቢያ፡ ይህ ታሪክ ሴጣን እንዴት የእግዝአብሔርና የሰዉ ጠላት እንደ ሆነ ይተርካል፡ ፡***

[12] አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ
ምድር ድረስ ተቈረጥህ! [13] አንተን በልብህ። ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ
አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በማኅበሩ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ [14] ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም
እመስላለሁ አልህ። [15] ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ። ሕዝ 28፡ 12 ጥበብን የተሞላህ ውበትህም
የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ። [13] በእግዚአብሔር ገነት በዔደን ነበርህ የከበረ ዕንቍ ሁሉ፥ የሚያብረቀርቅ
ዕንቍ፥ ወርቅ፥ ልብስህ ነበረ የከበሮህና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው
ነበር። [14] አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ በእሳት ድንጋዮች
መካከል ተመላለስህ። [15] ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ። [16] በንግድህ
ብዛት ግፍ በውስጥህ ተሞላ ኃጢአትንም ሠራህ ስለዚህ እንደ ርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ተራራ ጣልሁህ የምትጋርድ

ኪሩብ ሆይ፥ ከእሳት ድንጋዮች መካከል አጠፋሁህ። [17] በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን
አረከስህ በምድር ላይ ጣልሁህ ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ። [18] በበደልህ ብዛት በንግድህም ኃጢአት
መቅደስህን አረከስህ ስለዚህ እሳትን ከወስጥህ አወጥቻለሁ እርስዋም በልታሃለች፥ በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ
አመድ አደርጌሃለሁ። [19] በአሕዛብም ወስጥ የሚያወቁህ ሁሉ ይደነቁብሃል አንተም ለድንጋጤሆነሃል፥ እስከ ዘላለምም
አትገኝም።

**አብራም** ዘፍ 12፤ 13፤ 15

***መግቢያ፡*** *ኖህና ልጆቹ ከመርከብ ከወረዱ ከብዙ ዓመታት በኃላ እግዚአብሔር አብራም ለተባለ ሰዉ ተገለጠ*

*ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደሚከተለዉ ነዉ፡*

12፡ [1] እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።
[2] ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን፡፡ [3] የሚባርኩህንም
እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።

[4] አብራምም እግዚአብሔር እንደ ነገረው ሄደ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ የሰባ አምስት ዓመት
ሰውነበረ። [5] አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን፥ ያገኙትን ከብት ሁሉና በካራን ያገኙአቸውን ሰዎች
ይዞ ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ ወጣ ወደ ከነዓንም ምድር ገቡ። [7] እግዚአብሔርም ለአብራም ተገለጠለትና፦ ይህችን
ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለው። እርሱም ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መሠውያን ሠራ።

13፡ [2] አብራምም በከብት በብርና በወርቅ እጅግ በለጠገ። [5] ከአብራም ጋር የሄደውሎጥ ደግሞ የላምና የበግ መንጋ
ድንኳንም ነበረው። [7] የአብራምንና የሎጥን መንጎች በሚጠብቁት መካከልም ጠብ ሆነ፡፡ [8] አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ
ወንድሞቻች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ። [9] ምድር ሁሉ በፊትህ
አይደለችምን? ከእኔ ትለይ ዘንድ እለምንሃለሁ አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ አንተም ቀኙን
ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ። [10] ሎጥም ዓይኑን አነሣ፥ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት
መሆኑን አየ፡፡ [11] ሎጥም በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መረጠ፡

[14] ሎጥ ከተለየው በኋላም እግዚአብሔር አብራምን አለው። ዓይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሰሜንና ወደ
ደቡብ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ እይ [15] የምታየትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁና። 15፡ [5] ወደ
ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸውትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ
ይሆናል አለው። [6] አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።

**ሦራና አጋር** ዘፍ 16

[1] የአብራም ሚስት ሦራ ግን ለአብራም ልጅ አልወለደችለትም ነበር ስምዋ አጋር የተባለ ግብፃዊት ባሪያም ነበረቻት።
[2] ሦራም አብራምን፦ እነሆ፥ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ ምናልባት ከእርስዋ በልጅ እታነጽ እንደ ሆነ ወደ
እርስዋ ግባ አለችው። [4] እርሱም ወደ አጋር ገባ፥ አረገዘችም እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እመቤትዋን በዓይንዋ
አቃለለች። [6] ሦራም ባሠቀየቻት ጊዜ አጋር ከፊትዋ ኮበለለች።

[7] የእግዚአብሔር መልአክም በውኃ ምንጭአጠገብ በበረሀ አገኛት፡፡ [8] እርሱም፦ የሦራ ባሪያ አጋር ሆይ፥ ከወዴት
መጣሽ? ወዴትስ ትሄጃለሽ? አላት። እርስዋም፦ እኔ ከእመቤቴ ከሦራ የኮበለልሁ ነኝ አለች። [9] የእግዚአብሔር
መልአክም፦ ወደ እመቤትሽ ተመለሺ፥ ከእጅዋም በታች ሆነሽ ተገዢአላት። 11 እነሆ አንቺ ፀንሰሻል፥ ወንድ ልጅንም
ትወልጃለሽ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ፥ እግዚአብሔር መከራሽን ሰምቶአልና። [12] እርሱም የበዳ አህያን
የሚመስል ሰውይሆናል እጁ በሁሉ ላይ ይሆናል፥ የሁሉም እጅ ደግሞ በእርሱ ላይ ይሆናል እርሱም በወንድሞቹ ሁሉ ፊት
ይኖራል። [16] አጋር እስማኤልን ለአብራም በወለደችለት ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰውነበረ።

**ኪዳንና የይስሃቅ ወልደት** ዘፍ 17፣ 18፣ 21

17፡ 1 አብራምም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰውበሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና እንዲህ አለው፡- እኔ ኤልሻዳይ
ነኝ በፊቴ ተመላለስ፥ ፍጹምም ሁን፡ ፡ 4 ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ። 5 ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም
ተብሎአይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። 6 እጅግም አበዛሃለሁ፥
ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ። 8 የከነዓን ምድር ሁሉ፥ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና
ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ። 10 ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። 11 በእኔና በእናንተ
መካከል ላለወም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።

18፡1 ከዚህ ጊዜ በኋላ ብዙም ሳይቆይ እግዚአብሔር አምላክ ለአብራሃም ተገለጠ፡- 10 የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬውጊዜ ወደ
አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች አለ። 18 አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ
ይሆናልና፥ የምድር አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና። 19 ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ
ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና ይህም እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ የተናገረውን
ነገር ሁሉ ያመጣ ዘንድ ነው።

21፡ 1 እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ሣራን አሰበ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሣራ አደረገላት። 2 ሣራም ፀነሰች፥
እግዚአብሔርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት። 3 ሣራ የወለደችለትን የልጁን ስም
ይስሐቅ ብሎ ጠራው። 4 አብርሃምም ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛ ቀን ገረዘው። 5 አብርሃምም
ልጁ ይስሐቅ በተወለደለት ጊዜ የመቶ ዓመት ዕድሜነበረ። 6 ሣራም፡- እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልኛል ይህንንም የሚሰማ
ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል አለች። 7 ደግሞም፡- ሣራ ልጆችን እንድታጠባ ለአብርሃም ማን በነገረው? በእርጅናው ልጅን
ወልጄለታለሁና አለች።

**አብራሃምና ይስሃቅ** ዘፍ 22፡ 1-18

***መግቢያ፡*** *ከጥቂት ጊዜ በኋላ የራሱን ቤተሰብ እንዲማርት አብራሃም እስማኤልን ሰደደ፡ ፡ ነገር ግን የቃል ኪዳን ልጅ
ይስሃቅን ከራሱ ጋር አስቀራ፡ ፡*

1 ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ፡- አብርሃምም፡-
እነሆ፥ አለሁ አለ። 2 የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ሂድ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ
መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።

3 አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፥ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሕቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም
ለመሥዋዕት ሰነጠቀ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ። 4 በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና ቦታውን
ከሩቅ አየ ። 5 አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፡- አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፥
ወደ እናንተም እንመለሳለን።

6 አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለቱም
አብረው ሄዱ። 7 ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው፡- እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው?
አለ። 8 አብርሃምም፡- ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው ሁለቱም አብረው ሄዱ። 9 እግዚአብሔር
ወዳለውም ቦታ ደረሱ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨቱንም ረበረበ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው
በእንጨቱ ላይ አጋደመው። 10 አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ። 11 የእግዚአብሔር መልአክም
ከሰማይ ጠራና አብርሃም አብርሃም አለው 12 እርሱም፡- እነሆኝ አለ። እርሱም፡- በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥
አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ
አለ። 13 አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ወስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ
አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው። 14 አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ
ጠራው እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል።

[15] የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥ [16] እንዲህም አለው፦ እግዚአብሔር፦ በራሴ ማልሁ
ይላል ይህን ነገር አድርገሃልና፥ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና [17] በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ ዘርህንም
እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል [18] የምድር አሕዛብ
ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።

**ያዕቆብና የተሰረቀዉበረከት** ዘፍ 25፡ 20-34፤ 27፡ 1-42፤ 28፡ 5

***መግቢያ፡*** *ይስሃቅ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት የኣንዳኛዉስምአታለዉያዕቆብ ሲሆን የሁለተኛዉስምደግሞዔሳዉ
ነበር፡፡*

[20] ይስሐቅም አርባ ዓመት ሲሆነ ውርብቃን አገባ፡፡ [21] ይስሐቅም ስለሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፥ መካን ነበረችና
እግዚአብሔርም ተለመነው፥ ርብቃም ሚስቱ ፀነሰች። [23] እግዚአብሔርም አላት፦ ሁለት ወገኖች በማኅፀንሽ ናቸው፥
ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይከፈላሉ ሕዝብም ከሕዝብ ይበረታል ታላቁም ለታናሹ ይገዛል። [24] ትወልድ ዘንድ ዘመንዋ
በተፈጸመጊዜም፥ [25] በፊትም የወጣውቀይ ነበረ፥ ሁለንተናወም ጠጉር ለብሶ ነበር ስሙም ዔሳውተባለ። [26] ከዚያም
በኋላ ወንድሙወጣ፥ በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ነበር ስሙም ያዕቆብ ተባለ። እርስዋ ልጆችን በወለደቻቸውጊዜ
ይስሐቅ ስድሳ ዓመት ሆኖት ነበር። [27] ብላቴኖቹም አደጉ ዔሳወም አደን የሚያውቅ የበረሃ ሰውሆነ ያዕቆብ ግን ጭምት
ሰውነበረ፥ በድንኳንም ይቀመጥ ነበር። [28] ይስሐቅም ዔሳውን ይወድ ነበር፥ ካደነ ውይበላ ነበርና ርብቃ ግን
ያዕቆብን ትወድ ነበረች። [29] ያዕቆብም ወጥ ሠራ ዔሳወም ደክሞ ከበረሃ ገባ [30] ዔሳወም ያዕቆብን፦ ከዚህ ከቀዩ ወጥ
አብላኝ፥ እኔ እጅግ ደክሜአለሁና አለው። [31] ያዕቆብም፦ በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥልኝ አለው። [32] ዔሳወም፦ እነሆ፥
እኔ ልሞት ነኝ ይህች ብኵርና ለምኔ ናት? አለ። እንዲሁም ዔሳውብኵርናወን አቃለላት።

[27:1] ይስሐቅ ሸምግሎዓይኖቹ ከማየት በፈዘዙ ጊዜ ታላቁን ልጁን ዔሳወን ጠርቶ፦ ልጄ ሆይ አለውእርሱም፦ እነሆ አለሁ
አለው። [2] እርሱም አለው፦ እነሆ እኔ አረጀሁ፥ የምሞትበትን ቀን አላወቅም። [3] አሁንም ሚዶኛህን የፍላጻህን አፎትና
ቀስትህን ወሰድ፥ ወደ ምድረ በዳም ውጣ፥ አደንም አድንልኝ [4] ሳልሞትምነፍሴ እንድትባርክህ የጣፈጠመብል እኔ
እንደምወደውአዘጋጅተህ አበላ ዘንድ አምጣልኝ። [5] ርብቃም ይስሐቅ ለልጁ ለዔሳውሲነግር ትሰማነበር። ዔሳወም
አደን አድኖ ሊያመጣ ወደ ምድረ በዳ ከሄደ በኋላ ለያዕቆብ እንዲህ ኣለች [9] ወደ መንጋ ሄደህ ሁለት መልካካም ጠቦቶች
አምጣልኝ እነርሱንም ጣፋጭመብል ለአባትህ እንደሚወደውአደርጋለሁ፡፡ [10] ለአባትህም፥ ሳይሞት እንዲባርክህ፥
ይበላ ዘንድ ታገባለታለህ።

[15] ርብቃም ከእርስዋ ዘንድ በቤት የነበረችውን የታላቁን ልጅዋን የዔሳውን መልካሙን ልብስ አመጣች፥ ታናሹን ልጅዋን
ያዕቆብንም አለበሰችው፡፡ [16] የጠቦቶችንምለምድ በእጆቹና በለስላሳውአንገቱ ላይ አደረገች፡፡ [17] የሠራችውን ጣፋጭ
መብልና እንጀራውን ለልጅዋ ለያዕቆብ በእጁ ሰጠችው። [18] ወደ አባቱምገብቶ፦ አባቴ ሆይ አለውእርሱም፦ እነሆኝ ልጄ
ሆይ፥ አንተ ማን ነህ? አለ። [19] ያዕቆብም አባቱን አለው፦ የበኵር ልጅህ እኔ ዔሳውነኝ እንዳዘዝኸኝ አደረግሁ
ነፍስህ ትባርከኝ ዘንድ ቀና በልና ተቀመጥ፥ ካደንሁትም ብላ። [20] ይስሐቅም ልጁን፦ ልጄ ሆይ፥ እንዴት ፈጥነህ
አገኘኸው? አለው። እርሱም፦ እግዚአብሔር አምላክህ ወደ እኔ ስለ አቀረበውነውአለ። [22] ይስሃቅም ይህ ድምፅ
የያዕቆብ ድምፅ ነው፥ እጆች ግን የዔሳውእጆች ናቸውአለው። [24] አለውም፦ አንተ ልጄ ዔሳውነህን? እርሱም፦ እኔ ነኝ
አለ። [25] እርሱም፦ ከልጄ አደን እንድበላና ነፍሴ እንድትባርክህ አቅርብልኝ አለ። [26] አባቱ ይስሐቅም፦ ልጄ ሆይ፥
ወደ እኔ ቅረብ ሳመኝም አለው። [27] ወደ እርሱም ቀረበ፥ ሳመውም የልብሱንም ሽታ አሸተተ፥ ባረከውም፥ እንዲህም አለ፦
የልጄ ሽታ እግዚአብሔር እንደ ባረከውእርሻ ሽታ ነው። [28] እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ የእህልንም
የወይንንም ብዛት ይስጥህ። [29] አሕዛብ ይገዙልህ ሕዝብም ይስገዱልህ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፥ የእናትህም ልጆች
ይስገዱልህ የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን።
[30] ይስሐቅም ያዕቆብን ባርኮ ከፈጸመበኋላ፥ ያዕቆብም ከአባቱ ከይስሐቅ ፊት ከወጣበኋላ፥ ወዲያውበዚያውጊዜ
ዔሳውከአደኑ መጥቶ ገባ። [31] አባቱንም፡ አባቴ ይነሣ፥ ነፍስህም ትባርከኝ ዘንድ ከልጁ አደን ይብላ አለው። [32] አባቱ
ይስሐቅም፡ አንተ ማን ነህ? አለውእርሱም፦ እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳውነኝ አለው። [33] ይስሐቅም እጅግ ደነገጠ
እንዲህም አለ፦ ያደነ ውን አደን ወደ እኔ ያመጣ ማን ነው? አንተ ሳትመጣም ከሁሉ በላሁ ባረክሁትም እርሱም የተባረከ
ሆኖ ይኖራል።
[34] ዔሳወም የአባቱን ቃል በሰማጊዜ ታላቅ እጅግም መራራ ጩኸት ጮኸ፥ አባቱንም፡ አባቴ ሆይ፥ እኔንም ደግሞ ባርከኝ
አለው። [35] እርሱም፦ ወንድምህ በተንኮል ገብቶ በረከትህን ወሰደብህ አለ። [41] ዔሳወም አባቱ ስለ ባረከውበያዕቆብ ቂም
ያዘበት ዔሳወም በልቡ አለ። ለአባቴ የልቅሶ ቀን ቀርቦአል፥ ከዚያም በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገድለዋለሁ።

[42] ለርብቃም ይህ የታላቁ ልጇዋ የዔሳው ቃል ደረሰላት። [28:5] ይስሐቅም ከርብቃ ወንድም ከላባ ጋር እንዲኖር ያዕቆብን
ሰደደው፡፡

## ያዕቆብና ዔሳዉ ታረቁ ዘፍ 32

***መግቢያ፡* ያዕቆብ ከአጎቱ ላባን ጋር 20 ዓመት ኖረ፡፡ ወደ አገሩም ሲመለስ 11 ወንዶች ልጆችና አንድ ልጃገረድ ነበረው፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደሚከተለዉ ይቀርባል፡፡**

[3] ያዕቆብም ወደ ወንድሙ ወደ ዔሳው ከፊቱ መልእክተኞችን ላከ፡፡ [4] እንዲህም ብሎ አዘዛቸው። ለጌታዬ ለዔሳው።
ባሪያህ ያዕቆብ እንዲህ አለ ብላችሁ ንገሩት። በላባ ዘንድ በስደት ተቀመጥሁ እስከ አሁን ድረስ ቆየሁ
[6] መልእክተኞቹም ወደ ያዕቆብ ተመልሰው እንዲህ አሉት። ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን ነበር እርሱም ደግሞ ሊቀበልህ
ይመጣል፥ ከእርሱም ጋር አራት መቶ ሰዎች አሉ።

[7] ያዕቆብም እጅግ ፈርቶ ተጨንቆ እንዲህ ብሎ ጸለየ፡-[9] የአባቴ የአብርሃም አምላክ ሆይ፥ የአባቴም የይስሐቅ አምላክ
ሆይ። ወደ ምድርህ ወደ ተወለድህበትም ስፍራ ተመለስ፥ በጎነትንም አደርግልሃለሁ ያልኸኝ እግዚአብሔር ሆይ
[10] ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የሚገባኝ ነኝ በትሬን ብቻ ይዤ ይህን ዮርዳኖስን
ተሻግሬ ነበርና፥ አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ። [11] ከወንድሜ ከዔሳው እጅ አድነኝ መጥቶ እንዳያጠፋኝ፥
እናቶችንም ከልጆች ጋር እንዳያጠፉ እኔ እፈራዋለሁና። [12] አንተም፡ በእርግጥ መልካም አደርግልሃለሁ፥ ዘርህንም
ከብዛቱ የተነሣ እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ አደርጋለሁ ብለህ ነበር።

[13-18] ከያዘውም ሁሉ ለወንድሙ ለዔሳው እጅ መንሻን አወጣ ሁለት መቶ እንስት ፍየሎችንና ሀያ የፍየል አውራዎችን፥
ሁለት መቶ እንስት በጎችንና ሀያ የበግ አውራዎችን፥ ሠላሳ የሚያጠቡ ግመሎችን ከግልገሎቻቸው ጋር፥ አርባ ላሞች
አሥር በሬ፥ ሀያ እንስት አህያ፥ አሥርም የአህያ ግልገሎችን። ያዕቆብም እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፡- ለጌታዬ ለዔሳው እጅ
መንሻ የሰደደው የባሪያህ የያዕቆብ ነው እርሱም ደግሞ እነሆ ከኋላችን ነው በሉት። [21] እጅ መንሻው ከእርሱ ቀድሞ
አለፈ። [22] በዚያች ሌሊትም ተነሣ፥ ሁለቱን ሚስቶቹንና ሁለቱን ባሪያዎቹን አሥራ አንዱንም ልጆቹን ወስዶ የያቦቅን
ወንዝ ተሻገረ። [24] ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፡፡

አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር። [26] እንዲህም አለው፡- ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ። እርሱም፡-
ካልባረክኸኝ አልለቅቅህም አለው። [27] እንዲህም አለው፡- ስምህ ማን ነው? እርሱም፡- ያዕቆብ ነኝ አለው። [28] አለውም፡-
ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።
[30] ያዕቆብም፡ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች። [31] ጵኒኤልንም ሲያልፍ ፀሐይ ወጣችበት፥
እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር።

[33:1] ያዕቆብም ዓይኑን አነሣ፥ እነሆም ዔሳው ከአራት መቶ ሰዎች ጋር ሲመጣ አየው፥ [3] እርሱም በፊታቸው አለፈ ወደ
ወንድሙም እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ። [4] ዔሳውም ሊገናኘው ሮጠ፥ አንገቱንም አቅፎ ሳመው
ተላቀሱም። [5] ዓይኑንም አነሣና ሴቶችንና ልጆችን አየ፥ እንዲህም አለ፡- እነዚህ ምኖችህ ናቸው? እርሱም፡- እግዚአብሔር
ለእኔ ለባሪያህ የሰጠኝ ልጆች ናቸው አለ።

[8] እርሱም፡- ያገኘሁት ይህ ሠራዊት ሁሉ ምንህ ነው? አለ። እርሱም፡- በጌታዬ ፊት ሞገስን አገኝ ዘንድ ነው አለ።
[9] ዔሳውም፡ ለእኔ ብዙ አለኝ ወንድሜ ሆይ፥ የአንተ ለአንተ ይሁን አለ። [10] ያዕቆብም አለ። እንደዚህ አይደለም ነገር
ግን በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆንሁ እጅ መንሻዬን ተቀበለኝ የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያይ ፊትህን
አይቼአለሁና፥ በቸርነትም ተቀብለኸኛልና። [11] እስኪቀበለውም ድረስ ዘበዘበው። [16] ዔሳውም በዚያን ቀን ወደ ሴይር
መንገዱን ተመለሰ።

## ህልመኛዉ ዮሴፍ ዘፍ 37፣ 39

***መግቢያ፡* ወጣቱ ዮሴፍ ለጽድቅ ቆመ**

[2] ዮሴፍ የአሥራ ሰባት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር በጎችን ይጠብቅ ነበር ዮሴፍም የክፋታቸውን ወሬ ወደ
አባታቸው አመጣ። [3] እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፥ በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት።
[4] ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።

[5] ዮሴፍም ሕልምን አለመ፥ ለወንድሞቹም [6] እኔ ያለምሁትን ሕልም ስሙ [7] እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር
ነበርና፥ እነሆም፥ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተም ነዶች በዙሪያ ከብበው እነሆ ለእኔ ነዶ ሰገዱ።
[8] ወንድሞቹም፡ በእኛ ላይ ልትነግሥብን ይሆን? ወይስ ልትገዛ ይሆን? አሉት። [9] ደግሞም ሌላ ሕልምን አለመ፥

ለወንድሞቹም ነገራቸው፥ እንዲህም አለ፦ እነሆ ደግሞ ሌላ ሕልምን አለምሁ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ
ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ። 10 አባቱም በወኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?
11 ወንድሞቹም ቀኑበት አባቱ ግን ነገሩን ይጠብቀው ነበር።

18 አንድ ቀን ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ ሲመጣ እነርሱም በሩቅ ሳለ አዩትና እንዲ ተባባሉ፥ 19 ያ ባለ ሕልም ይኸው መጣ፡
20 አሁንም ኑ፥ እንግደለውና በአንድ ጉድጓድ ወስጥ እንጣለው። ክፉ አወሬም በላው እንላለን ከሕልሞቹም የሚሆነ ወን
እናያለን። 24 ወስደውም ወደ ጉድጓድ ጣሉት ጉድጓዱም ውኃ የሌለበት ደረቅ ነበረ።
25 እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ ዓይናቸውንም አንሥተው አዩ፥ እነሆም ነገዶች ወደ ግብፅ ለመውረድ ከገለዓድ መጡ
ግመሎቻቸውም ሽቱና በለሳን ከርቤም ተጭነ ውነበር። 27 ኑ፥ ለእስማኤላወያን እንሸጠው፥ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ
አንጣል፥ ወንድማችን ሥጋችንም ነውና። ወንድሞቹም የእርሱን ነገር ሰሙት። 28 እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጉድጓድ
አወጡት ለእስማኤላወያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት።
39፡ 1 ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ
ካወረዱት ከእስማኤላወያን እጅ ገዛው። 2 እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ
በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበረ። 3 ጌታውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ፥ እርሱ የሚሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር
በእጁ እንዲያከናውንለት አየ። 4 ዮሴፍም በጌታው ፊት ሞገስን አገኘ፥ እርሱንም ያገለግለው ነበር በቤቱም ላይ
ሾመው፥ ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው። 5 እንዲህም ሆነ በቤቱ ባለውም ሁሉ ላይ ከሾመው በኋላ እግዚአብሔር የግብፃዊውን
ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው የእግዚአብሔር በረከት በወጪም በግቢም ባለው ሁሉ ላይ ሆነ።
6 የዮሴፍም ፊቱ መልከ መልካምና ውብ ነበረ። 7 ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ የጌታው ሚስት በዮሴፍ ላይ ዓይንዋን ጣለች።
ከእኔም ጋር ተኛ አለችው። 8 እርሱም እንቢ አለ፥ ለጌታውም ሚስት እንዲህ አላት፦ እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር
አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ? 10 ይህንም ነገር በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር
11 እንዲህም ሆነ በዚያን ጊዜ ሥራውን እንዲሠራ ወደ ቤቱ ገባ በቤትም ወስጥ ከቤት ሰዎች ማንም አልነበረም፡ 12 ከእኔ
ጋር ተኛ ስትል ልብሱን ተጠማጥማ ያዘች እርሱም ልብሱን በእጇዋ ትቶላት ሸሸ ወደ ውጪም ወጣ፡ 16 ጌታው ወደ ቤቱ
እስኪገባ ድረስም ልብሱን ከእርስዋ ዘንድ አኖረች። 17 ይህንም ነገር እንዲህ ብላ ነገረችው። ያገባህልን ዕብራዊው
ባሪያ ሊሣለቅብኝ ወደ እኔ ገባ 18 እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ስጮኽ ልብሱን በእጄ ተወና ወደ ውጭ ሸሸ። 19 ጌታውም፡
ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ ብላ የነገረችውን የሚስቱን ቃል በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ፡
20 የዮሴፍም ጌታ ወሰደው፥ የንጉሡ እስረኞችም ወደሚታሰሩበት ስፍራ ወደ ግዞት ቤት አገባው ከዚያም በግዞት ነበረ።
21 እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ ምሕረትንም አበዛለት፥ በግዞት ቤቱም አለቃ ፊት ሞገስን ሰጠው፡ 22 የግዞት ቤቱም
አለቃ በግዞት ያሉትን እስረኞች ሁሉ በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። 23 የግዞት ቤቱም አለቃ በእጁ ያለውን ነገር ከቶ
አላሰበም፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና የሚያደርገውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያቀናለት ነበር።

**ዮሴፍ ገዥ ሆነ** ዘፍ 41፤ 42፤ 45፤ 46

## ***መግቢያ፡*** *ዮሴፍ እስር ቤት በነበረ ጊዜ ፈርዖን ሕልም አየ*

1 ከሁለት ዓመት በኋላም ፈርዖን ሕልምን አየ፥ እነሆም፥ በወንዙ ዳር ቆሞ ነበር። 2 ሥጋቸውም የወፈረ ሰባት ላሞች
ከወንዙ ወጡ፥ 3 ከእነርሱም በኋላ እነሆ መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዝ ወጡ፥ 4 መልካቸው
የከፋ ሥጋቸውም የከሳ እነዚያም ላሞች መልካቸው ያማረውን ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን ላሞች ዋጡአቸው። ፈርዖንም
ነቃ። 5 ደግሞም ተኛ ሁለተኛም ሕልምን አየ። እነሆም በአንድ አገዳ ላይ የነበሩ ያማሩና መልካም የሆኑ ሰባት እሸቶች
ወጡ 6 እነሆም ከእነርሱ በኋላ የሰለቱና በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት እሸቶች ወጡ 7 ሰባቱን ያማሩና የዳበሩ
እሸቶች ዋጡአቸው።

8 በነጋም ጊዜ ነፍሱ ታወከችበት ወደ ሕልም ተርጓሚዎች ሁሉ ወደ ግብፅ ጠቢባንም ሁሉ ልኮ ወደ እርሱ ጠራቸው
ፈርዖንም ሕልሙን ነገራቸው፥ ነገር ግን ከእነርሱ ለፈርዖን የሚተረጉም አልተገኘም። 9-13 የዚያን ጊዜ የጠጅ
አሳላፊዎቹ አለቃ በወይኒ ቤት ያለ ዮሴፍ የሚባል ዕብራዊ ባሪያ ሕልም ይተረጉማል ብሎ ለፈርዖን ተናገረ። 14-
25 ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራ፥ ዮሴፍም ፈርዖንን አለው። የፈርዖን ሕልሙ አንድ ነው እግዚአብሔር ሊያደርገው
ያለውን ለፈርዖን ነግሮታል። 26 ሰባቱ መልካካሞች ላሞች ሰባት ዓመታት ናቸው፥ ሰባቱም መልካካሞች እሸቶች ሰባት
ዓመታት ናቸው ሕልሙ አንድ ነው። 27 ከእነርሱም በኋላ የወጡት የከሱትና መልከ ክፉዎቹ ሰባት ላሞች ሰባት ዓመታት
ናቸው፥ የሰለቱትና የምሥራቅ ነፋስ የመታቸው ሰባቱም እሸቶች እነርሱ ራብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ናቸው።
29 እነሆ በግብፅ ምድር ሁሉ እጅግ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ።

33-34 አሁንም ፈርዖን ብልህና አዋቂ ሰውን ይፈልግ፥ ከሚገኘው ፍሬ በግብፅ ምድር ሁሉ ከአምስት እጅ አንደኛውን እንዲወስድ
በግብፅ ምድር ላይም ይሾመው። 36 በግብፅ ምድር ስለሚሆነውስለ ሰባቱ ዓመታት ራብ እህሉ ተጠብቆ ይኑር፥ ምድሪቱም በራብ

አትጠፉም። [39] ፈርዖንም ዮሴፍን አለው። እንደ አንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም፥ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃልና።
[41] ፈርዖንም ዮሴፍን፦ በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾምሁህ አለው። [42] ፈርዖን ቀለበቱን ከእጁ አወለቀ በዮሴፍ እጅም አደረገው፥ ነጭ
የተልባ እግር ልብስንም አለበሰው፥ በአንገቱም የወርቅ ዝርግፍን አደረገለት፡ ፡ [43] የእርሱም በምትሆን በሁለተኛይቱ ሰረገላ
አስቀማጠው፥ አዋጅ ነጋሪም፡ ስገዱ እያለ በፊት በፊቱ ይጮኽ ነበር እርሱም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ተሾመ፡ [46] ዮሴፍም በግብፅ
ንጉሥ በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበረ።

[42:1] የዮሴፍ አባት ያዕቆብም በግብፅ እህል እንዳለ ሰሞ፥ ልጆቹን [2] እነሆ ስንዴ በግብፅ እንዲገኝ ሰምቼአለሁ ወደዚያ
ወረዱ፥ እንድንድንና እንዳንሞትም ከዚያ ሸምቱልን። [6] ዮሴፍም በምድር ላይ ገዥ ነበረ፥ እርሱም ለምድር ሕዝብ ሁሉ
ይሸጥ ነበር የዮሴፍም ወንድሞች በመጡ ጊዜ በምድር ላይ በግምባራቸው ሰገዱለት። [45:1] ሰዎቹንም ሁሉ ከፊቴ
አስወጡልኝ ብሎ ጮኾ ተናገረ [3] ዮሴፍም ለወንድሞቹ። እኔ ዮሴፍ ነኝ አባቴ እስከ አሁን በሕይወቱ ነወን? አለ።
ወንድሞቹም ይመልሱለት ዘንድ አልቻሉም፥ በፊቱ ደንግጠው ነበርና። [4] ዮሴፍም ወንድሞቹን፦ ወደ እኔ ቅረቡ አለ። ወደ
እርሱም ቀረቡ። እንዲህም አላቸው፦ ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ። [5] አሁንም ወደዚህ ስለ
ሸጣችሁኝ አትዘኑ፥ አትቈርቈሩም እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና። [8] አሁንም እናንተ
ወደዚህ የላካችሁኝ አይደላችሁም፥ እግዚአብሔር ላከኝ እንጂ፡ ፡

[9] አሁንም ፈጥናችሁ ወደ አባቴ ወጡ፥ የራብ ዘመን ገና አምስት ዓመት ቀርቶአልና ፈጥኖ ወደዚህ እንዲህ መጣ
ንገሩት፡ ፡
[25] ከግብፅ አገርም ወጡ፥ ወደ ከነዓንም ምድር ከአባታቸው ከያዕቆብ ዘንድ ደረሱ። [26] ዮሴፍ ገና በሕይወቱ ነው፥
እርሱም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ገዥ ሆኖአል። ያዕቆብም ልቡ ደነገጠ፥ አላመናቸውም ነበርና። [27] እርሱን ያነሡት
ዘንድ ዮሴፍ የሰደዳቸውን ሰረገሎች ባየ ጊዜ የአባታቸው የያዕቆብ የነፍሱ ሕይወት ታደሰች። [46:2] እግዚአብሔርም
በሌሊት ራእይ ለያዕቆብ እንዲ አለው፦ [3] የአባቶችህ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ወደ ግብፅ መውረድ አትፍራ፥ በዚያ
ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና። [4] እኔ ወደ ግብፅ አብሬህ እወርዳለሁ፥ ከዚያም ደግሞ እኔ አወጣሃለሁ ዮሴፍም እጁን
በዓይንህ ላይ ያኖራል።

## ሙሴ፡-የሚቃጠለዉ የእሾህ ቁጥቋጦና ፈርዖን ዘጸ 3፣ 7፣ 8፣ 9

***መግቢያ፡*** *ዮሴፍ ከራሃቡ ሊያስመልጣቸዉ አባቱንና ወንድሞቹን ወደ ግብፅ ከወሰዳቸዉ በኋላ፣ ተከታዉ ትዉልድ ለ 430 ዓመት በዛዉ ስፍራ ቆየ፡ ፡ በግብፅ አገር ስለ ዮሴፍ የማያዉቅ አደስ ፈርዖን ተነሳ፤ የእስራኤልንም ልጆች ሜጨቆን ጀመረ፡ ፡ ከነሱ መካከል ሙሴ የሚባል ከከግብጻዊዉ ፈርዖን እጅ አምልጦ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡ ፡ ከእግዝአብሔር የሆነ ታሪክ እንደሚከተለዉ ነዉ፡*

[3:1] ሙሴ ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ። [2] የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት
ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየ ውእነ ሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነ ድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።
[3] ሙሴም፦ ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። [4] እግዚአብሔር እርሱ
ይመለከት ዘንድ እንደ መጣባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ።
[5] እርሱም፦ እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች ሜሬት ናትና ጫማህን
ከእግርህ አወጣ አለው። [6-8] ደግሞም፦ እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ
የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ጩኸታቸውን ሰማሁ
ሥቃያቸውንም አወቄአለሁ፡ ፡ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ ከዚያችም አገር ወተትና ማር
ወደምታፈስሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ። [10] አሁንም ና፥ ሕዝቤን
የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። [11] ሙሴም እግዚአብሔርን፦ ወደ ፈርዖን
የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው። [13] ሙሴም እግዚአብሔርን፦ እነሆ፥ እኔ
ወደ እስራኤል ልጆች በመጣሁ ጊዜ። የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁም ጊዜ። ስሙስ ማን ነው?
ባሉኝ ጊዜ፥ ምን እላቸዋለሁ? አለ። [14] እግዚአብሔርም ሙሴን፦ **እኔ ነኝ** አለው እንዲህ ለእስራኤል ልጆች ወደ
እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው።

7:6 ሙሴና አሮንም እንዲህ አደረጉ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ። 8 እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል
ተናገራቸው። 9-10 ፈርዖን፡- ተአምራትን አሳዩኝ ሲላችሁ፥ አሮንን፡- በትርህን ወስደህ እባብ እንድትሆን በፈርዖን ፊት
ጣለት በለው። አሮንም በትሩን በፈርዖንና በባሮቹ ፊት ጣለ፥ እባብም ሆነ ች። 11 ፈርዖንም ጠቢባንንና መተተኞችን ጠራ
የግብፅ ም ጠንቋዮች በአስማታቸው እንዲሁ ደግሞ አደረጉ። 12-13 እያንዳንዳቸውም በትራቸውን ጣሉ፥ እባቦችም ሆኑ
የአሮን በትር ግን በትራቸውን ዋጠች። የፈርዖን ልብ ጸና፥ አልሰማቸውምም።

16 እንዲህም ትለዋለህ። የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር፡- በምድረ በዳ እንዲያገለግሉኝ ሕዝቤን ልቀቅ ብሎ ወደ
አንተ ላከኝ እነ ሆም እስከ ዛሬ አልሰማህም። 19 እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ አሮንን፡- በትርህን ወሰድ፥ ደምም
እንዲሆኑ በግብፅ ውኆች በወንዞ ቻቸውም በመስኖቻቸውም በኩሬዎቻቸውም በውኃ ማከማቻዎቻቸውም ሁሉ ላይ እጅህን ዘርጋ
በለው·20 ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው እንዲሁ አደረጉ በትሩንም አነሣ፥ በፈርዖንና በባሪያዎቹም ፊት
የወንዙን ውኃ መታ የወንዙም ውኃ ሁሉ ተለወጠ ደም ሆነ ። 21 በወንዙም የነበሩ ዓሦች ሞቱ ወንዙም ገማ፥ ግብፃ ወያንም
ከወንዙ ውኃ ይጠጡ ዘንድ አልቻሉም ደሙም በግብፅ አገር ሁሉ ነበረ።

8፡ 6 አሮንም በግብፅ ወሆች ላይ እጁን ዘረጋ፤ ጓጉንቸሮችም ወጥተዉ ምድሪቱን ሸፈኑ፡ ፡ 8 ፈርዖንም ሙሴንና አሮነ ንን
አስጠርቶ እንዲህ አላቸዉ፤ ጓጉንቸሮቹን ከእኔና ከሕዝቤ ያርቅ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፤ ከዚያም
ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ትሠዉ ዘንድ ሕዝቡ እንዲሄዱ እፈቅዳለሁ፡ ፡ 12 ሙሴና አሮን ከፈርዖን ዘንድ ከተማለሱ
በኋላ፤ በፈርዖን ላይ እግዚአብሔር ስላመጣቸዉ ጓጉንቸሮች ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፡ ፡ 15 ፈርዖን ችግሩ ጋብ
ማለቱን ባየ ጊዜ ግን ልክ እግዚአብሔር እንደ ተናገረዉ ልቡን በማደንደን ሙሴንና አሮንን አልሰማቸዉም፡ ፡

9፡ 13 እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ ማልደህ ተነ ሣ፥ በፈርኦንም ፊት ቆመህ በለው። የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፡- እንዲያገለግሉኝ ሕዝቤን ልቀቅ። 15 አሁን እጄን ዘርግቼ አንተን ሕዝብህንም በቸነፈር በመታሁህ
ነበር፥ አንተም ከምድር በጠፋህ ነበር 16 ነገር ግን ኃይሌን እገልጥብህ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ላይ ይነገር ዘንድ
ስለዚህ አስነሥቼሃለሁ።

## **ፋስካና ቀይ ባህርን መሻገር** ዘጸ 11፤ 12፤ 14

### ***መግቢያ፡*** *እግዝአብሔር 10 መቅሰፍትን በግብጸዊያን ላይ አመጣ፡ ይህ ታሪክ ከሚጨረሻዉና አስረኛዉ ይጀምራል፡ ፡*

11፡ 1 እግዚአብሔርም ሙሴን፡- በፈርዖንና በግብፅ ላይ ገና አንዲት መቅሰፍት አመጣለሁ፥ 12፡ 21 ሙሴም የእስራኤልን
ሽማግሌዎች ጠርቶ አላቸው። በየቤታችሁ ጠቦት ምረጡ፥ ወስዳችሁም ለፋሲካ እረዱት። 22 በዕቃውም ወስጥ ካለው ደም
ሁለቱን መቃኖችና ጉበኑን እርጩክእናንተም አንድ ሰው ከቤቱ ደጅ እስኪነጋ ድረስ አይወጣ። 23 እግዚአብሔር
ግብፃ ወያንን ይመታ ዘንድ ያልፋልና ደማንም በጉበኑና በሁለቱ መቃኖች ላይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በደጁ ላይ ያልፋል፥
አጥፊወም ይመታችሁ ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተወም። 28 የእስራኤልም ልጆች ፥ እንዲሁም አደረጉ፡ ፡
29 እንዲህም ሆነ እኩል ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር፥ የግብፃ ወያንን በኵር ሁሉ መታ።

30 ፈርዖንም ባሪያዎቹም ሁሉ ግብፃ ወያንም ሁሉ በሌሊት ተነ ሡየ ሞት የሌለበት ቤት አልነ በረምና በግብፅ ምድር ታላቅ
ልቅሶ ሆነ ። 31 ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት ጠርቶ። እናንተ የእስራኤልም ልጆች ተነ ሡ፥ ከሕዝቤ መካከል ወጡ
ሂዱም፥ እንዳላችሁም እግዚአብሔርን አገልግሉ፡ ፡
37 የእስራኤልም ልጆች ከሕፃናትና ሴቶች ሌላ ስድስት መቶ ሺህ ወንዶች የሚሆህል እግረኛ ነበረ። 40 የእስራኤልም
ልጆች በግብፅ ምድር የተቀማጡት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ነ ው።
14:5 ሕዝቡም እንደ ኰበለሉ ለግብፅ ንጉሥነ ገሩት የፈርዖንና የባሪያዎቹም ልብ በሕዝቡ ላይ ተለወጠና። እንዳይገዛልን
እስራኤልን የለቀቅነ ውምን አድርገናል? አሉ። 6 ሰረገላወንም አሰናዳ፥ ሕዝቡንም ከእርሱ ጋር ወሰደ 7 ስድስት መቶ
የተመረጡ ሰረገ ሎችንም፥ የግብፅንም ፈረሶች ሁሉ፥ በእያንዳንዱም ሰረገላ ሁሉ ላይ ሦስተኞችን ወሰደ። 10
የእስራኤልም ልጆች እጅግ ፈሩ፥ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ። 13 ሙሴም ለሕዝቡ። አትፍሩ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን

ግብፃ ውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሐርን ማዳን እዩ።
[14] እግዚአብሐር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው።

[15] እግዚአብሐርም ሙሴን አለው፦ [16] አንተም በትርህን አንሣ፥ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋ፥ ክፈለውም የእስራኤልም
ልጆች በባሕሩ ወስጥ በየብስ ያልፋሉ። [21] ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ እግዚአብሐርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ
ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፥ ባሕሩንም አደረቀው፥ ውኃውም ተከፈለ። [22] የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል
በየብስ ገቡ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው። [23] ግብፃውያንም፥ የፈርዖን ፈረሶችና ሰረገሎች
ፈረሰኞቹም ሁሉ፥ እያሳደዱ በኋላቸው ወደ ባሕር መካከል ገቡ። [26] እግዚአብሐርም ሙሴን፦ እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ፥
ውኃውም በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም ላይ ይመለስ አለው። [27] ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፥
ባሕሩም ማለዳ ወደ መፍሰሱ ተመለሰ ግብፃውያንም ከእርሱ ሸሹ፥ እግዚአብሐርም ግብፃውያንን በባሕሩ መካከል ጣላቸው።

## 10 ትዕዛዛት ዘጸ 19፡ 1-20፡ 23

19፡1 በሦስተኛውም ወር የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ በዚያ ቀን ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ። በተራራውም
ፊት ሰፈረ። [3] ሙሴም ወደ እግዚአብሐር ዘንድ ወጣ እግዚአብሐርም በተራራው ጠርቶ አለው። ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ
ንገር። [4] በግብፃውያን ያደረግሁትን፥ በንስርም ክንፍ እንደ ተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል።
[5] አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት
ትሆኑልኛላችሁ [6] እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ። ለእስራኤል ልጆች የምትነግራቸው
ቃል ይህ ነው።

[7] ሙሴም መጣ፥ የሕዝቡንም ሽማግሌዎች ጠርቶ እግዚአብሐር ያዘዘውን ይህን ቃል ሁሉ በፊታቸው ተናገረ። [8] ሕዝቡ ሁሉ
አንድ አፍ ሆነው። እግዚአብሐር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሐር
አደረሰ።

[9] እግዚአብሐርም ሙሴን፦ ከአንተ ጋር ስነጋገር ሕዝቡ እንዲሰሙ ደግሞም ለዘላለም እንዲያምኑብህ፥ እነሆ በከባድ
ደመና እመጣልሃለሁ አለው። [10] እግዚአብሐርም ሙሴን አለው፦ ወደ ሕዝቡ ሂድ፥ ዛሬና ነገም ቀድሳቸው፥ ልብሳቸውንም
ይጠቡ [11] በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ ሁሉ ሲያዩ እግዚአብሐር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ።
[12] ወሰንም ለሕዝቡ በዙሪያው አድርግላቸው። ወደ ተራራው እንዳትወጡ ጫፉንም እንዳትነኩ ተጠንቀቁ ተራራውንም የነካ
ፈጽሞ ይሞታል 13 ሳያቋርጥ የመለከት ድምፅ ሲነፋ በዚያን ጊዜ ወደ ተራራው ይወጡ።

[14] ሙሴም ከተራራው ወደ ሕዝቡ ወረደ፥ ሕዝቡንም ቀደሰ ልብሳቸውንም አጠቡ። [15] ሕዝቡንም፡ ለሦስተኛው ቀን ተዘጋጁ፥
ወደ ሴቶቻችሁ አትቅረቡ አለ። [16] እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና
እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ በተራራው ላይ ሆነ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ። [17] ሙሴም
ሕዝቡን ከእግዚአብሐር ጋር ለማገናኘት ከሰፈር አወጣቸው ከተራራውም እግርጌ ቆሙ። [18] እግዚአብሐርም በእሳት ስለ
ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣነበር፥ ተራራውም ሁሉ እጅግ
ይናወጥ ነበር። [19] የቀንደ መለከቱም ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ ሙሴ ተናገረ እግዚአብሐርም በድምፅ መለሰለት።

[20] እግዚአብሐርም በሲና ተራራ ላይ ወደ ተራራው ራስ ወረደ እግዚአብሐርም ሙሴን ወደ ተራራው ራስ ጠራው ሙሴም ወጣ።
[21] እግዚአብሐርም ሙሴን። ወረድ፥ እግዚአብሐርን ለማየት ዳርቻውን እንዳያልፉ ከእነርሱም ብዙ እንዳይጠፉ ለሕዝቡ
አስጠንቅቃቸው።

20:1 እግዚአብሐር እነዚህን ቃሎች ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤

2 ከግብፅ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሐር አምላክህ እኔ ነኝ፡፡ 3 ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ፡፡

4 በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለዉ ወይም በውሃ ወስጥ ከሚኖሩት ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን
አታብጅ፡፡ 5 አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሐር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ፡፡

[7] የእግዚአብሔር የአምላክህን ስምያለ አግባብአታንሣ፤ እግዚአብሔር ስሙን ያለ አግባብየሚያነሣውን በደል አልባ
አያደርገውምና፡፡

[8] የሰንበት ቀን ቅዱስ አድርገህ አክብር፡፡ [9] ስድስት ቀን ትሠራለህ፤ ሥራህንም ሁሉ አከናውን፡፡ 10 ሰባተኛዉ ቀን
ግን ምንም አትስሩ፡፡

[12] አባትህንና እናትህን አክብር፡፡

[13] አትግደል፡፡

[14] አታመንዝር፡፡

[15] አትስረቅ፡፡

[16] በባለንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡

[17] የባለንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባለንጀራህን ሚስት ወይምየእርሱን ወንድ አገልጋይ ሆነ ሴት አገልጋይ፤ በሬውንም
ሆነ አህያውን ወይምየእርሱ የሆነ ውን ማናቸውንምነገር አትመኝ፡፡ [22] ከዚያምእግዚአብሔር ሙሴን አለው፤
ለእስራኤላዊያን ይህን ንገራቸው፤ ከሰማይ ሆኜ እንደ ተናገርኋችሁ እናንተ ራሳችሁ አይታችኋል፡፡ [23-24] ከእኔ በቀር
ሌሎች አሚልክት አይኑራችሁ እባርክሃለሁ፡፡

## ሰላዮች ዘኁልቍ13-14

***መግቢያ፡*** *የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ስለ ተቤርናክልና ቅደስና ኑሮ መሜሪያ በመቀበል
በተራራዉላይ ቆዩ፡፡ ከዚህያ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ተስፋይቷ ምድር አከባቢ እስክደርሱ ድረስ መራቸው፡
ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደሚከተለዉይሆናል፡፡*

[13: 1-2] እግዚአብሔርምሙሴን እንዲህ ብሎተናገረው። ለእስራኤል ልጆች የምሰጣትን የከንዓንን ምድር ይሰልሉ ዘንድ
ሰዎችን ላክ ከአባቶች ነገድ ሁሉ እያንዳንዱ በመካከላቸውአለቃየሆነ አንድ ሰውትልካላችሁ። [25-26] ምድሪቱንም
ሰልለውከአርባ ቀን በኋላ ተመለሱ። ወደ ሙሴና ወደ አሮን ወደ እስራኤልምልጆች ማኀበር ሁሉ ሄደውደረሱ፡
[27] እንዲህምብለውነገሩት። ወደ ላክኸን ምድር ደረስን፥ እርስዋምወተትና ማር ታፈስሳለች፥ ፍሬዋምይህ ነው።
[28] ነገር ግን በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ኃያላን ናቸው። ከተሞቻቸውምየተመሸጉ እጅግምየጸኑ ናቸውደግሞምበዚያ
የዔናቅን ልጆች አየን።

[30-33] ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝምአሰኘና። ሟኸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንወረሰውአለ። ከእርሱ ጋር የወጡ
ሰዎች ግን፦ በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብላይ መውጣት አንችልምአሉ። ስለ ሰለሉአትምምድር ክፉ ወሬ
ለእስራኤል ልጆች እያወሩ። እኛ ዞረን የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ምድር ናት በእርስዋምዘንድ
ያየናቸውሰዎች ሁሉ ረጃጅምሰዎች ናቸው። የዔናቅን ልጆች፥ አየን እኛምበዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች
ነበርን፥ ደግሞምእኛ በዓይናቸውዘንድ እንዲሁነበርን አሉ።

[14:1] ማኀበሩምሁሉ ድምፃቸውን አንሥተውጮኹሕዝቡምበዚያ ሌሊት አለቀሱ። [2] በግብፅ ምድር ሳለን ምነ ውበሞትን ኖሮ!
ወይምበዚህ ምድረ በዳ ምነ ውበሞትን ኖሮ! [3] እግዚአብሔርምበሰይፍ እንሞት ዘንድ ወደዚች ምድር ለምን ያገባናል?
ሴቶቻችንና ልጆቻችን ምርኮ ይሆናሉ ወደ ግብፅ መመለስ አይሻለንምን? አሉአቸው። [4] እርስ በርሳቸውም። ኑ፥ አለቃ
ሾመን ወደ ግብፅ እንመለስ ተባባሉ።

[5] ሙሴና አሮንምበእስራኤል ልጆች ጉባኤ ፊት በግምባራቸውወደቁ። [6] ምድርን ከሰለሉት ጋር የነበሩት ኢያሱና ካሌብ
ልብሳቸውን ቀደዱ [7] ለእስራኤልምልጆች ማኀበር ሁሉ። ዞረን የሰለልናት ምድር እጅግ መልካምናት። [8] እግዚአብሔርስ
ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈስሰውወደዚች ምድር ያገባናል እርስዋንምይሰጠናል። [9] ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ
አታምፁ [10] ማኀበሩ ሁሉ ግን በድንጋይ ይወግሩአቸውዘንድ ተማከሩ።

የእግዚአብሔርም ክብር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ተገለጠ፡፡ [11] እግዚአብሔርም ሙሴን። ይህ ሕዝብ እስከ
መቼ ይንቀኛል? በፊቱስ ባደረግሁት ተአምራት ሁሉ እስከ መቼ አያምንብኝም? [12] ከርስታቸው አጠፋቸው ዘንድ በቸነፈር
እመታቸዋለሁ አንተም ከእነርሱ ለሚበዛና ለሚጠነክር ሕዝብ አደርግሃለሁ አለው፡፡ [13] ሙሴም እግዚአብሔርን አለው፡፡
[15] ይህን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው ብትገድል ዝናህን የሰሙ አሕዛብ። [16] እግዚአብሔር ይህን ሕዝብ ወደ ማለላቸው ምድር
ያገባቸው ዘንድ አልቻለምና በምድረ በዳ ገደላቸው ብለው ይናገራሉ። 17 አሁንም፥ እባክህ። እግዚአብሔር ታጋሽና
ምሕረቱ የበዛ፥ አበሳንና መተላለፍን ይቅር የሚል፥ ኃጢአተኞችንም ከቶ የማያነጻ፥ [19] ይህን ሕዝብ ከግብፅ ምድር
ካወጣህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይቅር እንዳልሃቸው፥ እባክህ፥ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር
በል።

[20] እግዚአብሔርም አለ፦ እንደ ቃልህ ይቅር አልሁ [22] በግብፅ ምድርና በምድረ በዳ ያደረግሁትን ተአምራቴንና ክብሬን
ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አሥር ጊዜ ስለ ተፈታተኑኝ፥ [23] ነገሬንም ስላልሰሙ፥ በእውነት ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን
ምድር አያዩም ከእነርሱም የናቀኝ ሰው ሁሉ አያያትም [31] ምርኮኛ ይሆናሉ ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን እነርሱን
አገባቸዋለሁ፥ እናንተም የናቃችኋትን ምድር ያውቃሉ። [34] ምድሪቱን በሰላለችሁባት ቀን ቍጥር፥ አርባ ቀን፥ ስለ
አንድ ቀንም አንድ ዓመት፥ ኃጢአታችሁን አርባ ዓመት ትሸከማላችሁ፥ ቍጣዬንም ታውቃላችሁ። [38] ነገር ግን ምድሪቱን
ሊሰልሉ ከሄዱ ሰዎች ኢያሱና ካሌብ በሕይወት ተቀመጡ፡፡

## እስራኤላዊያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ   ኢያሱ 1፣ 3፣ 4

***መግቢያ፡*** *የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ለ40 ዓመት ተጓዙ፡ ፡ ሙሴ ከሱ በኋለ የእስራኤልን ልጆች ወደ ከነዓን በማምራት እንዲያስገባ ኢያሱን ሚጡ ፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደምከተለዉ ይሆናል፡ ፡*

[1፡1] ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው። [2] ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል አሁንም አንተና ይህ
ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ምድር ይህን ዮርዳኖስ ተሻገሩ። [3፡5] ኢያሱም ሕዝቡን፦
ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ።

[14] በሕዝቡ ፊት ታቦቱንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ፥ [16] ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመወደ ጨው
ባሕር የሚወርደው ውኃ ፈጽሞ ተቋረጠ ሕዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት ተሻገሩ። [17] የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን ታቦት
የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ ሜዳ ጸንተው ቆመው ነበር፥ ሕዝቡም ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው
እስኪሻገሩ ድረስ እስራኤል ሁሉ በደረቅ ሜዳ ተሻገሩ።

[4፡1] እግዚአብሔርም ኢያሱን፦ [2] ከሕዝቡ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው፥ አሥራ ሁለት ሰዎች ምረጥና። [3] በዮርዳኖስ መካከል
የካህናት እግር ከቆሙበት ስፍራ አሥራ ሁለት ድንጋዮች አንሡ ተሸክማችሁም በዚህ ሌሊት በምታድሩበት ስፍራ
አኑሩአቸው ብለህ እዘዛቸው አለው።

[15-16] እግዚአብሔርም ኢያሱን፦ የምስክሩን ታቦት የሚሸከሙትን ካህናት ከዮርዳኖስ እንዲወጡ እዘዝ ብሎ ተናገረው።
[18] የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል በወጡ ጊዜ፥ የካህናቱም እግር ጫማ
ደረቅ ሜዳ መርገጥ በጀመረ ጊዜ፥ የዮርዳኖስ ውኃ ወደ ስፍራው ተመለሰ፥ ቀድሞም እንደ ነበረ በዳሩ ሁሉ ላይ ሄደ።

[20] ከዮርዳኖስም ወስጥ የወሰዱአቸውን እነዚያን አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ኢያሱ በጌልገላ አቆማቸው። [21] ለእስራኤልም
ልጆች እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። በሚመጣው ዘመን ልጆቻችሁ አባቶቻቸውን። እነዚህ ድንጋዮች ምንድር ናቸው? ብለው
ሲጠይቁ፥ [22] ለልጆቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ታስታውቃላችሁ። እስራኤል ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻገረ [23] እስክንሻገር
ድረስ አምላካችሁ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቀ እንዲሁ እስክትሻገሩ ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር
የዮርዳኖስን ውኃ ከፊታችሁ አደረቀ። [24] ይህን ያደረገ ውም፥ የእግዚአብሔር ክንድ ብርቱ መሆኑን የምድር ሕዝቦች ሁሉ
እንዲያውቁና እናንተም አምላካችሁን እግዚአብሔርን ለዘላለም እንድትፈሩ ነው፡ ፡

## **ኢያርኮ** ኢያሱ 6

6፡1 ኢያሪኮም ከእስራኤል ልጆች የተነሣ ፈጽማ ተዘግታ ነበር ወደ እርስዋ የሚገባ ከእርስዋም የሚወጣ ማንም
አልነበረም። [2] እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው። ተመልከት፥ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ጽኑዓን ኃያላንዋንም በእጅህ
ሰጥቼአለሁ። [3] ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ ይዞሩአት እንዲሁም ስድስት ቀን አድርጉ። [4] ሰባትም ካህናት
ሰባት ቀንደ ማለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ፥ ካህናቱም ቀንደ ማለከቱን
ይንፉ። [5] ቀንደ ማለከቱም ባለማቋረጥ ሲነፉ፥ የማለከቱንም ድምፅ ስትሰሙ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ
የከተማይቱም ቅጥር ይወድቃል፥ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ይገባባታል።

6 ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ። የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ ማለከት ወስደው በእግዚአብሔር
ታቦት ፊት ይሂዱ አላቸው። [7] ሕዝቡንም። ሂዱ፥ ከተማይቱንም ዙሩ፥ ሰልፈኞችም በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ አለ።
[10] ኢያሱም ሕዝቡን፦ እኔ። ጩኹ እስከምልበት ቀን ድረስ አትጩኹ ድምፃችሁንም አታንሡ ከአፋችሁም አንድ ቃል
አይወጣ በዚያን ጊዜ ትጮኻላችሁ ብሎ አዘዛቸው። [11] እንዲሁ የእግዚአብሔርን ታቦት አንድ ጊዜ ከተማይቱን አዞረው
እነርሱም ወደ ሰፈሩ ተመልሰው አደሩ።

[12] ኢያሱም ማለዳ ተነሣ ካህናቱም የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸከሙ። [13] ሰባቱም ካህናት ሰባት ቀንደ ማለከት ይዘው
በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሄዱ ነበር ቀንደ ማለከቱንም ይነፉ ነበር። 14 ስድስት ቀንም እንዲህ አደረጉ።
[15] በሰባተኛውም ቀን በነጋ ጊዜ ማልደው ተነሡ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ። [16] በሰባተኛውም ጊዜ ካህናቱ ቀንደ
ማለከቱን ሲነፉ ኢያሱ ሕዝቡን አለ። እግዚአብሔር ከተማይቱን ሰጥቶአችኋልና ጩኹ። [17] ከተማይቱም በእርስዋም ያለው
ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም ይሆናሉ። [19] ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ
ይሁን ወደ እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ።

[20] ሕዝቡም ጮኹ ካህናቱም ቀንደ ማለከቱን ነፉ ሕዝቡም የቀንደ ማለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታላቅ ጩኸት ጮኹ ቅጥሩም
ወደቀ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ወደ ፊቱ ወደ ከተማይቱ ወጣ ከተማይቱንም ወሰዱ። [24] ከተማይቱንም በእርስዋም
የነበረውን ሁሉ በእሳት አቃጠሉ ነገር ግን ብሩንና ወርቁን የናሱንና የብረቱንም ዕቃ በእግዚአብሔር ግምጃ ቤት
አደረጉት። [27] እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር ነበረ ዝናውም በምድር ሁሉ ላይ ወጣ።

## **ዳዊትና ጎልያድ** 1ሳሙ17

***መግቢያ፡*** *ከኢያሱ ከብዙ ዓመት በኋላ ሳኦል የሚባል ሰዉ የእስራኤል ንጉስ ሆነ፡፡ በዚህን ጊዜ የፍልስጤም ወታደሮች እስራኤልን ይዋጉ ነበረ፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ ይህ ነዉ፡*

17፡1 ፍልስጥኤማውያን ለዉጊያ ሀይላቸዉን አሰባሰቡ፡፡ [2] ሳኦልና የእስራኤል ሰዎች ተከማቹ፥ በዔላ ሸለቆም ሰፈሩ፥
ከፍልስጥኤማውያንም ጋር ሊዋጉ ተሰለፉ። [4] ከፍልስጥኤማውያንም ሰፈር የጌት ሰው ጎልያድ፥ ቁመቱም ስድስት ክንድ
ከስንዝር የሆነ፥ ዋነኛ ጀግና መጣ። [8] እርሱም ቆሞ ወደ እስራኤል ጭፍሮች ጮኸ። ለሰልፍ ትሠሩ ዘንድ ለምን ወጣችሁ?
እኔ ፍልስጥኤማዊ፥ እናንተም የሳኦል ባሪያዎች አይደላችሁምን? ለእናንተ አንድ ሰው ምረጡ ወደ እኔም ይውረድ
[9] ከእኔም ጋር ሊዋጋ ቢችል ቢገድለኝም ባሪያዎች እንሆናችኋለን እኔ ግን ባሸንፈው ብገድለውም እናንተ ባሪያዎች
ትሆኑናላችሁ፥ ለእኛም ትገዛላችሁ አለ። [10] ፍልስጥኤማዊውም። ዛሬ የእስራኤልን ጭፍሮች ተገዳደርኋቸው እንዋጋ

ዘንድ አንድ ሰው ስጠኝ አለ። [11] ሳኦልና እስራኤልም ሁሉ እንዲህ የሚሉቸውን የፍልስጥኤማዊውን ቃል በሰሙጊዜ እጅግ
ፈሩ፥ ደነገጡም።

[14] ዳዊት ከእሴይ ልጆች የሁሉ ታናሽ ነበረ፡ ፡ [15] ዳዊትም የአባቱን በጎች ለማጠበቅ ከሳኦል ዘንድ ወደ ቤተ ልሔም
ይመላለስ ነበር። [17] እሴይም ልጁን ዳዊትን እንዲህ አለው፦ ከዚህ ከተጠበሰው እሸት አንድ የኢፍ መስፈሪያ እነ ዚህንም
አሥር እንጀራዎች ለወንድሞችህ ወሰድ፥ ወደ ሰፈሩም ወደ ወንድሞችህ ፈጥነ ህ አድርሳቸው፡ ፡ [20] ዳዊትም ማልዶ ተነ ሣ
እሴይም ያዘዘውን ይዞ ሄደ ጭፍራውም ተሰልፎ ሲወጣ ለሰልፍም ሲጮኽ በሰረገሎች ወደ ተከበበው ሰፈር መጣ። [23] እርሱም
ከወንድሞቹ ጋር ሲነ ጋገር፥ እነ ሆ፥ ጎልያድ የተባለው ያ ዋነ ኛ ጀግና ከፍልስጥኤማውያን ጭፍራ መካከል ወጣ፤
የተናገረውንም ቃል ተናገረ ዳዊትም ሰማ። 26 የሕያወን አምላክ ጭፍሮች የሚ ዳደር ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን
ነ ው? ብሎ ተናገ ራቸው። [31] ዳዊትም የተናገ ረው ቃል ተሰማ፤ ለሳኦልም ነገሩት ወደ እርሱም አስጠራው። [32] ዳዊትም
ሳኦልን፦ ስለ እርሱ የማንም ልብ አይወደቅ እኔ ባሪያህ ሄጄ ያንን ፍልስጥኤማዊ እወጋዋለሁ አለው። [33] ሳኦልም
ዳዊትን፦ አንተ ገና ብላቴና ነ ህና፥ [36] እኔ ባሪያህ አንበሳና ድብ መታሁ ይህም ያልተገረዘው ፍልስጥኤማዊ የሕያወን
አምላክ ጭፍሮች ተገዳድሮአልና ከእነ ርሱ እንደ አንዱ ይሆናል። [40] ከዚህያ በኋለ ዳዊትም በትሩን በእጁ ወሰደ፥
ከወንዝም አምስት ድብልብል ድንጋዮችን ሚረጠ፤ በእረኛ ኮረጆውም በኪሱ ከተታቸው ወንጭፍም በእጁ ነ በረ ወደ
ፍልስጥኤማዊውም ቀረበ።

42-44 ጎልያድም ዳዊትን ትኩር ብሎ አየ ው ቀይ ብላቴናም ነበረ፤ እርሱም ዳዊትን፦ ወደ እኔ ና፥ ሥጋህንም ለሰማይ
ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ አለው።

[45] ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን አለው። አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው
በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ። [46] እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል እመታህማለሁ፥ ራስህንም
ከአንተ አነ ሣዋለሁ የፍልስጥኤማውያንንም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ዛሬ እሰጣለሁ። ይኸውም
ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ ታወቅ ዘንድ፡ ፡ [48] ፍልስጥኤማዊውም ተነ ሥቶ ዳዊትን ሊገናኘው በቀረበ
ጊዜ ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ሊገናኘው ወደ ሰልፉ ሮጠ። [49] ዳዊትም እጁን ወደ ኮረጆው አግብቶ አንድ ድንጋይ ወሰደ፥
ወነ ጨፈውም፥ ፍልስጥኤማዊውንም ግምባሩን መታ፥ እርሱም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ። [51] ዳዊትም ሮጦ በፍልስጥኤማዊው
ላይ ቆመ ሰይፉንም ይዞ ከሰገባው መዘዘው፤ ገደለውም፥ ራሱንም ቈረጠው። ፍልስጥኤማውያንም ዋናቸው እንደ ሞተ ባዩ
ጊዜ ሸሹ። 52 የእስራኤል ሰዎች ተነ ሥተው እልል አሉ፥ ፍልስጥኤማውያንንም አሳደዱአቸው። [53] የእስራኤልም ልጆች
ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ ተመልሰው ሰፈራቸውን በዘበዙ።

## **ዳዊት ሳኦልን መግደል ተወ** 1ሳሙ24

### **መግቢያ፡** *የዳዊት ዝና በሰዎች መካከል በወጣ ጊዜ ንጉስ ሳዖል በቅናት ዳዊትን መግደል ፈለገ፡ ፡*

24፡ 2 ሳኦልም ከእስራኤል ሁሉ የተመረጡትን ሦስት ሺህ ሰዎች ወሰደ፥ ዳዊትንና ሰዎቹንም ለመፈለግ የበረሀ ፍየሎች ወደ
ነ በሩባቸው ዓለቶች ሄደ። [3] በመንገ ድም አጠገ ብ ወዳሉት የበጎች ማደሪያዎች መጣ፤ በዚያም ዋሻ ነበረ ሳኦልም ወገቡን
ይሞክር ዘንድ ከዚያ ገባ ዳዊትና ሰዎቹም ከዋሻው በወስጠኛው ቦታ ተቀምጠው ነበር። [4] የዳዊትም ሰዎች። እነ ሆ፥
ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፥ በዓይንህም ደስ የሚያሰኝህን ታደርግበታለህ ብሎ እግዚአብሔር የነገረህ
ቀን፥ እነ ሆ፥ ዛሬ ነ ው አሉት። ዳዊትም ተነ ሥቶ የሳኦልን መጎናጸፊያ ዘርፍ በቀስታ ቈረጠ። [6] ሰዎቹንም።
እግዚአብሔር የቀባው ነ ውና እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት
ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው አላቸው። [7] ዳዊትም በዚህ ቃል ሰዎቹን ከለከላቸው፤ በሳኦልም ላይ ይነ ሡ ዘንድ
አልተዋቸውም ሳኦልም ከዋሻው ተነ ሥቶ መንገ ዱን ሄደ።

[8] ከእርሱም በኋላ ዳዊት ደግሞ ተነ ሣ፥ ከዋሻውም ወጣ፤ ከሳኦልም በኋላ። ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ ብሎ ጮኸ ሳኦልም ወደ
ኋላው ተመለከተ፥ ዳዊትም ወደ ምድር ተጐንብሶ እጅ ነ ሣ። [9] ዳዊትም ሳኦልን አለው። እነ ሆ፥ ዳዊት ክፉ ነገር
ይሻብሃል የሚሉህን ሰዎች ቃል ለምን ትሰማለህ? [10] እነ ሆ፥ ዛሬ በዋሻው ወስጥ እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ እንደ ሰጠህ

ዓይንህ አይታለች አንተንም እንድገድልህ ሰዎች ተናገሩኝ እኔ ግን፦ በእግዚአብሔር የተቀባ ነውና እጄን በጌታዬ ላይ
አልዘረጋም ብዬ ራራሁልህ። [11] ደግሞም፥ አባቴ ሆይ፥ የልብስህ ዘርፍ በእጄ እንዳለ ተመልከተህ እወቅ የልብስህንም
ዘርፍ በቈረጥሁ ጊዜ አልገደልሁህም ስለዚህም በእጄ ክፋትና በደል እንደሌለ እወቅ።

[16] እንዲህም ሆነ ዳዊት ይህን ቃል ለሳኦል መናገር በፈጸመ ጊዜ፥ ሳኦል፦ ልጄ ሆይ ዳዊት፥ ይህ ድምፅህ ነውን? አለ
ሳኦልም ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ። [17] ዳዊትን አለው። እኔ ክፉ በመለስሁልህ ፋንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ
ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ። [18] እግዚአብሔርም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶኝ ሳለ አልገደልኸኝምና ለእኔ መልካም
እንዳደረግህልኝ አንተ ዛሬ አሳየኸኝ። [19] ስለዚህ ለእኔ ስላደረግኸው ቸርነት እግዚአብሔር ይመልስልህ። [20] አሁንም፥
እነሆ፥ አንተ በእርግጥ ንጉሥ እንድትሆን የእስራኤልም መንግሥት በእጅህ እንድትጸና እኔ አውቃለሁ። [21] አሁን
እንግዲህ ከእኔ በኋላ ዘሬን እንዳትቈርጥ ከአባቴም ቤት ስሜን እንዳታጠፋው በእግዚአብሔር ማልልኝ። [22] ዳዊትም
ለሳኦል ማለለት ሳኦልም ወደ ቤቱ ሄደ፥ ዳዊትና ሰዎቹም ወደ አምባው ወጡ።

## ኤልያስ 1ነገ 18

***መግቢያ፡*** *ከዳዊት ጊዜ በኋላ ሌላ አከኣብ የሚባል መጥፎ ንጉስ በእስራኤል ላይ ነገሰ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን ንጉስ የሚቋቋም ሰዉ ነብይ ኤልያስን ላከበት፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደሚከተለዉ ነው፡፡*

[17] አክዓብም ኤልያስን ባየው ጊዜ። እስራኤልን የምትገለባብጥ አንተ ነህን? አለው። [18] ኤልያስም። እስራኤልን
የምትገለባብጡ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ በኣሊምን የተከተላችሁ፥ አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ እኔ
አይደለሁም። [19] አሁንም ልከህ እስራኤልን ሁሉ፥ በኤልዛቤልም ማዕድ የሚበሉትን አራት መቶ አምሳ የበኣልን ነቢያት፥
አራት መቶም የማምለኪያ ዐፀድን ነቢያት ወደ እኔ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሰብስብ አለ። [20] አክዓብም ወደ እስራኤል ልጆች
ሁሉ ልኮ ነቢያቱን ሁሉ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሰበሰበ።

[21] ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ። እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን
እርሱን ተከተሉ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ። ሕዝቡም አንዲት ቃል አልመለሱለትም።

[22] ኤልያስም ሕዝቡን አለ። ከእግዚአብሔር ነቢያት እኔ ብቻ ቀርቻለሁ የበኣል ነቢያት ግን አራት መቶ አምሳ ሰዎች
ናቸው። 23 ሁለት ወይፈኖች ይሰጡን እነርሱም አንድ ወይፈን ይምረጡ፥ እየ ብልቱም ይቍረጡት፥ በእንጨቱም ላይ
ያኑሩት፥ በበታቹም እሳት አይጨምሩ እኔም ሁለተኛውን ወይፈን አዘጋጃለሁ፥ በእንጨቱም ላይ አኖረዋለሁ፥ በበታቹም
እሳት አልጨምርም። [24] እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፥ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ ሰምቶም በእሳት
የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን፦ ሕዝቡም ሁሉ። ይህ ነገር መልካም ነው ብለው መለሱ።

[26] ወይፈኑንም ወስደው አዘጋጁ፥ ከጠዋትም እስከ ቀትር ድረስ። በኣል ሆይ፥ ስማን እያሉ የበኣልን ስም ጠሩ። ድምፅም
አልነበረም፥ የሚመልስም አልነበረም በሠሩትም መሠዊያ ዙሪያ እያነከሱ ያሸበሽቡ ነበር። [27] በቀትርም ጊዜ ኤልያስ።
አምላክ ነውና በታላቅ ቃል ጩኹምናልባት አሳብ ይዞታል፥ ወይም ፈቀቅ ብሎአል፥ ወይም ወደ መንገድ ሄዶአል፥ ወይም
ተኝቶ እንደ ሆነ መቀስቀስ ያስፈልገዋል እያለ አላገጠባቸው። [28] በታላቅም ቃል ይጮኹ፥ እንደ ልማዳቸውም ደማቸው
እስኪፈስስ ድረስ ገላቸውን በካራና በቀጭኔ ይብዋጩ ነበር።

[30] ኤልያስም ሕዝቡን ሁሉ። ወደ እኔ ቅረቡ አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ። ፈርሶ የነበረውንም
የእግዚአብሔርን መሠዊያ አበጀ። [31] ኤልያስም። ስምህ እስራኤል ይሆናል የሚል የእግዚአብሔር ቃል እንደ ደረሰለት
እንደ ያዕቆብ ልጆች ነገድ ቍጥር አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ወሰደ። [32] ከድንጋዮችም ለእግዚአብሔር ስም መሠዊያ ሠራ
በመሠዊያውም ዙሪያ ጕድጓድ ቈፈረ። [33] እንጨቱንም በተርታ አደረገ፥ ወይፈኑንም በብልት በብልቱ ቈረጠ፥ በእንጨቱም
ላይ አኖረና። [34] አራት ጋን ውኃ ሙሉ በሚቃጠለው መሥዋዕትና በእንጨቱ ላይ አፍስሱ አለ። ደግሞም፦ ድገሙ አለ

እነርሱም ደገሙ። እርሱም፦ ሦስተኛ አድርጉ አለ ሦስተኛም አደረጉ። [35] ውኃውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ ደግሞም
ጉድጓዱን በውኃ ሞላው።

[36] መሥዋዕተ ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ። አቤቱ፥ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ
ሆይ፥ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፥ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፥ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ
ዛሬ ይገለጥ። [37] አንተ፥ አቤቱ፥ አምላክ እንደ ሆንህ፥ ልባቸውንም ደግሞ እንደ መለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ
ስማኝ፥ አቤቱ፥ ስማኝ አለ። [38] የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም
አፈሩንም በላች፥ በጉድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች። [39] ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ተደፍተው።
እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ።

## **የመበለቷ ዘይት** 2ነገ 4፡ 1-7

***መግቢያ፡*** *ኤልያስ ወደ ሰማይ ስነጠቅ ኤልሰዕ ለተባለ ነብዩ ስልጣኑን አሳለፈ፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል የሆነ ታሪክ እንደምከተለዉ ይሆናል፡፡*

[1] ከነቢያትም ወገን ሚስቶች አንዲት ሴት። ባሌ ባሪያህ ሞቶአል ባሪያህም እግዚአብሔርን ይፈራ እንደ ነበረ አንተ
ታውቃለህ ባለ ዕዳ ልጆቼን ባሪያዎች አድርጎ ሊወስዳቸው መጥቶአል ብላ ወደ ኤልሳዕ ጮኸች። [2] ኤልሳዕም። በቤትሽ
ያለውን ንገሪኝ አላት። እርስዋም፦ ለእኔ ለባሪያህ ከዘይት ማሰሮ በቀር በቤቴ አንዳች የለኝም አለች።

[3] እርሱም፦ ሄደሽ ከጎረቤቶችሽ ሁሉ ከሜዳ ባዶ ማድጋዎችን ተዋሺ አታሳንሻቸውም አላት። [4] ገብተሽም ከአንቺና
ከልጆችሽ በኋላ በሩን ዝጊ፥ ወደ እነዚህም ማድጋዎች ሁሉ ዘይቱን ገልብጪ የሞላውንም ፈቀቅ አድርጊ አለ።

[5] እንዲሁም ከእርሱ ሄዳ በሩን ከእርስዋና ከልጆችዋ በኋላ ዘጋች እነርሱም ማድጋዎቹን ወደ እርስዋ ያመጡ ነበር፥
እርስዋም ትገለብጥ ነበር። [6] ማድጋዎቹም በሞሉ ጊዜ ልጅዋን፦ ደግሞ ማድጋ አምጣልኝ አለችው እርሱም፦ ሌላ ማድጋ
የለም አላት ዘይቱም ቆመ።

[7] መጥታም ለእግዚአብሔር ሰው ነገረችው እርሱም፦ ሄደሽ ዘይቱን ሽጪ ለባለ ዕዳውም ክፈዪ አንቺና ልጆችሽም ከተረፈው
ተመገቡ አለ።

## **ንዕማን** 2ነገ 5፡ 1-19

***መግቢያ፡*** *ለምፃ የተጠቃ የቆዳ በሽታ ነበረ፡፡*

[1] የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አለቃ ንዕማንም እግዚአብሔር በእርሱ እጅ ለሶርያ ደኅንነትን ስለ ሰጠ በጌታው ዘንድ ታላቅ
ክቡር ሰው ነበረ ደግሞም ጽኑዕ ኃያል ነበረ፥ ነገር ግን ለምጻም ነበረ።

[2] ከእስራኤልም ምድር ታናሽ ብላቴና ሴት ማርከው ነበር የንዕማንንም ሚስት ታገለግል ነበር። [3] እመቤትዋንም፦ ጌታዬ
በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር አለቻት።

[4] ንዕማንም ገብቶ ለጌታው። ከእስራኤል አገር የሆነች አንዲት ብላቴና እንዲህና እንዲህ ብላለች ብሎ ነገረው።
[5] የሶርያም ንጉሥ ንዕማንን፦ ሂድ፥ ለእስራኤል ንጉሥ ደብዳቤ እልካለሁ አለው። እርሱም ሄደ፥ አሥርም መክሊት ብር፥
ስድስት ሺህም ወርቅ፥ አሥርም መለወጫ ልብስ በእጁ ወሰደ።

[7] የእስራኤልም ንጉሥ ደብዳቤውን ባነበበ ጊዜ ልብሱን ቀደደ። ሰውን ከለምጹ እፈውስ ዘንድ ይህ ሰው ወደ እኔ መስደዱ
እኔ በውኑ ለመግደልና ለማዳን የምችል አምላክ ሆኜ ነውን? ተመልከቱ፥ የጠብ ምክንያትም እንደሚፈልግብኝ እዩ አለ።

[8] የእግዚአብሔርምሰውኤልሳዕ የእስራኤል ንጉሥልብሱን እንደ ቀደደ በሰማጊዜ። ልብስህን ለምን ቀደድህ? ወደ እኔ
ይምጣ፥ በእስራኤልምዘንድ ነቢይ እንዳለ ያወቃል ብሎ ወደ ንጉሡላከ። [9] ንዕማንም በፈረሱና በሰረገላው መጣ፥
በኤልሳዕምቤት ደጃፍ ወጭቆመ። [10] ኤልሳዕም። ሂድ፥ በዮርዳኖስምሰባት ጊዜ ታጠበ ሥጋህም ይፈወሳል፥ አንተም
ንጹሕትሆናለህ ብሎ ወደ እርሱ መልእክተኛ ላከ።

[11] ንዕማን ግን ተቈጥቶ ሄደ፥ እንዲህምአለ፦ እነ ሆ፥ ወደ እኔ የሚወጣ፥ ቆሞምየአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም
የሚጠራ፥ የለምጹንምስፍራ በእጁ ዳስሶ የሚፈወሰኝ መስሎኝ ነበር። [12] የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል
ውኆች ሁሉ አይሻሉምን? በእነርሱስ ወስጥ መታጠበና መንጻት አይቻለኝምኖሮአልን? ዘወርምብሎ ተቈጥቶ ሄደ።

[13] ባሪያዎቹምቀርበው። አባት ሆይ፥ ነቢዩ ታላቅ ነገርስ እንኳ ቢነግርህ ኖሮ ባደረግኸውነበር ይልቁንስ። ታጠበና
ንጹሕሁን ቢልህ እንዴት ነዋ! ብለውተናገሩት። [14] ወረደም፥ የእግዚአብሔርምሰውእንደ ተናገረውበዮርዳኖስ ሰባት
ጊዜ ብቅ ጥልቅ አለ ሥጋወምእንደ ገና እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ሆኖ ተመለሰ፥ ንጹሕምሆነ።

[15] እርሱምከጭፍራውሁሉ ጋር ወደ እግዚአብሔር ሰውተመለሰ፥ ወጥቶምበፊቱ ቆመ። እነ ሆ፥ ከእስራኤል ዘንድ በቀር
በምድር ሁሉ አምላክ እንደሌለ አወቅሁ አሁንምከባሪያህ በረከት ትቀበል ዘንድ እለምንሃለሁ አለ። [16] እርሱም፦ በፊቱ
የቆምሁት ሕያውእግዚአብሔርን! አልቀበልምአለ። ይቀበለወም ዘንድ ግድ አለውእርሱ ግን እንቢ አለ።

[17] ንዕማንም። እኔ ባሪያህ ከእንግዲህ ወዲህ ከእግዚአብሔር በቀር ለሌሎች አሜልክት የሚቃጠል መሥዋዕት ወይምሌላ
መሥዋዕት አላቀርብምና ሁለት የበቅሎ ጭነት አፈር እንድወስድ እሺ ትለኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። [19] እርሱም፦ በደኅና
ሂድ አለው።

## የምሳሩ ብረት 2ነገ 6፡ 1-7

[1] የነቢያትምልጆች ኤልሳዕን፦ እነ ሆ፥ በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ ጠበቦናል። [2] ወደ ዮርዳኖስምእንሂድ፥ ከእኛም
እያንዳንዱ ከዚያ ምሰሶ ያምጣ፥ የምንቀመጥበትንምስፍራ በዚያ እንሥራ አሉት እርሱም፦ ሂዱ አለ።

[3] ከእነርሱምአንዱ። አንተ ደግሞከእኛ ከባሪያዎችህ ጋር ለመሄድ ፍቀድ አለ። እርሱም፦ እሄዳለሁ አለ።
[4] ከእነርሱም ጋር ሄደ ወደ ዮርዳኖስምበደረሱ ጊዜ እንጨት ቆረጡ፥ [5] ከእነርሱምአንዱ ምሰሶወን ሲቆርጥ የምሳሩ
ብረት ወደ ወኃውወስጥ ወደቀ እርሱም፦ ጌታዬ ሆይ፥ ወየው! ወየው! የተዋስሁት ነበረ ብሎ ጮኸ። [6] የእግዚአብሔርም
ሰው። የወደቀውወዴት ነው? አለ ስፍራወንምአሳየውእንጨትምቆርጦ በዚያ ጣለው፥ ብረቱምተንሳፈፈ። [7] እርሱም፦
ወሰደውአለ እጁንምዘርግቶ ወሰደው።

## ዮናስ 1፤ 2፤ 3፤ 4

### **መግቢያ፡** *በዮናስ ዘመን ነነዌ የእስራኤል ጠላት የነበረችዉየሶርያ ዋና ከተማነበለች፡፡*

[1] የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ። [2] ተነ ሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማወደ ነነዌ ሂድ፥
ክፋታቸወም ወደ ፊቴ ወጥቶአልና በእርስዋ ላይ ስበክ። [3] ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ይኰብልል ዘንድ
ተነሣ ወደ ኢዮጴም ወረደ፥ [4] እግዚአብሔርምበባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን አመጣ፥ በባሕርምላይ ታላቅ ሞገድ ሆነ፥
መርከቢቱምልትሰበር ቀረበች። [7] እርስ በእርሳቸወም። ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንዳገኘን እናወቅ ዘንድ ኑ፥
ዕጣእንጣጣል ተባባሉ። ዕጣም ተጣጣሉ፥ ዕጣወምበዮናስ ላይ ወደቀ። [8] የዚያን ጊዜም። ይህ ክፉ ነገር በማን
ምክንያት እንዳገኘን እባክህ ንገረን ሥራህ ምንድር ነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ ወዴት ነው? ወይስ ከማን ወገን
ነህ? አሉት። [9] እርሱም፦ እኔ ዕብራዊ ነኝ በሕሩንና የብሱን የፈጠረወን የሰማዩን አምላክ እግዚአብሔርን እመልካለሁ
አላቸው። [10] እነዚያም ሰዎች ከእግዚአብሔር ፊት እንደ ኰብለለ እርሱ ስለ ነገራቸውአወቀዋልና እጅግ ፈሩ፡፡

12 እርሱም፦ ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገኛችሁ አወቃለሁና አንሥታችሁ ወደ ባሕር ጣሉኝ፥ ባሕሩም ጸጥ
ይልላችኋል አላቸው። 15 ዮናስንም ወስደውወደ ባሕሩ ጣሉት ባሕሩምከማናወጡጸጥ አለ። 17 (2፡ 1) እግዚአብሐርምዮናስን
የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ ዮናስምሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣውሆድ ወስጥ ነበረ።

2፡ 1 (2) ዮናስምበዓሣውሆድ ወስጥ ሆኖ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሐር ጸለየ፥እንዲህምአለ፦ 5 (6) የባሕሩ ሣር በራሴ
ተጠምጥሞነበር። 7 (8) ነፍሴ በዛለችብኝ ጊዜ እግዚአብሐርን አሰብሁት ጸሎቴምወደ አንተ ወደ ቅዱስ መቅደስህ ገባች።
9 (10) ደኅንነት ከእግዚአብሐር ዘንድነው።

3:1 የእግዚአብሐርምቃል ሁለተኛ ወደ ዮናስ እንዲህ ሰል መጣ፡ 2 ተነሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማወደ ነነዌ
ሂድ፥ የምነግርህንምስብከት ስበክላት አለው። 3 ዮናስምተነሥቶ እንደ እግዚአብሐር ቃል ወደ ነነዌ ሄደ ነነዌም
እጅግ ታላቅ ከተማነበረች። 4 ዮናስምጮኸ። በሦስት ቀን ወስጥ ነነዌ ትገለበጣለች አለ። 5 የነነዌምሰዎች
እግዚአብሐርን አሙኑ ለጾምአዋጅ ነገሩ፥ ከታላቁምጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ።

7 ንጉሱምአዋጅ አስነገረ፥እንዲህምአለ፦ ሰዎችና እንስሶች ላሞችና በጎች አንዳችን አይቅሙሱ አይሰማሩም ወኃንም
አይጠጡ8 ወደ እግዚአብሐርምበብርቱ ይጩኹሰዎችምሁሉ ከክፉ መንገዳቸወና በእጃቸውካለውግፍ ይመለሱ። 9 እኛ
እንዳንጠፋ እግዚአብሐር ተመልሶ ይጸጸት እንደ ሆነ ፥ ከጽኑ ቍጣውምይመለስ እንደ ሆነ ማን ያወቃል?
10 እግዚአብሐርምከክፉ መንገዳቸውእንደተመለሱ ሥራቸወን አየ እግዚአብሐርምያደርግባቸውዘንድ በተናገረውክፉ
ነገር ተጸጽቶ አላደረገወም። 4፡ 1 ይህምዮናስን ከቶ ደስ አላሰኘወም፤ እርሱምተቈጣ፡ 2 ዮናስምእግዚአብሐርምን
እንዲህ አለ፡ ፡ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፤ ምሕረትህም
የበዛ፥ ከክፉውነገርምየተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አወቄአለው፡ ፡ 3 አሁንም፤ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት
ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ወሰድ አለው። 4 እግዚአብሐርም፦ በወኑ ትቈጣዘንድ ይገባሃልን? አለ።

5 ከከተማይቱምበስተ ምሥራቅ በኩል ተቀመጠከተማይቱንምየሚሆገኛትን እስኪያይ ድረስ በዚያ ተቀመጡ፡
6 እግዚአብሐር አምላክምቅል አዘጋጀ፥ ከጭንቀቱምታድነ ውዘንድ በራሱ ላይ ጥላ እንድትሆን በዮናስ ላይ ከፍ ከፍ
አደረጋት ዮናስምስለ ቅሊቱ እጅግ ደስ አለው። 7 በነጋውግን ወገግ ባለ ጊዜ እግዚአብሐር ትልን አዘጋጀ፥ እርስዋም
ቅሊቱን እስክትደርቅ ድረስ መታቻት። 8 ፀሐይምበወጣች ጊዜ እግዚአብሐር ትኩስ የምሥራቅ ነፋስ አዘጋጀ ዮናስ
እስኪዝል ድረስምፀሐይ ራሱን መታውለራሱምሞትን ፈለገና። ከሕይወት ሞት ይሻለኛል አለ።

9 እግዚአብሐርምዮናስን፦ በወኑ ስለዚች ቅል ትቈጣዘንድ ይገባሃልን? አለው። እርሱም፦ እስከ ሞት ድረስ እቈጣ
ዘንድ ይገባኛል አለ። 10 እግዚአብሐርም፦ አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፤ በአንድ ሌሊት
ለበቀለች፥ በአንድ ሌሊትምለደረቀችውቅል አዝነሃል። 11 እኔስ ቀኛቸወንና ግራቸወን የማይለዩ ከመቶ ሀያ ሺህ
የሚበልጡሰዎችና ብዙ እንስሶች ላሉባት ለታላቂቱ ከተማለነነዌ አላዝንምን? አለው።

## **ዳንኤል** ዳን 1-2

***ሚብያ፡*** *ምንምእግዚአብሐር ብያስጠነ ቅቃቸወምየእስራኤል ሕዝብ ጣዖትን ማምለክ ቀጠሉበት፤ ስለዚህ እግዚአብሐር በምርኮ በባብሎን ንጉስ በነበኬደናዘር እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፡ ፡*

1፡ 1-2 የባቢሎን ንጉሥናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌምመጥቶ ከበባት። ጌታምየይሁዳን ንጉሥኢዮአቄምን
ከእግዚአብሐርምቤት ዕቃ ከፍሎበእጁ አሳልፎ ሰጠው። 3 ንጉሡም በቤቱ መቆምየሚችሉትን ብላቴኖች ከእስራኤል ልጆች
ከነገሥታቱና ከመኳፍንቱ ዘር ያመጣዘንድ ለጃንደረቦች አለቃ ለአስፋኔዝ ነገረ። 6 በእነ ዚህምመካከል ከይሁዳ ልጆች
ዳንኤልና አናንያ ሚኪኤልና አዛርያ ነበሩ።

2:1 ናቡከደነፆርምበነገሠ በሁለተኛውዓመት ናቡከደነፆር ሕልምአለመመንፈሱም ታወከ፥ እንቅልፉምከእርሱ ራቀ።
2 ለንጉሡም ሕልመን እንዲነ ግሩት ንጉሡየ ሕልምተርጓሚዎቹንና አስማተኞቹን መተተኞቹንና ከለዳወያኑንም ይጠሩ ዘንድ

አዘዘ እነርሱም ገብተው በንጉሡ ፊት ቆሙ። [4] ከለዳውያኑም ንጉሡን ። ንጉሥ ሆይ፥ ሺህ ዓመት ንገሥ ለባሪያዎችህ
ሕልምህን ንገር፥ እኛም ፍቺውን እናሳይሃለን ብለው ተናገሩት።

[5] ንጉሡም መልሶ ከለዳውያኑንም፡ ሕልሙና ፍቺውን ባታስታውቁኝ፥ ትቈረጣላችሁ አለ፡፡ [10] ከለዳውያኑም በንጉሡ ፊት
መልሰው። የንጉሡን ነገር ያሳይ ዘንድ የሚችል ሰው በምድር ላይ የለም ከነገሥታትም ታላቅና ኃይለኛ የሆነ እንደዚህ
ያለ ነገር የሕልም ተርጓሚና አስማተኛን ከለዳዊንም አልጠየቀም። [12] ስለዚህም ንጉሡ ተበሳጨ እጅግም ተቈጣ፥
የባቢሎንንም ጠቢባን ሁሉ ያጠፉ ዘንድ አዘዘ። [16] ዳንኤልም ገብቶ ፍቺውን ለንጉሡ የሚያስታውቅበት ጊዜ ይሰጠው ዘንድ
ንጉሡን ለመነ ።

[17-18] የዚያን ጊዜም ዳንኤል ወደ ቤቱ ሄደ። ባልንጀሮቹም ከቀሩት ከባቢሎን ጠቢባን ጋር እንዳይሞቱ ስለዚህ ምሥጢር
ምሕረትን ከሰማይ አምላክ ይለምኑ ዘንድ ነገሩን ለአናንያና ለሚሳኤል ለአዛርያ አስታወቃቸው። [19] የዚያን ጊዜም
ምሥጢሩ በሌሊት ራእይ ለዳንኤል ተገለጠለት ዳንኤልም የሰማይን አምላክ አመሰገነ ።

[24] ከዚህም በኋላ ዳንኤል። የባቢሎንን ጠቢባን አታጥፋ ወደ ንጉሡ አስገባኝ፥ እኔም ፍቺውን ለንጉሡ አሳያለሁ አለው።

[26] ንጉሡም መልሶ ዳንኤልን፦ ያየሁትን ሕልምና ፍቺውን ታስታውቀኝ ዘንድ ትችላለህን? አለው። [27] ዳንኤልም በንጉሡ
ፊት መልሶ እንዲህ አለ፦ ንጉሡ የጠየቀውን ምሥጢር ጠቢባንና አስማተኞች የሕልም ተርጓሚዎችና ቃላተኞች ለንጉሡ
ያሳዩ ዘንድ አይችሉም [28] ነገር ግን ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ወስጥ አለ፥ እርሱም በኋለኛው ዘመን
የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታወቆታል።

[29] አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ ከአንተ በኋላ የሚሆነውምን እንደ ሆነ በአልጋህ ላይ ታስብ ነበር ምሥጢርንም የሚገልጠው
የሚሆነውን ነገር አስታወቆሃል። [31] አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ ታላቅ ምስል አየህ ይህም ምስል ታላቅና ብልጫልጫታው የበዛ
ነበረ፥ በፊትህም ቆሞ ነበር መልኩም ግሩም ነበረ። [32] የዚህም ምስል ራስ ጥሩ ወርቅ፥ ደረቱና ክንዶቹም ብር፥ ሆዱና
ወገቡም ናስ፥ [33] ጭኖቹም ብረት፥ እግሮቹም እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ ነበረ። [34] እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው
ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ። [35] የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፥
ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጩ ነፋስም ወሰደው፥ ቦታውም አልታወቀም ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ
ምድርንም ፈጽሞ ሞላ፡፡
[37] አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይልን፥ ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ
ነህ። 38 አንተ የወርቁ ራስ ነህ። [39] ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሣል ከዚያም በኋላ በምድር
ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ ሦስተኛ የናስ መንግሥት ይነሣል። [40] አራተኛውም መንግሥት ሁሉን እንደሚቀጠቅጥና
እንደሚያደቅቅ ብረት ይበረታል እነዚህንም ሁሉ እንደሚፈጭ ብረት ይቀጠቅጣል ይፈጫል። [43] ብረቱም ከሸክላው ጋር
ተደባልቆ እንዳየህ፥ እንዲሁ ከሰው ዘር ጋር ይደባለቃሉ ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር እንደማይጣበቅ፥ እንዲሁ እርስ
በርሳቸው አይጣበቁም። [44] በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል ለሌላ
ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፉቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች።

[46] የዚያን ጊዜም ንጉሡ ናቡከደነፆር በግምባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት፥ የእህሉንም ቍርባን ዕጣኑንም ያቀርቡለት
ዘንድ አዘዘ። [47] ንጉሡም ዳንኤልን፦ ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት አምላካችሁ የአማልክት
አምላክ፥ የነገሥታትም ጌታ፥ ምሥጢርም ገላጭ ነው ብሎ ተናገረው። [48] ንጉሡም ዳንኤልን በባቢሎን አውራጃ ሁሉ ላይ
ሾመው፡፡

## **ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ** ዳን 6

***መግቢያ፡*** *ከነበቱኬደናፆር ከብዙ ዓመት በኋላ፤ ከሜዶን የሆነ ዳርዮስ ንጉስ ሆነ፡፡*

*ታሪኩ እንዲህ ይተረካል፡፡*

[1:1] ዳርዮስም በመንግሥቱ ሁሉ ዘንድ እንዲሆኑ መቶ ሀያ መሳፍንት በመንግሥቱ ላይ ይሾም ዘንድ ወደደ። [2] ከእነርሱም
አንደኛው ዳንኤል ነበረ። [3] ዳንኤልም መልካም መንፈስ ስላለው ከአለቆችና ከመሳፍንት በለጠ ንጉሡም በመንግሥቱ ሁሉ

ላይ ይሾመው ዘንድ አሰበ። [4] የዚያን ጊዜም አለቆችና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር
ነገር ግን የታመነ ነበረና፥ ስሕተትና በደልም አልተገኘበትምና በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ያገኙበት ዘንድ
አልቻሉም።

[5] እነዚያም ሰዎች። ከአምላኩ ሕግ በቀር በዚህ በዳንኤል ላይ ሌላ ሰበብ አናገኝበትም አሉ። [6] የዚያን ጊዜም አለቆቹና
መሳፍንቱ ወደ ንጉሡ ተሰብስበው እንዲህ አሉት። ንጉሥ ዳርዮስ ሆይ፥ ሺህ ዓመት ንገሥ። [7] የመንግሥቱ አለቆች ሁሉ
ሹማምቶችና መሳፍንት አማካሪዎችና አዛገቶች። ንጉሥ ሆይ፥ ከአንተ በቀር ማንም እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ልመና ከአምላክ
ወይም ከሰው ቢለምን፥ በአንበሶች ጕድጓድ ወስጥ ይጣል የሚል የንጉሥ ሕግና ብርቱ ትእዛዝ ይወጣ ዘንድ ተማከሩ።
[8] አሁንም፥ ንጉሥ ሆይ፥ እንደማይለወጠው እንደ ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ፥ እንዳይለወጥ ትእዛዙን አጽና፥ ጽሕፈቱንም
ጻፍ።

[9] ንጉሡም ዳርዮስ ጽሕፈቱንና ትእዛዙን ጻፈ። [10] ዳንኤልም ጽሕፈቱ እንደ ተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ የእልፍኙም
መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ነበር ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጕልበቱ
ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም። [11] እነዚያም ሰዎች ተሰብስበው ዳንኤል በአምላኩ ፊት ሲጸልይና ሲለምን
አገኙት። [12] ወደ ንጉሡም ቀርበው ስለ ንጉሡ ትእዛዝ። ንጉሥ ሆይ፥ ከአንተ በቀር እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ከአምላክ
ወይም ከሰው የሚለምን ሰው ሁሉ በአንበሶች ጕድጓድ ወስጥ እንዲጣል ትእዛዝ አልጻፍህምን? አሉት። ንጉሡም መልሶ፦
ነገሩ እንደማይለወጠው እንደ ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ እውነት ነው አላቸው።

[13] የዚያን ጊዜም በንጉሡ ፊት መለሰው። ንጉሥ ሆይ፥ ከይሁዳ ምርኮኞች የሆነው ዳንኤል በየዕለቱ ሦስት ጊዜ ልመናውን
ይለምናል እንጂ አንተንና የጻፍኸውን ትእዛዝ አይቀበልም አሉት። [14] ንጉሡም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ በጣም አዘነ፥
ያድነውም ዘንድ ልቡን ወደ ዳንኤል አደረገ ሊያድነውም ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ደከመ። [15] የዚያን ጊዜም እነዚያ ሰዎች
ወደ ንጉሡ ተሰብስበው ንጉሡን፦ ንጉሥ ሆይ፥ ንጉሡ ያጸናው ትእዛዝ ወይም ሥርዓት ይለወጥ ዘንድ እንዳይገባ የሜዶንና
የፋርስ ሕግ እንደ ሆነ እወቅ አሉት። [16] የዚያን ጊዜም ንጉሡ አዘዘ፥ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጕድጓድ ጣሉት
ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም። ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ እርሱ ያድንህ አለው። [17] ድንጋይም አምጥተው በጕድጓዱ
አፍ ላይ ገጠሙት ንጉሡም በዳንኤል ላይ የተደረገው እንዳይለወጥ በቀለበቱና በመኳንንቱ ቀለበት አተመው።

[18] ንጉሡም ወደ ቤቱ ሄደ ሳይበላም አደረ መብልም አላማጡለትም፥ እንቅልፉም ከእርሱ ራቀ። [19] በነጋውም ንጉሡ ማልዶ
ተነሣ፥ ፈጥኖም ወደ አንበሶች ጕድጓድ ሄደ። [20] ወደ ጕድጓዱም ወደ ዳንኤል በቀረበ ጊዜ በኀዘን ቃል ጠራው ንጉሡም
ተናገረ ዳንኤልንም። የሕያው አምላክ ባሪያ ዳንኤል ሆይ፥ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ
ችሎአልን? አለው። [21] ዳንኤልም ንጉሡን፦ ንጉሥ ሆይ፥ ሺህ ዓመት ንገሥ። [22] በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና፥ በአንተም
ፊት ደግሞ፥ ንጉሥ ሆይ፥ አልበደልሁምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ፥ እነርሱም አልጐዱኝም አለው።

[23] የዚያን ጊዜም ንጉሡ እጅግ ደስ አለው፥ ዳንኤልንም ከጕድጓዱ ያወጡት ዘንድ አዘዘ ዳንኤልም ከጕድጓድ ወጣ፥
በአምላኩም ታምኖ ነበርና አንዳች ጕዳት አልተገኘበትም። [24] ንጉሡም አዘዘ፥ ዳንኤልንም የከሰሱ እነዚያን ሰዎች
አማጡአቸው፥ እነርሱንና ልጆቻቸውንም ሚስቶቻቸውንም በአንበሶች ጕድጓድ ጣሉአቸው ወደ ጕድጓዱም መጨረሻ ሳይደርሱ
አንበሶች ያዙአቸው አጥንታቸውንም ሁሉ ሰባበሩ።

[25] የዚያን ጊዜም ንጉሥ ዳርዮስ በምድር ሁሉ ላይ ወደሚኖሩ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩም ቋንቋ ወደሚናገሩ ሁሉ
ጻፈ፥ እንዲህም አለ፦ ሰላም ይብዛላችሁ። [26] በመንግሥቴ ግዛት ሁሉ ያሉ ሰዎች በዳንኤል አምላክ ፊት እንዲፈሩና
እንዲንቀጠቀጡ አዝዣለሁ እርሱ ሕያው አምላክ ለዘላለም የሚኖር ነውና መንግሥቱም የማይጠፋ ነው፥ ግዛቱም እስከ
መጨረሻ ድረስ ይኖራል። [27] ያድናል ይታደግማል፥ በሰማይና በምድርም ተአምራትንና ድንቅን ይሠራል፥ ዳንኤልንም
ከአንበሶች አፍ አደኖታል።

**ነህሚያ** 2፣ 3፣ 4፣ 6

***መግቢያ፡*** *የነህሚያ ታሪክ በአጭሩ ከዳንኤል ዘመን በኋላ የአይሁድ ሕዝብ ከምርኮ በመመለስ ወደ*
*ሀገራቸዉ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸዉ በኋላ የተደረገ ነዉ፡ ነህሚያ ራሱ ስለዚህ ታሪክ*
*ይነግረናል፡፡*

2፡1 በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግስት በሃኛዉ ዓመት የንጉሱ የወይን ጠጅ አሰላፊ ነበርኩ፡ ቀድሜ በፊቱ ዐዝኜ
አላዉቅም ነበር፤ 2 ስለዚህ ንጉሡ፤ "ሳትታመም ፊትህ ለምን እንደህ ዐዘነ? መቼም ይህ የልብ ሐዘን እንጂ ሌላ
አይደለም" አለኝ፡፡ 3 ለንጉሡም "ንጉሡ ለዘላለም ይኑር፤ አባቶቼ የተቀበሩባት ከተማ ስትፈርስ፣ በሮቿም ሲቃጠሉ
ለምን ፊቴ አይዘን?" አልሁት፡፡ ንጉሡም፡ "ታድያ ምን ትፈልጋለህ?" አለኝ፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ አምላክ ጸለሁ፤ 5
ለንጉሡም፤ "ንጉሡን ደስ የሚያሰኘዉ ቢሆንና ባሪያህ በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ፣ እንደ ገና እንድሠራት አባቶቼ ወደ
ተቀበሩባት ወደ ይሁዳ ከተማ እንድሄድ ይፍቀድልኝ" አልሁት፡፡ 6 ንጉሡም እኔን ለማስደድ ደስ አለዉ፡

9 ንጉሡም የጦር አለቆችና ፈረሰኞች አብረዉኝ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ አደረገ፡፡ 11 በዚያም ሶስት ቀን ከቆየሁ
በኋላ 13 በሌሊት ወጥቼ የፈረሱትንም የኢየሩሳሌምን ቅጥሮችና በእሳት የወደሙትን በሮች ተመለከትሁ፡ 16 ለአይሁድ
ወይም ለካህናቱ ወይም ለመኳንንቱ ወይም ለሹማምቱ ወይም ሥራዉን ለሚሠሩት ሰዎች ገና ምንም የተናገርሁት ነገር
ስላልነበረ፣ ወዴት እንደ ሄድሁ ወይም ምን እንዳደረግሁ ሹማምቱ አለወቁም፡ 17 ከዚያም፡ "ያለንበት ችግር ይኸዉ
ታያላችሁ፤ ኢየሩሳሌም ፈርሳለች፤ በሮቿም በእሳት ጋይተዋል፤ አሁንም ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደ ገና እንሥራ፤
ከእንግደህስ መሣለቂያ አንሆንም" አልኋቸዉ፡ 18 እነርሱም፡ እንደ ገና መሥራቱን እንጀምር! ካሉ በኋላ ይህን
መልካም ሥራ ጀመሩ፡፡

19 ነገር ግን ሰንባላጥ፣ ጦቢያና ጌሳም ይህን ሲሰሙ አፌዙብን፤ እንዲህም እንዲህ በማለት አንቋሸሹንንም፤ 4:2 እነዚህ
ደካሞች አይሁድ የሚሠሩት ምንድር ነወ? ይተዉላቸዋልን? ይሠዋሉን? በአንድ ቀንስ ይጨርሳሉን? የተቃጠለዉንስ ድንጋይ
ከፍርስራሹ መልሰው ያድሱታልን? ብሎ ተናገረ። 3 አሞናዊዉም ጦብያ በአጠገቡ ቆሞ፡ በድንጋይ በሚሠሩት ቅጥራቸው ላይ
ቀበሮ ቢወጣበት ያፈርሰዋል አለ።

4 አምላካችን ሆይ፥ ተንቀናልና ስማስድባቸዉን በራሳቸው ላይ መልስባቸው በምርኮ አገር ለብዝበዛ አሳልፈህ
ስጣቸው። 5 በደላቸዉንም አትክደን፥ ኃጢአታቸዉም ከፊትህ አይደምሰስ በሠራተኞች ፊት አስቆጥተዉሃልና። 6 ቅጥሩንም
ሠራን ቅጥሩም ሁሉ እስከ እኩሌታው ድረስ ተጋጠመ የሕዝቡም ልብ ለሥራው ጨከነ ።

7 ሰንባላጥና ጦብያም ዓረባዉያንም አሞናዉያንም አሽዶዳዉያንም የኢየሩሳሌም ቅጥር እየ ታደሰ እንደ ሄደ፥ የፈረሰዉም
ሊጠገን እንደ ተጀመረ በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቈጡ። 9 ወደ አምላካችንም ጸለይን፥ ከእነርሱም የተነሣ በአንጻራቸው
ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን። 14 አይቼም ተነሣሁ፥ ታላላቆቹንና ሹማምቱንም የቀሩትንም ሕዝብ።
አትፍሩአቸው ታላቁንና የተፈራዉን ጌታ አስቡ፥ ስለ ወንድሞቻችሁም ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ልጆቻችሁም ስለ
ሚስቶቻችሁም ስለ ቤቶቻችሁም ተዋጉ አልኋቸው። 16 ከዚያም ቀን ጀምሮ እኩሌቶቹ ብላቴኖቼ ሥራ ይሠሩ ነበር፥
እኩሌቶቹም ጋሻና ጦር ቀስትና ጥሩርም ይዘው ነበር አለቆቹም ከይሁዳ ቤት ሁሉ በኋላ ይቆሙ ነበር። 17 ቅጥሩንም
የሚሠሩትና ተሸካሚዎቹ በአንድ እጃቸው ይሠሩ ነበር፥ በአንድ እጃቸዉም የጦር መሣሪያቸዉን ይይዙ ነበር። 23 እኔና
ወንድሞቼም ብላቴኖቼም በኋላዬም የነበሩት ጠባቂዎች ልብሳችንን አናወልቅም ነበር።

6፡2 ሰንበላጥና ጌሴም "ናና በአንዲቱ መንደር እንገናኝ" ሲሉ ይህችን መልዕክት ላኩብኝ፡፡ እነርሱ ግን እኔን
ለመጉዳት አቅዶ ነበር፡፡ 3 እኔም "ታላቅ ሥራ እየሠራሁ ስለሆነ፣ ወደላችሁበት ስፍራ መዉረድ አልችልም፤ ትቼዉ ወደ
እናንተ ወርጄ ሥራዉ ለምን ይቆማል?" በማለት መልእክተኞችን ወደ እነርሱ ላክሁ፡ 4 አራት ጊዜም ይህንኑ ዐይነት
መልእክት ላኩብኝ፤ እኔም በእያንዳንዱ ጊዜ ያንንኑ መልስ ሰጠሁ፡ 9 እኔ ግን፣ አሁንም እጄን አበርታ ስል
ጸለይሁ፡

10 አንድ ቀን አንድ ሰዉ "ሰዎች ልገድሉህ ይመጣሉ፤ በእግዚአብሔር ቤት ባለዉ በቤተ መቅደሱ ዉስጥ እንገናኝ፤ የቤተ
መቅደሱንም በሮች እንዝጋቸዉ" አለኝ፡፡ 11 እኔ ግን፣ "እንደ እኔ ያለ ሰዉ ሸሽቶ ይደበቃል? ወይም ደግሞ ሕይወቱን
ለማዳን ሲል ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ይገባዋልን? አልሄድም!" አልሁ፡ 12 በእኔ ላይ ትንቢት የተናገረዉ ጦቢና
ሰንባላጥ በገንዘብ ስለ ገዙት እንጂ እግዚአብሔር ወደ እኔ እንዳልላከዉ ተረዳሁ፡

[15] ቅጥሩም በአምሳ ሁለት ቀን ዉስጥ ተጠናቀቀ፡ ፡ [16] ጠላቶቻችን ሁሉ ይህን ሲሰሙ በዙሪያችን ያሉ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ፤ በራሳቸዉ መተማመን አልቻሉም፤ ምክንያቱም ይህ ሥራ የተከናወነዉ በአምላካችን ርዳታ መሆኑን ተገንዝበዋል፡ ፡

## አዲስ ኪዳን

**የኢየሱስ መወለድ** ሉቃስ 1፡ 26፤ /ሉቃስ 2

***መግቢያ፡*** *ከመቶ ዓመታት በፊት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከሴቷ ዘር ሲለማ ኘዉ መሲህ ስናገሩ ቆይተዋል፡ ፡ በቤቴልሄም ከተማ ከድንግል እንደምወለድና ከንጉስ ዳዊት ዘር እንደሆነ በነቢያት ተነ ግሮ ነበር፡ ፡ ይህ ታሪክ ከእግዚአብሔር ቃል ነ ው፡ ፡*

ሉቃ 1፡ 26 እግዝአብሔር መልአኩ ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘዉ ወደ ናዝሬት ከተማ ላከዉ፡ ፡ [27] የተላከዉም ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰዉ ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም ስም ሚርያም ነበረ፡ ፡ [28] መልኣኩም እርሷ ወዳለችበት ገበቶ፡- እጅግ የተወደደሽ ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን ጌታ ከአንቺ ጋር ነዉ አንቺ የተባረክሽ ነሽ አላት፡ ፡

[29] ሚርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም ደንግጣ ይህ ምን አይነት ሰላምታ ይሆን እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፤ [30] መልአኩም እንዲህ አላት፡- ሚርያም ሆይ በእግዝአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ፡ ፡ [31] እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ቲዪዋለሽ፡ ፡ [32] እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑልም ልጅ ይባላል ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ [33] በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘለአለም ይነግሳል፤ ለመንግስቱም ፍጻሜ የለዉም፡ ፡

[34] ሚርያምም መልአኩን፡- እኔ ወንድ ስለማላዉቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል አለችዉ፡ ፡

[35] መልአኩም መልሶ እንደህ አላት መንፈስ ቅዱስ በአንች ላይ ይመጣል የልዑልም ሀይል ይፀልልሻል፤ [37] ለእግዝአብሔር የሚሳነዉ ነገር የለምና፡ ፡

ሉቃ 2፡1 በዚያን ዘመን የአለሙሁሉ ሕዝብ እንድቆጠርና እንድማዝገብ ከአውግስጦስ ቄሳር ትእዛዝ ወጣ፡፡ 3 ስለዝህ
እያንዳንዱ ሰዉ ለመመዝገብ ወደየ ራሱ ከተማ ሄደ፡፡

4 ዮሴፍም ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ በገሊላ አወራጃ ከምትገኘዉ ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ የዳዊት ከተማ ወደ
ሆነችዉ ቤተልሔም ወደምትባል ከተማ ወደ ይሁዳ መጣ፡፡ 5 ወደዚያም ለመመዝገብ የተጓዘዉ የመዉለጃ ግዜዋ ከተቃረበዉ
ከእጮኛዉ ከሚርያም ጋር ነበር፡፡ 6 በዚያም እነዳሉ የምትወልድበት ግዜ ደረሰ፡፡ 7 የበኩር ልጅ የሆነ ዉን ወንድ ልጅ
ወለደች፤ በጨርቅም ጠቀለለችዉ፤ በእንግዶችም ሚረፍያ ቦታ ሰላላገኙ በግርግም አስተኛችዉ፡፡

8 በዚያዉ አገር በለሊት መንጋቸዉን ሲጠብቁ በሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ፡፡ 9 የጌታም መልአክ ድንገት መጥቶ
በአጠገባቸዉ ቆመ፤ የጌታም ክብር በዙርያቸዉ አበራ ታላቅም ፍርሀት ያዛቸዉ፡፡ 10 መልአኩ ግን እንደህ አላቸዉ፦
አትፈሩ ለህዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች አምጥቼላችኋለሁና፡፡ 11 ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኅን
ተወልዶላችኋልና፡ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነዉ፡፡ 12 ይህ ምልክት ይሁናችዉ፤ ህፃን ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም
ተኝቶ ታገኛላችዉ፡፡ ድነጋትም ብዙ የሰማይ ሰራዊት ከመልአኩ ጋር ታዩ፤ እግዝአብሔርንም እያመስገኑ እንደህ አሉ፦
14 ክብር ለእግዝአብሔር በአርያም ሰላምም እርሱ ለሚወዳቸዉ ሰዎች በምድር ይሁን! 15 መላእክቱ ከእርሱ ተለይተዉ ወደ
ሰማይ ከወጡበኋላ እረኞቹ፦ጌታ የገለጠልንን ይህን የሆነ ዉን ነገር እንድናይ ወደ ቤቴልሄም እንሂድ ተባባሉ፡፡ 16
እነርሱም ፈጥነ ው ሄዱ፡ ሚርያምንና ዮሴፍን፣ ህፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ፡፡ 17 ካዩም በኋላ ስለ ህፃኑ
የተነገረቸዉን ገልጠው አወሩ፡፡ 18 ይህንንም የሰሙሁሉ እረኞቹ በነገሯቸው ነገር ተደነቁ፣ 19 ሚርያም ግን ይህንን
ሁሉ በልቧ ይዛ ታሰላስል ነበር፡፡ 20 እረኞቹም ሁሉም ነገር እንደ ተነገራቸው ሆኖ በማግኘታቸው፣ ስለ ሰሙትና
ስላዩት ሁሉ እግዝአብሔርን እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ፡፡

## **የኢየሱስ ማጥመቅ** ሉቃስ 3፡ 1-15 ፣ ማቴ 3፡ 13 ፣ ዮሐ 1፡ 29

***መግቢያ፡*** *እነሆ የእግዚአብሔር በግ!*

1 ጳንጥዮስ ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ በሆነ ጊዜ፣ የእግዝአብሄር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሃንስ በምድረ በዳ መጣ፡፡ 3
እርሱም ለኀጢአት ስርየት የሚሆን የንስሓን ጥምቀት እየ ሰበከ በዮርዳኖስ ወንዝ አከባቢ ወዳሉት ስፍራዎች ሁሉ መጣ
4 ይኸውም ነብዩ ኢሳያስ በመጽሓፉ እንዲህ ሲል በጻፈው ቃል መሠረት ነበር፦

በበርሓ እንዲህ ብሎ የሚጮኸ ሰው ድምፅ፣

የጌታን ን መንገድ አዛጋጁ ጎዳናዋንም አቅኑ፣

5 ሸለቆው ሁሉ ይሞላል፣ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፣

ጠምምው መንገድ ቀና፣ ሸካራውም ጎዳና ትክክል ይሆናል፣

6 የሰው ዘር ሁሉ የእግዝአብሔርን ማዳን ያያል፡፡

7 ዮሓንስም በእርሱ እጅ ሊጠመቁ የወጡትን ሰዎች እንዲህ ይላቸው ነበር፣ « እናንት የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቁጣ
እንድትሸሹ ማን መከራችው? 8 እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ ደግሞም በልባችው፣ ‹ አብርሃም አባታችን አለን›
ማለትን አትጀምሩ፤ እግዝአብሔር ከእነ ዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማስነሳት እንደሚቻል እነግራችኋለሁና፡፡ 9
አሁን እንኳ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጦዋል፤ መልካም ፍሬ የማያፈረም ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል፡፡» 10 ሕዝቡም፡
« ታዲያ፣ ምን እናድርግ?» ብሎ ጠየቁት፡፡ 11 ዮሓንስም ሁለት ልብስ ያለው ምንም ለሌው ያከፍል፤ ምግብ ያለውም
እንዲው ያድርግ» ከዛ ብለው መለሰላቸው፡ 12 ቀረጥ ሰብሳቢዎችም ሊጠመቁ ወደ እርሱ መጥተው፡ « መምህር ሆይ፤ እኛስ
ምን እናድርግ?» አሉት፡፡ 13 እርሱም፡ « ከታዘዛቸውት በላይ ቀረጥ አትሰብስቡ» አላቸው፡ 14 ወታደሮች ደግሞ፡ «
እኛስ ምን እናድርግ?» ብለዉ ተየቁት፡፡ እርሱም፡ የማንንም ገንዘብ በግፍ አትንጠቁ፤ ሰዉንም በሐሰት አትክሰሱ፤
ደመወዛችዉ ይብቃችዉ»፡፡ 15 ሕዝቡም በጉጉት እየተጠበበቁ ሳሉ፣ « እርሱም ክርቶስ ይሆንን?» እያሉ ሁሉም በልባቸዉ
ስለ ዮሐንስ ያሰላስሉ ነበር፡፡ 16 ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸዉ« እኔ በዉሃ አጠምቃችዋለው፤ ነገር ግን
ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እኔም የእርሱን የጫማ ማሰርያ መፍታት የሚገባኝ አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና
በእሳት የጠምቃችኋል፤

ማቴ 3፤ 13-17 በዝያን ግዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለማጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ 14 ዮሐንስ ግን፤ «ይህማ አይሆንም፤
እኔ ባንተ ማጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ?» ብሎ ተከላከለ፡፡ 15 ኢየሱስም፡ «ግድ የለም
ፍቀድልኝ፤ ይህን በሚድረግ ጽድቅን ሁሉ ሚፈጸም ይገባናልና» አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ፡ 16 ኢየሱስም እንደ
ተጠመቀ ከዉሀዉ ወጣ፤ ወድያዉንም ሰማይ ተከፈቶ የእግዝአብሄር መንፈስ እነደ እርግብ ሲወርድበት አየ፡፡ 17 እነሆ
«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወዳዉ ልጄ ይህ ነዉ» የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ፡

ዮሐ 1፤ 29 ዮሐንስ በማግስቱ፣ እየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንደህ አለ፤ «እነሆ! የዓለምን ሀጥያት የሚያስወግድ
የእግዝአብሐር በግ፤

**የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት** ማር 1፡ 16-28

***መግቢያ፡*** *ኢየሱስ ሠላሳ ዓመት ሲሆን ዉአገልግሎቱን ጀመረ፡፡ አገልግሎቱንም የጀመረ ዉደቀመዝሙሮች የሚሆኑትን በመጥራት ነበር፡፡*

16 በገሊላ ባሕርም አጠገብ ሲያልፍ ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥
ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። 17 ኢየሱስም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።
18 ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት። 19 ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙም
ዮሐንስን ደግሞ በታንኳ ላይ መረባቸውን ሲያበጁ አየ ። 20 ወዲያውም ጠራቸው አባታቸውንም ዘብዴዎስን
ከሞያተኞቹ ጋር በታንኳ ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ። 21 ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ፤ ወዲያውም በሰንበት ወደ
ምኵራብ ገብቶ አስተማረ ።

22 እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ። 23 በዚያን
ጊዜም በምኲራባቸው ርኵስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤ 24 እርሱም፦ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን
አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አወቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ። 25 ኢየሱስም፦ ዝም
በል ከእርሱም ወጣ ብሎ ገሠጸው። 26 ርኩሱም መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምፅ ጮኾ ከእርሱ ወጣ።
27 ሁሉም፡ ይህ ምንድር ነው? በሥልጣን ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታልና ይህ አዲስ
ትምህርት ምንድር ነው? ብለው እስኪጠያየቁ ድረስ አደነቁ። 32 ፀሐይም ገብቶ በመሸ ጊዜ፥ የታመሙትንና
አጋንንት ያደረባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤ 34 በልዩ ልዩ ደዌም የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፥ ብዙዎችንም
አጋንንት አወጣ፥ አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን አወቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም። 39 በምኵራባቸውም

እየሰበከ አጋንንትንምእያወጣወደ ገሊላ ሁሉ መጣ።

## ኢየሱስ ሽባ ፈወሰ  ማር 2፡ 1-12

**መግቢያ፡** *የትኛዉ ይበልጥ ይከብዳል? ሚዉስ ወይስ ኃጥአትን ማስተሰረይ?*

2፤ 1 ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆምደግሞገብቶ በቤት እንደ ሆነ ተሰማ፡ 2 በደጅ ያለውስፍራምእስኪጠብቸው
ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንምይነግራቸውነበር። 3 አራት ሰዎችምየተሸከሙትን ሽባ አመጡለት። 4 ስለ
ሕዝቡም ብዛት ወደ እርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሡ ፥ ነድለውም ሽባው የተኛበትን
አልጋ አወረዱ። 5 ኢየሱስምእምነታቸውን አይቶ ሽባውን። አንተ ልጅ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው። 6 ከጻፎችም
አንዳንዶቹ በዚያ ተቀምጠውነበር በልባቸውም፡ ይህ ሰው ስለ ምን እንደዚህ ያለ ስድብ ይናገራል? 7 ከአንዱ
ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ። 8 ወዲያውም ኢየሱስ በልባቸውእንዲህ
እንዳሰቡ በመንፈስ አውቆ እንዲህ አላቸው፦ በልባችሁ ይህን ስለ ምን ታስባላችሁ? 9 ሽባውን። ኃጢአትህ
ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣ አልጋህንምተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸውይቀላል? 10 ነገር ግን ለሰውልጅ
በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለውእንድታውቁ፤ 12 ተነ ሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞበሁሉ
ፊት ወጣ፥ ስለዚህምሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለውእግዚአብሔርን አከበሩ።

## የዘሪውምሳሌ  ማር 4፤ 1-20 ፡ 33

**መግቢያ፡** *ኢየሱስምበምሳሌ ሕዝቡን ያስተምር ጀመር*

1 ደግሞም በባሕር ዳር ሊያስተምር ጀመረ። እጅግ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ ስለ ተሰበሰቡ እርሱ በታንኳ ገብቶ በባሕር
ላይ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕር ዳር በምድር ላይ ነበሩ። 2 በምሳሌም ብዙ ያስተምራቸውነበር፥ በትምህርቱም
አላቸው፡ ስሙ፡ 3-4 እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ፡ ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተውበሉት።
5 ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ስላልነበረውወዲያውበቀለ፤ 6 ፀሐይም ሲወጣ
ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረውደረቀ። 7 ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው፥ ፍሬም አልሰጠም፡
8 ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀና ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ፥ አንዱም ሠላሳ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ አፈራ።

9 "የሚሰማ ጆሮ ያለውይስማ" አለ።

10 ብቻውንም በሆነ ጊዜ፥ በዙሪያውየነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ጋር ስለ ምሳሌው ጠየቁት። 11-12 እንዲህም አላቸው፦
ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭላሉት ግን፥ አይተውእንዲያዩ
እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸውነገር ሁሉ
በምሳሌ ይሆንባቸዋል። 14 ዘሪው ቃሉን ይዘራል። ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው፥ 15 በሰሙ
ት ጊዜም ሰይጣን ወዲያውመጥቶ በልባቸውየተዘራውን ቃል ይወስዳል። 16 እንዲሁም በጭንጫላይ የተዘሩት እነዚህ
ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተውወዲያውበደስታ ይቀበሉታል፥ 17 ለጊዜውምነውእንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ
ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያውይሰናከላሉ። 18 በእሾህም የተዘሩት ሌሎች ናቸው፥ ቃሉን የሰሙት
እነዚህ ናቸው ፥ 19 የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተውቃሉን ያንቃሉ፥
የማያፈራም ይሆናል። 20 በመልካምም መሬት የተዘሩት ቃሉን ሰምተውየሚቀበሉት አንዱም ሠላሳ አንዱም ስድሳ
አንዱም መቶ ፍሬ የሚያፈሩት እነዚህ ናቸው።

33 መስማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸውነበር፤ ያለ ምሳሌ ግን
አልነገራቸውም፥

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ  ማር 4፤ 35-40

**መግቢያ፡** *ደቀመዛሙርት ኢየሱስ ማን እንደ ሆነ ማወቅ ፈለጉ*

35 በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ። ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው። 36 ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዲያውወሰዱት፥ ሌሎች
ታንኳዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ። 37 ብርቱ ዐወሎ ነፋስም ተነሣና ወቃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ
ይገባ ነበር። 38 እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅተውም፡ መምህር ሆይ፥ ስንጠፉ
አይገደህምን? አሉት።

39 ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው ባሕሩንም፡ ዝም በል፥ ፀጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ ። 40 እንዲህ
የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው። 41 እጅግም ፈሩና። እንግዲህ ነፋስም ባሕርም
የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባባሉ።

## አጋንንት ያደረበት ጌርጌሴኖን ሰዉ ማር 5፤ 1-21

## መግቢያ፡ *የዳነ ሰዉ ማገልገል ይችላል*

5:1 ወደ ባሕር ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጡ። 2 ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር
ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው፤ 3 እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ ማንም ሊያስረው በዚያን ጊዜ
አይችልም ነበር፤ 4 ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጥስ እግር
ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤

6 ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሮጦ ሰገደለት፥ 7 በታላቅ ድምፅም እየጮኸ። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥
ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ፤ 8 አንተ ርኩስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ
ብሎት ነበርና።

9 ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። ብዙዎች ነንና ስሜሌጌዎን ነው አለው፥ 10 ከአገርም ውጭ እንዳይሰዳቸው አጥብቆ
ለመነ ው።

11 በዚያም በተራራ ጥግ ብዙ የእሪያ መንጋ ይሰማሩ ነበርና። 12 ወደ እሪያዎቹ እንድንገባ ስደደን ብለው ለመኑት።
13 ኢየሱስም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ገቡ፥ ሁለት ሺህም የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ
ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ። 14 እረኞቹም ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩ፤ ነገሩንም ምን እንደ ሆነ ለማየት
መጡ። 15 ወደ ኢየሱስም መጡ፥ አጋንንትም ያደሩበትን ሌጌዎንም የነበረበትን ሰው ተቀምጦ ለብሶም ልቡም ተመልሶ
አዩና ፈሩ። 16 ያዩት ሰዎችም አጋንንት ላደሩበት ሰው የሆነ ውንና ስለ እሪያዎቹ ተረኩላቸው። 17 ከአገራቸውም
እንዲሄድላቸው ይለምኑት ጀመር።

18 ወደ ታንኳይቱም በገባ ጊዜ አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው ከእርሱ ጋር እንዲኖር ለመነ ው። 19 ኢየሱስም
አልፈቀደለትም፥ ነገር ግን። ወደ ቤትህ በቤተ ሰዎችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ
እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው አለው። 20 ሄዶም ኢየሱስ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት አሥር ከተማ
በሚባል አገር ይሰብክ ጀመር፥ ሁሉም ተደነቁ።

## ኢያኢሮስ ሉቃ 8፡ 40-56

## መግቢያ፡ *ሴትየዋ ወደ ሕብረተሰቧ ተመለሰች፤ የምትቿም ብላቴና ነፍሷ ተመለሰላት*

40 ኢየሱስም በተመለሰ ጊዜ ሁሉ ይጠብቁት ነበርና ሕዝቡ ተቀበሉት። 41 እነሆም፥ ኢያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ፥
እርሱም የምኵራብ አለቃ ነበረ በኢየሱስም እግር ላይ ወድቆ ወደ ቤቱ እንዲገባ ለመነ ው፤ 42 አሥራ ሁለት ዓመት
የሆናት አንዲት ሴት ልጅ ነበረችውና፤ እርስዋም ለሞት ቀርባ ነበረች። ሲሄድም ሕዝቡ ያጨናንቁት ነበር። 43 ከአሥራ
ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ነበረች፥ ትዳርዋንም ሁሉ ለባለመድኃኒቶች ከስራ ማንም ሊፈውሳት
አልተቻለውም፡ 44 በኋላውም ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፥ የደምዋም ፈሳሽ በዚያን ጊዜ ቆመ። 45 ኢየሱስም፦
የዳሰሰኝ ማን ነው? አለ። ሁሉም በካዱ ጊዜ፥ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት። አቤቱ፥ ሕዝቡ ያጨናንቁሃልና
ያጋፉህማል፤ የዳሰሰኝ ማን ነው ትላለህን? አሉ። 46 ኢየሱስ ግን፦ አንድ ሰው ዳሰሶኛል፥ ኃይል ከእኔ እንደ ወጣ
እኔ አውቃለሁና አለ። 47 ሴቲቱም እንዳልተሰወረች ባየች ጊዜ እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች፥ በምን
ምክንያትም እንደ ዳሰሰችው ፈጥናም እንደ ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ ፊት አወራች። 48 እርሱም፦ ልጄ ሆይ፥ እምነትሽ
አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት። 49 እርሱም ገና ሲናገር አንድ ሰው ከምኵራብ አለቃው ቤት መጥቶ። ልጅህ ሞታለች፤

እንግዲህ ማህሩን አታድክም አለ።

[50] ኢየሱስ ግን ሰምቶ። አትፍራ፤ እመን ብቻ ትድንማለች ብሎ ማለሰለት።[51] ወደ ቤትም ሲገባ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ
ከዮሐንስም ከብላቴናይቱም አባትና እናት በቀር ማንም ከእርሱ ጋር ይገባ ዘንድ አልፈቀደም። [52] ሁሉም እያለቀሱላት
ዋይ ዋይ ይሉ ነበር። እርሱ ግን፦ አታልቅሱ፤ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አለ። [53] እንደ ሞተችም አወቀው በጣም
ሳቁበት። [54] እርሱ ግን እጅዋን ይዞ። አንቺ ብላቴና፥ ተነሺ ብሎ ጮኸ። [55] ነፍስዋም ተመለሰች፥ ፈጥናም ቆመች፥
የምትበላውንም እንዲሰጡአት አዘዘ። [56] ወላጆችዋም ተገረሙ፤ እርሱ ግን የሆነውን ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው።

**ደጉ ሳምራዊ** ሉቃ 10፡ 25-37

[25] እነሆም፥ አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው ተነሥቶ፦ መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን
ላድርግ? አለው። [26] እርሱም በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው። [27] እርሱም መልሶ፦
ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥
ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው። [28] ኢየሱስም፦ እውነት መለስህ፤ ይህን አድርግ በሕይወትም
ትኖራለህ አለው። [29] እርሱ ግን ራሱን ሊያጸድቅ ወድዶ ኢየሱስን፦ ባልንጀራዬስ ማን ነው? አለው።

[30] ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዶችም እጅ ወደቀ፤
እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ። [31] ድንገትም አንድ ካህን
በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ። [32] እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጥና
አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። [33] አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ [34] ቀርቦም
ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች
ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም። [35] በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና። ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ
የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው። [36] እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዶች እጅ
ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል? [37] እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ
አንተም እንዲሁ አድርግ አለው።

**እጁ የሰለለ ሰዉ** ማቴ 12፡ 1-14፤ ማር 2፡ 27፤ 3፡ 3-5

[1] በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በእርሻ መካከል አለፈ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተራቡና እሸት ይቀጥፉ ይበሉም ጀመር።
[2] ፈሪሳውያንም አይተው፦ እነሆ፥ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት። [7] ምሕረትን
እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኮነናችሁም ነበር።
ማር 2፡ 27 ደግሞ ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም፤

ማቴ 12፡ 9 ከዚያም አልፎ ወደ ምኩራባቸው ገባ። [10] እነሆም፥ እጁ የሰለለች ሰው ነበረ፤ ይከሱትም ዘንድ፦ በሰንበት
መፈወስ ተፈቅዶአልን? ብለው ጠየቁት። ማር 3፡ 3 እጁ የሰለለችውንም ሰው፦ ተነሥተህ ወደ መካከል ና አለው።
[4] በሰንበት በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን? ወይስ ክፉ? ነፍስ ማዳን ወይስ መግደል? አላቸው፤ እነርሱም ዝም አሉ።

ማቴ 12፡ 11 እርሱ ግን፦ ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበት በጉድጓድ ቢወድቅበት፥ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው?
[12] እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም! ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል አላቸው።
እነርሱም ዝም አሉ። ማር 3፡ 5 ስለ ልባቸውም ድንዛዜ አዝኖ ዙሪያውን እየተመለከተ በቍጣ አያቸው። [13] ከዚያም በኋላ
ሰውየውን እጅህን ዘርጋ አለው። ዘረጋትም፥ እንደ ሁለተኛይቱም ደህና ሆነች። [14] ፈሪሳውያን ግን ወጥተው እንዴት
አድርገው እንዲያጠፉት ተማከሩበት።

**የፈሪሳዊያን ግብዝነት** ማቴ 15፡ 1-20

[1] በዚያን ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን ከኢየሩሳሌም ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፦[2] ደቀ መዛሙርትህ ስለ ምን የሽማግሌዎችን ወግ
ይተላለፋሉ? እንጀራ ሲበሉ እጃቸውን አይታጠቡምና አሉት። [3] እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ እናንተስ ስለ ወጋችሁ
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ምን ትተላለፋላችሁ? [4] እግዚአብሔር፦ አባትህንና እናትህን አክብር፤ ደግሞ፦ አባቱን
ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና፤ [5] እናንተ ግን፦ አባቱን ወይም እናቱን ከእኔ የምትጠቀምበት መባ ነው

የሚሉ ሁሉ፥ [6] አባቱን ወይም እናቱን አያከብርም ትላላችሁ፤ ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ።

[7] እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ፡- [8] ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤
9 የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ። [10] ሕዝቡንም
ጠርቶ፡- ስሙአስተውሉም፤ [11] ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን
የሚያረክሰው ይህ ነው አላቸው።

[12] በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፣ [15] ጴጥሮስም መልሶ፡- ምሳሌውን ተርጉምልን አለው።

[16] ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- እናንተ ደግሞ እስካሁን የማታስተውሉ ናችሁን? [17] ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ አልፎ
ወደ እዳሪ እንዲጣል አትመለከቱምን? [18] ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው። [19] ከልብ
ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በሐሰት መመስከር፥ ስድብ ይወጣሉና። [20] ሰውን የሚያረክሰው
ይህ ነው እንጂ፥ ባልታጠበ እጅ መብላትስ ሰውን አያረክሰውም።

## **ኒቆድሞስ** ዮሐ 3

## ***መግቢያ፡*** *ኢየሱስ የፈርሳዊያንን አስተሳሰብ መቀየር ጀመረ*

3፡ 1 ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ
መጥቶ። [2] መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነ ዚህን ምልክቶች ሊያደርግ
የሚችል የለምና መምህር ሆነ ህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው። [3] ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት
እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።
[4] ኒቆዲሞስም፡- ሰው ከሸመገ ለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገ ብቶ ይወለድ ዘንድ
ይችላልን? አለው።

[5] ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ሊገ ባ አይችልም። [6] ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነ ው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነ ው። [7] ዳግመኛ
ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ። [8] ነ ፋስ ወደሚወደው ይነ ፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነ ገ ር ግን
ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነ ው።

[9] ኒቆዲሞስ መልሶ፡- ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው። [10] ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- አንተ የእስራኤል
መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? [12] ስለ ምድራዊ ነ ገ ር በነ ገ ርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነ ገ ር
ብነ ግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?

[16] በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ
ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። [17] ዓለም በልጁ እንዲድን ነ ው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም
አልላከውምና።

## **ኢየሱስ በውሃ ጉድጓድ አጠገ ብ ያገ ኛት ሴት** ዮሐ 4፡ 3-42

## ***መግቢያ፡*** *የሰማሪያ ሰዎች በኢስራኤል አገ ር በአይሁዶች መካከል ብኖሩም ከእነ ርሱ ጋር ግኑኝነ ት ኣልነ በራቸውም ፡*

[3] ይሁዳን ትቶ ወደ ገ ሊላ ደግሞ ሄደ፤ [4] በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነ በት። [6] በዚያም የያዕቆብ ጉድጓድ ነ በረ።
ኢየሱስም መንገ ድ ከመሄድ ደክሞ በጉድጓድ አጠገ ብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነ በረ።
[7] ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፡- ውኃ አጠጪኝ አላት፤ [9] ስለዚህ ሳምራዊቲቱ። አንተ የይሁዳ
ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ ማጠጣ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር
አይተባበሩም ነ በርና።

[10] ኢየሱስ መልሶ፡- የእግዚአብሔርን ስጦታና። ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ትለምኚው ነ በርሽ

የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት። 11 ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ መቅጃ የለህም ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይወት
ውኃ ከወዴት ታገኛለህ? 12 በእውኑ አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ራሱም ልጆቹም
ከብቶቹም ከዚህ ጠጥተዋል አለችው።

13 ኢየሱስም መለሰ፡- ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤ 14 እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም
አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ወስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።
15 ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ እንዳልጠማ ወኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ አለችው።

16 ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት። 17 ሴቲቱ መለሳ። ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፡- ባል
የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ 18 አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤
በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።

19 ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። 20 አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም። ሰው
ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው። 21 ኢየሱስም እንዲህ አላት፡- አንቺ ሴት፥
እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። 23 ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ
ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነ ዚህ ያሉትን
ይሻልና፤ 24 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።

25 ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አወቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው። 26 ኢየሱስ፡-
የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት። 27 በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ማጡና ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ፤ ነገር ግን።
ምን ትፈልጊያለሽ? ወይም። ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም። 28 ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ
ሄደች ለሰዎችም። 29 ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰውኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች። 30 ከከተማ
ወጥተው ወደ እርሱ ይማጡነበር። 39 ሴቲቱም። ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ ማከረችው ቃል ከዚያች ከተማ
የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት።

40 የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በማጡ ጊዜ በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ። 41 ስለ
ቃሉ ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች አመኑ፤ 42 ሴቲቱንም። አሁን የምናምን ስለ ቃልሽ አይደለም፥ እኛ ራሳችን
ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ ሆነ እናወቃለን ይሉአት ነበር።

## አንተ ክርስቶስ ነህ ማቴ16፡ 13-28

13 ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?
ብሎ ጠየቀ። 14 እርሱም፦ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው
ይላሉ አሉት። 15 እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። 16 ስምዖን ጴጥሮስም መለሰ፡- አንተ
ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።

17 ኢየሱስም መለሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማየት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን
አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። 18 እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን
እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። 19 የመንግሥተ ሰማየትንም መከፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው
ሁሉ በሰማየት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማየት የተፈታ ይሆናል። 20 ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ
እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው። 21 ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ
ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ
እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። 22 ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ
አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ። 23 እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን
እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።

24 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም
ተሸክሞ ይከተለኝ። 25 ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፉታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፉ ሁሉ ያገኛታል።
26 ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?

## አልዓዛርና ባለ ጠጋዉ ሰዉ አሉቃ 16፡ 13-31

## መግቢያ፡ *ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ገንዘብን ለሚወዱ ሰዎች ተናገረ*

[13] ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፥ ወይም ወደ
አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። [14] ገንዘብንም የሚወዱ
ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር። [15] እንዲህም አላቸው፦ ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ
ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና። [19] ቀይ
ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር።
[20] አልዓዛርም የሚባል አንድ ደሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ [21] ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ
ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።
[22] ደሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋውም ደግሞ ሞተና ተቀበረ። [23] በሲኦልም በሥቃይ
ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። [23] በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ
አልዓዛርንም በእቅፉ። [24] እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን
ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።

[25] አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤
አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። [26] ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ
እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።
[27] እርሱም፦ እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤
[28] እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።

[29] አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙአቸው አለው። [30] እርሱም፦ አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥
ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። [31] ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ፥ ከሙታንም እንኳ
አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።

## ፈሪሳዊውና ቀራጩ ሰዉ ሉቃ 18፡ 9-14

[9] ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፥ [10] እንዲህ ሲል፦
ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ። [11] ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ።
እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ
አመሰግንሃለሁ፤ [12] በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።

[13] ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን
ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር።

[14] እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን
የሚያዋርድ ከፍ ይላል።

## ሀብታሙ ወጣት ገዥ ማር 10፡ 17-31

[17] እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና። ቸር መምህር ሆይ፥ የዘላለም ሕይወትን
እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው።

[18] ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም። [19] ትእዛዛትን ታውቃለህ፤
አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አታታልል፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው።

[20] እርሱም መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለው። [21] ኢየሱስም ወደ እርሱ ተመልክቶ
ወደደውና። አንድ ነገር ጎደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መስቀሉንም
ተሸክመህ ና፥ ተከተለኝ አለው። [22] ነገር ግን ስለዚህ ነገር ፊቱ ጠቈረ፥ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ምሄደ።

[23] ኢየሱስም ዘወር ብሎ አይቶ ደቀ መዛሙርቱን። ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ

ይሆናል አላቸው። [24] ደቀ መዛሙርቱም እነ ዚህን ቃሎች አደነ ቁ። ኢየ ሱስም ደግሞ መልሶ፦ ልጆች ሆይ፥ በገ ንዘብ
ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነ ው። [25] ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገ ባ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል አላቸው። [26] እነ ርሱም ያለ ማጠን ተገ ረሙና እርስ በርሳቸው። እንግዲያ ማን
ሊድን ይችላል? ተባባሉ።

[27] ኢየ ሱስም ተመለከታቸውና። ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ
ይቻላልና አለ። [28] ጴጥሮስም፦ እነ ሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ይለው ጀመር።

[29] ኢየ ሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ እውነ ት እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም
እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የ ተወ፥ [30] አሁን በዚህ ዘመን
ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም
የ ዘላለም ሕይወት የ ማይቀበል ማንም የ ለም። [31] ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።

## አባከኙ ልጅ ሉቃ 15፡ 11-32

[11] እንዲህም አለ፦ አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነ በሩት። [12] ከእነ ርሱም ታናሹ አባቱን፦ አባቴ ሆይ፥ ከገ ንዘብህ
የ ሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገ ንዘቡንም አካፈላቸው። [13] ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገ ንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ
ወደ ሩቅ አገ ር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገ ዘቡን በተነ ። [14] ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገ ር ጽኑ ራብ ሆነ ፥
እርሱም ይጨነ ቅ ጀመር። [15] ሄዶም ከዚያች አገ ር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ፥ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ
ሰደደው። [16] እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነ በር፥ የ ሚሰጠውም አልነ በረም።

[17] ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፦ እንጀራ የ ሚተርፋቸው የ አባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ
እጠፋለሁ። [18] ተነ ሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁ። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ [19] ወደ ፊትም ልጅህ ልባል
አይገ ባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገ ኝ እለዋለሁ። [20] ተነ ሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገ ና ሩቅ ሳለ
አባቱ አየ ውና አዘነ ለት፥ ሮጦም አንገ ቱን አቀፈውና ሳመው።

[21] ልጁም፦ አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገ ባኝም አለው። [22] አባቱ ግን
ባሪያዎቹን አለ፦ ፈጥናችሁ ከሁሉ የ ተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ [23] የ ሰባውን
ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤ [24] ይህ ልጄ ሞቶ ነ በርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም
ነ በር ተገ ኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር። [25] ታላቁ ልጁ በእርሻ ነ በረ፤ መጥቶም ወደ ቤት በቀረበ ጊዜ የ ማኅንቆና
የ ዘፈን ድምፅ ሰማ፤ [26] ከብላቴናዎችም አንዱን ጠርቶ፦ ይህ ምንድር ነ ው? ብሎ ጠየ ቀ። [27] እርሱም፦ ወንድምህ
መጥቶአልና በደኅና ስላገ ኘው አባትህ የ ሰባውን ፊሪዳ አረደለት አለው።

[28] ተቈጣም ሊገ ባም አልወደደም፤ አባቱም ወጥቶ ለመነ ው። [29] እርሱ ግን መልሶ አባቱን። እነ ሆ፥ ይህን ያህል ዓመት
እንደ ባሪያ ተገ ዝቼልሃለሁ ከትእዛዝህም ከቶ አልተላለፍሁም፤ ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት
ስንኳ አልሰጠኸኝም፤ [30] ነ ገ ር ግን ገ ንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ፥ የ ሰባውን ፊሪዳ
አረድህለት አለው። [31] እርሱ ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነ ህ፥ ለእኔም የ ሆነ ሁሉ የ አንተ ነ ው፤
[32] ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነ በረ ሕያው ስለ ሆነ ጠፍቶም ነ በር ስለ ተገ ኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ
ይገ ባናል አለው።

## ይቅርታ ማድረግ ማቴ 18፡ 15-35

## መግቢያ፡ *ኢየ ሱስ ደቀመዛሙርቶቹን ስለ ይቅርታ ማድረግ አስተማራቸዉ*

[15] ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ወቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገ ንዘብ
አደረግኸው፤ [16] ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነ ገ ር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም
ሁለት ከአንተ ጋር ወሰድ፤ [17] እነ ርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገ ራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን
ባይሰማት፥ እንደ አረማዊና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።
[21] በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን?
አለው። [22] ኢየ ሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም። [23] ስለዚህ መንግሥተ
ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የ ወደደን ንጉሥ ትመስላለች። [24] መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን

አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። [25] የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው
እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።[26] ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና። ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው።
[27] የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት።

[28] ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ
ያዘና አነቀው። [29] ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ። ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። [30] እርሱም
አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። [31] ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው
እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ።

[32] ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ። አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤ [33] እኔ እንደ ማርሁህ
ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው። [34] ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ
እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው። [35] ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ
ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።

## ዘኬዎስ ሉቃ 19፡ 1-11

## መግቢያ፡ *ሰዉ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ሲመጣ ወደ ሕዝቡ ይመለሳል*

19፡ 1-2 ወደ ኢያሪኮም ገብቶ ያልፍ ነበር። እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው፥ እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ፥ ባለ ጠጋም
ነበረ። [3] ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው።
[4] በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ።

[5] ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና። ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ
ወረድ አለው። [6] ፈጥኖም ወረደ በደስታም ተቀበለው። [7] ሁሉም አይተው። ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው
አንጐራጐሩ።

[8] ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን። ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ
አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው። [9] ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፤
[10] የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።

## በርጠሜዎስ ማር 10፡ 46-52

## መግቢያ፡ *ይህ ታሪክ የተደረገዉ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄድ ላይ እያለ በምድር ሕይወቱ ሚጨረሻ አከባቢ ላይ ነዉ*

[46] ወደ ኢያሪኮም መጡ። ከደቀ መዛሙርቱና ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጣ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ በርጠሜዎስ
እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር። [47] የናዝሬቱ ኢየሱስም እንደ ሆነ በሰማ ጊዜ። የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥
ማረኝ እያለ ይጮኽ ጀመር። [48] ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን፦ የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረኝ እያለ አብዝቶ
ጮኸ።

[49] ኢየሱስም ቆመና። ጥሩት አለ። ዕውሩንም። አይዞህ፥ ተነሣ፥ ይጠራሃል ብለው ጠሩት። [50] እርሱም እየዘለለ ተነሣና
ልብሱን ጥሎ ወደ ኢየሱስ መጣ።

[51] ኢየሱስም መልሶ፦ ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? አለው። ዕውሩም። መምህር ሆይ፥ አይ ዘንድ አለው። [52] ኢየሱስም፦
ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። ወዲያውም አየ በመንገድም ተከተለው።

## በክብር መግባት ሉቃ 19፡ 29-40፤ 45-48 / ዮሐ 12፡ 15

29 ደብረ ዘይትም በሚባል ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ፥ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን
ላከና። 30 በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ ወደ እርስዋም ገብታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ ታስሮ
ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁም አምጡት። 31 ማንም ስለ ምን ትፈቱታላችሁ? ብሎ ቢጠይቃችሁ፥ እንዲሁ፦ ለጌታ ያስፈልገዋል
በሉ አላቸው። 32 የተላኩትም ሄደው እንዳላቸው አገኙ። 33 እነርሱም ውርንጫውን ሲፈቱ ጌቶቹ። ውርንጫውን ስለ ምን
ትፈቱታላችሁ? አሉአቸውም ፡ 34 እርሱም፦ ለጌታ ያስፈልገዋል አሉ። ሚር 11:6 እነርሱም ኢየሱስ እንዳዘዘ አሉአቸው፤
ተወአቸውም።

35 ወደ ኢየሱስም አመጡት፥ በውርንጫውም ላይ ልብሳቸውን ጫኑ ውኢየሱስን አስቀመጡት። 36 ሲሄድም ልብሳቸውን
በመንገድ ያነጥፉ ነበር። 37 ወደ ደብረ ዘይት ቁልቁለትም አሁን በቀረበ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ሁላቸው ደስ እያላቸው
ተአምራትን ሁሉ ስላዩ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ጀምረው። 38 በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ
ነው፤ በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር አሉ።

ዮሐ 12:14-15 አንቺ የጽዮን ልጅ አትፍሪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ይመጣል ተብሎ እንደ ተጻፈ፥
ኢየሱስ የአህያ ውርንጫ አግኝቶ በእርሱ ተቀመጠ።

39 ከሕዝብም መካከል ከፈሪሳውያን አንዳንዱ። መምህር ሆይ፥ ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው አሉት።
40 መልሶም። እላችኋለሁ፥ እነ ዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው።
45 ወደ መቅደስም ገብቶ በእርሱ የሚሸጡትን የሚገዙትንም ያወጣ ጀመር፤ 46 እርሱም፦ ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ
ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው።

47 ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች የሕዝቡ ታላላቆችም ሊገድሉት
ይፈልጉ ነበር፥ 48 የሚያደርጉበትንም አጡ፤ ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙት ተንጠልጥለውበት ነበርና።

## ማሪያም ኢየሱስን ቀባች ዮሐ 12/ ማቴ 26፡ 13

## *መግቢያ፡ ኢየሱስ የማርያምና የማርታ ቤተሰብ ወዳጅ ነበር ወንድማቸዉ ዓልአዘርንም ከሞት አስነስቶት ነበር*

1 ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። 2 በዚያም
እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ። 3 ማርያምም
ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም
ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።

4 ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ። 5 ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ
ዲናር ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ። 6 ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች
ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በወስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው። 7 ኢየሱስም፦ ለምቀበርበት ቀን
እንድትጠብቀው ተወአት፤ 8 ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም
አለ። ማቴ 26፡ 13 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት ስፍራ በሚከበክበት እርስዋ ያደረገችው
ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።

## የጌታ እራት ማቴ 26፡ 14፡ 1-35 ዮሐ 14፡ 1-6፤ 15፤ 12

## መግቢያ፡

14 በዚያን ጊዜ የአስቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ። 15 ምን ልትሰጡኝ
ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ? እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት። 16 ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ አሳልፎ ሊሰጠው
ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር።

17 በቂጣው በዓል በመጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው። ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ
ትወዳለህ አሉት። 21 ሲበሉም። እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል አለ። 22 እጅግም አዝነው
እያንዳንዱ። ጌታ ሆይ፥ እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር። 23 እርሱም መልሶ፦ ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ያጠለቀ፥ እኔን

አሳልፎ የሚሰጥ እርሱ ነው። [24] የሰውልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፥ ነገር ግን የሰውልጅ አልፎ
ለሚሰጥበት ለዚያ ሰውወዮለት፤ ያ ሰውባልተወለደ ይሻለውነበር አለ። [25] አሳልፎ የሚሰጠውይሁዳም መልሶ፡-
መምህር ሆይ፥ እኔ እሆንን? አለ፤ አንተ አልህ አለው።

[26] ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነውአለ።
[27] ጽዋንምአንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸውእንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፥ [28] ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ
የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜይህ ነው።

[ዮሐ 14፡ 1] ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞእመኑ። [2] በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ
ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ [3] ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት
እናንተ ደግሞእንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። [4] ወደምሄደበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም
ታውቃላችሁ። [5] ቶማስም፡ ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄደበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው።
[6] ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትምነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣየለም። [15፡ 12] እኔ እንደ
ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።

[30] መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ። [31] በዚያን ጊዜ ኢየሱስ፡- በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ
ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፎአልና፤

[33] ጴጥሮስም መልሶ፡- ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም አለው። [34] ኢየሱስ፡- እውነት እልሃለሁ፥ በዚች
ሌሊት ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው። [35] ጴጥሮስ፡- ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፥ ከቶ
አልክድህም አለው። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደግሞእንደዚሁ አሉ።

## የኢየሱስ መያዝና መከሰስ ሉቃ 22፡ 40-71

[40] ወደ ስፍራውም ደርሶ። ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው። [41] ከእነርሱም የድንጋይ ወርወራ የሚያህል ራቀ፥
ተንበርክኮም፡ አባት ሆይ፥ [42] ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ወስድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ
እያለ ይጸልይ ነበር። [43] ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው። [44] በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤
ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደምነ ጠብጣብ ነበረ።

[45] ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥና ከኀዘን የተነሣ ተኝተውሲያገኛቸው። [46] ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ
ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው። [47] ገናም ሲናገር እነሆ፥ ሰዎች መጡ፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ
የሚባለውይቀድማቸውነበር፥ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ። [48] ኢየሱስ ግን፡- ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ
አሳልፈህ ትሰጠዋለህን? አለው።

[49] በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት። [50] ከእነርሱም አንዱ የሊቀ
ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው። [51] ኢየሱስ ግን መልሶ፡- ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው።

[52] ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም፡ ወንበዴን እንደምትይዙ
ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ወጣችሁን? [53] በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ስሆን እጃችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ
ግን ጊዜያችሁና የጨለማውሥልጣን ነውአላቸው። [54] ይዘውም ወሰዱት ወደ ሊቀ ካህናት ቤትም አገቡት፤ ጴጥሮስም ርቆ
ይከተለውነበር። [55] በግቢ መካከልም እሳት አንድደውበአንድነት ተቀምጠውሳሉ ጴጥሮስ በመካከላቸውተቀመጠ።
[56] በብርሃኑም በኩል ተቀምጦ ሳለ አንዲት ገረድ አየችውና ትኵር ብላ። ይህ ደግሞከእርሱ ጋር ነበረ አለች።
[57] እርሱ ግን፡- አንቺ ሴት፥ አላውቀውም ብሎ ካደ። [58] ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሌላውአይቶት። አንተ ደግሞከእነርሱ
ወገን ነህ አለው። ጴጥሮስ ግን። አንተ ሰው፥ እኔ አይደለሁም አለ።

[59] አንድ ሰዓትምየሚያህል ቆይቶ ሌላውአስረግጦ። እርሱ የገሊላ ሰውነውና በእውነት ይህ ደግሞከእርሱ ጋር ነበረ
አለ። [60] ጴጥሮስ ግን። አንተ ሰው፥ የምትለውን አላውቅም አለ። ያን ጊዜም ገና ሲናገር ዶሮ ጮኸ። [61] ጌታም ዘወር
ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው፤ ጴጥሮስም፦ ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ እንዳለውየጌታ ቃል ትዝ አለው።
[62] ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።

[66] በነጋም ጊዜ የሕዝቡ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች ጻፎችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸውወሰዱትና [67] ክርስቶስ

አንተ ነህን? ንገረን አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፦ ብነግራችሁ አታምኑም፤ 71 እርሱም፦ ራሳችን ከአፉ
ሰምተናልና ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር ያስፈልገናል? አሉ።

## **የኢየሱስ ማቀል** ሉቃ 23/ ዮሐ 18 ፣ 19

## **መግቢያ፡** *አይሁዶች ኢየሱስን በመቃን ን ልሰቅሉት ከሮማማንግስት ፈቃድን ጠየቁ*

1 ሁሉም በሞላ ውተነሥተው ወደ ጲላጦስ ወሰዱትና። 2 ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣር ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል
ደግሞ፦ እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር።

ዮሐ 18፡ 33 ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ገዥ ግቢ ገባና ኢየሱስን ጠርቶ። የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? አለው።
36 ኢየሱስም መለሰ፡- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ
ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው። 37 ጲላጦስም፦ እንግዲያ ንጉሥ ነህን?
አለው። ኢየሱስም መለሰ፡- እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ
ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። 38 ጲላጦስ። እውነት ምንድር ነው?
አለው። ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ። እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም።

ሉቃ 23፡ 21 ነገር ግን እነርሱ። ስቀለው ስቀለው እያሉ ይጮኹ ነበር። 22 ሦስተኛም፦ ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር
ነው? ለሞት የሚያደርሰው በደል አላገኘሁበትም፤ ስለዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ አላቸው። 23 እነርሱ ግን እንዲሰቀል
በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት። የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ። 24 ጲላጦስም ልመናቸው
እንዲሆንላቸው ፈረደበት።

26 በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም
ጫኑበት። 32 ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። 33 ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ
በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። 34 ኢየሱስም፦ አባት
ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት። 35 ሕዝቡም ቆመው
ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ፦ ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን
ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር። 36 ጭፍሮችም ደግሞ ወደ እርሱ ቀርበው ሆምጣጤም አምጥተው። 37 አንተስ የአሁድ ንጉሥ
ከሆንህ፥ ራስህን አድን እያሉ ይዘብቱበት ነበር። 38 ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ
በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ። 39 ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ። አንተስ
ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው። 40 ሁለተኛው ግን መለሰ፡- አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ
ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? 41 ስለ አደረግነው ምየሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ
ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሠጸው። 42 ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ
አለው። 43 ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።

44 ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፥ ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ፥ ፀሐይም ጨለመ። 45 የቤተ
መቅደስም መጋረጃ ከመካከሉ ተቀደደ። 46 ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ
እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።

50 እነሆም፥ በጎና ጻድቅ ሰው የሸንጎ አማካሪም የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበረ፤ 51 ይህም በምክራቸውና በሥራቸው
አልተባበረም ነበር፤ አርማትያስም ከምትባል ከአይሁድ ከተማ ሆኖ እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠብበቅ
ነበር። 52 ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነ ው፤ 53 አወርዶም በተልባ እግር ልብስ ከፈነው፥ ማንም
ገና ባልተቀበረበት ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው።
ዮሐ 19፡ 39 ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት
ቅልቅል ይዞ መጣ።
55 ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንደ ዴት እንዳኖሩት አዩ። 56 ተመልሰውም
ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ።

## **ትንሳኤ** ሉቃ 24/ ማቴ 28/ የሐዋ 1

## ***መግቢያ፡*** *ይህ ታሪክ በታሪክ ዉስጥ የመጀመሪያ ነዉ*

[1] ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያውቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘውከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ
ማልደውመጡ፡ [4] እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፥ እነሆ፥ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰውወደ እነርሱ ቀረቡ፤
[5] ፈርተወም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረውሳሉ፥ እንዲህ አሉአቸው። ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን
ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም፡ [8-9] ቃሎቹንም አሰቡ፥ ከመቃብሩም ተመልሰውይህን ሁሉ ለአሥራ
አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው። [11] ይህም ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም። [12] ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ
መቃብር ሮጠ፤ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር ልብስን ብቻ አየ፤ በሆነ ወም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ
ሄደ። [13] እነሆም፥ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያ ቀን ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር
ይሄዱ ነበር፤ [15] ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤ [16] ነገር ግን እንዳያወቁት
ዓይናቸውተይዞ ነበር። [17] እርሱም፦ እየ ጠወለጋችሁ ስትሄዱ፥ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸውእነ ዚህ ነገሮች
ምንድር ናቸው? አላቸው። [18] ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ፦ አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነ ህ ለብቻህ ትኖራለህን?
በእነ ዚህ ቀኖች በዚያ የሆነ ውን ነገር አታውቅምን? አለው። [19] እርሱም፦ ይህ ምንድር ነ ው? አላቸው። እነርሱም
እንዲህ አሉት። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነ ቢይ ስለ ነ በረውስለ ናዝሬቱ ስለ
ኢየሱስ፤ [20] እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈውእንደ ሰጡትና እንደ
ሰቀሉት ነ ው።[22] ደግሞም ከእኛ ወስጥ ማልደውከመቃብሩ ዘንድ የነ በሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ [23] ሥጋወንም
ባጡጊዜ። ሕያውነ ውየሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞአየን ሲሉ መጥተውነ በር።[27] ከሙሴና ከነ ቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ
እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።
[28] ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው። [29] እነርሱ። ከእኛ ጋር እደር፥ ሚታ ቀርቦአልና
ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለውግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ። [30] ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ
እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤ [31] ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ።
[32] እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነ በረምን? ተባባሉ። [33-
34] በዚያችም ሰዓት ተነሥተውወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ አሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነ በሩትም። ጌታ በእውነ ት
ተነሥቶአል ለስምዖንም ታይቶአል እያሉ በአንድነ ት ተሰብስበውአገኙአቸው። [35] እነርሱም በመንገድ የሆነ ውን
እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸውተረከላቸው።

[36] ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸውቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። [37] ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ
መንፈስም ያዩ መሰላቸው። [38] እርሱም፦ ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? [39] እኔ ራሴ
እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ
አላቸው።
[44] እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነ ቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈውሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል
ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነ ውአላቸው። [45] በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤
[46] እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ [47] በስሙም ንስሐና የኃጢአት
ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎእንዲሁ ተጽፎአል። ማቴ 28፡ 19 እንግዲህ ሂዱና
አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ
እያስተማራችኋቸውደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ሉቃ 24፡ 49 እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤
እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ። የሐዋ ስራ 1፡ 3,8 ደግሞ አርባ ቀን እየ ታያቸው
ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያውሆኖ ለእነርሱ
ራሱን አሳያቸው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥
በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

ሉቃ 24፡ 51 ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ። እነርሱም፤ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም
ተመለሱ፥ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ።

## **በዓለ ኀምሳ** የሐዋ ስራ 2

## ***መግቢያ፡*** *ቤተክርስቲያን የተመሠረተችዉ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከዐረገ ከ 50 ቀን በኋላ ነዉ*

[1] በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነ ውአብረውሳሉ፥ [2] ድንገት እንደሚ ጥቅ ዓወሎ
ነ ፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠውየነ በሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። [3] እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤

በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጠባቸው። 4 በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው
በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። 5 ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤
6 ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማስለ ነበር የሚሉትን
አጡ፥ 7 ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ። እነ ሆ፥ እነ ዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? 8 እኛም
እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? 12 ሁሉም ተገረሙ አመነትተውእርስ
በርሳቸው። እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ። 13 ሌሎች ግን እያፌዙባቸው። ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።

14 ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆሞ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው። አይሁድ
በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ። 15 ለእናንተ እንደ
ሚመስላችሁ እነ ዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነ ውና፤ 16 ነገር ግን ይህ በነ ቢዩ በኢዩኤል የተባለው
ነ ው። 17 እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤
21 የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።
22 የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ
በእርሱ በኩል ባደረገ ውተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰውነ በረ፤
23 እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነ ውአሳቡና በቀደመውእውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ
ገደላችሁት። 24 እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነ ሣው፥ ሞት ይይዘውዘንድ አልቻለምና። 36 አለ።
እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገ ውየእስራኤል ወገን
ሁሉ በእርግጥ ይወቅ። 37 ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸውተነ ካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን
እናድርግ? አሉአቸው። 38 ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። 41 ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ
የሚያህል ነ ፍስ ተጨመሩ፤

42 በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነ በር። 43 ነ ገር ግን በሰውሁሉ
ፍርሀት ሆነ ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ ። 44 ያመኑትም ሁሉ አብረውነ በሩ፤ 45 ያላቸውንም ሁሉ
አንድነ ት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነ በር።
46 በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነ ውበመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን
ይመገቡ ነ በር፤ 47 እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነ በራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት
በእነ ርሱ ላይ ይጨምር ነ በር።

## ሽባው በመቅደስ ደጅ የተደረገ ፈውስ የሐዋ ሥራ 3

1 ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡነ በር። 2 ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምጽዋት
ይለምን ዘንድ፥ ሰዎች ተሸክመውሽባም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት የነ በሩ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ
አንካሳ የሆነ አንድ ሰውነ በረ። 3 እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ እንዳላቸውባየ ጊዜ፥ ምጽዋትን
ለመናቸው። 4 ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኩር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ። ወደ እኛ ተመልከት አለው። 5 እርሱም አንድ
ነ ገር ከእነ ርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነ ርሱ ተመለከተ።
6 ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነ ሣና
ተመላለስ አለው። 7 በቀኝ እጁም ይዞ አስነ ሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭሚቱ ጸና፥ 8 ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥
ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነ ርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።
9 ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፤ 10 ሽባውም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለ ምጽዋት
ተቀምጦ የነ በረውእርሱ እንደ ሆነ አወቁት፤ በእርሱም ከሆነ ውየተነ ሣ መደነ ቅና መገረም ሞላባቸው። 11 እርሱም
ጴጥሮስንና ዮሐንስን ይዞ ሳለ፥ ሕዝቡ ሁሉ እየተደነ ቁ የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በሚባለውአብረውወደ እነ ርሱ ሮጡ።
12 ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ። የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ በዚህ ስለ ምን ትደነ ቃላችሁ? ወይስ በገዛ
ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነ ውስለ ምን ትኩር ብላችሁ
ታዩናላችሁ? 13 የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ
የሰጣችሁትንና ሊፈታውቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። 14 እናንተ ግን
ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነ ፍሰ ገዳዩን ሰውይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥ 15 የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን
ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነ ሣው፥ ለዚህም ነ ገር እኛ ምስክሮች ነ ን። 16 በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና
የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነ ውእምነ ት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው።

17 አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤ 19-20 እንግዲህ
ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የሚጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥
ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። 24 ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት
ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ። 25 እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም። በዘርህ የምድር ወገኖች
ሁሉ ይባረካሉ ብሎ፥ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ።

## ጴጥሮስና ዮሐንስ በክስ ላይ የሐዋ ሥራ 4

1 ለሕዝቡም ሲናገሩ የካህናት አለቆችና የመቅደስ አዛዥ ሰዱቃውያንም፥ 2 ሕዝቡን ስለ አስተማሩና በኢየሱስ
የሙታንን ትንሣኤ ስለ ሰበኩ ተቸግረው፥ ወደ እነርሱ ቀረቡ፥ 3 እጃቸውንም ጫኑ ወባቸው አሁን መሸቶ ነበርና እስከ
ማግሥቱ ድረስ በወኅኒ አኖሩአቸው። 4 ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥ የወንዶችም ቁጥር አምስት ሺህ ያህል
ሆነ ።
5-6 በነገውም አለቆቻቸውና ሽማግሌዎች ጻፎችም ሊቀ ካህናቱ ሐናም ቀያፋም ዮሐንስም እስክንድሮስም የሊቀ ካህናቱም
ዘመዶች የነበሩት ሁሉ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ፤ 8 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፦
እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች፥ 9 እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰውስለ ተደረገው መልካም ሥራ ይህ በምን እንደዳነ
ብንመረመር፥ 10 እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደኅና
ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን ። 11 እናንተ ግንበኞች
የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ የሆነ ውይህ ድንጋይ ነው። 12 መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን
ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና ።
13 ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው
አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤ 14 የተፈወሰውንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ሲያዩ የሚቃወሙትን
አጡ፡ 14 የተፈወሰውንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ሲያዩ የሚቃወሙትን አጡ፡ 18 ጠርተውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው
እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው። 19 ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መለሰው። እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ
እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቀኺጡ፤ 20 እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር
ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው። 21 እነርሱም እንደ ምን እንደሚቀጡምክንያት ስላላገኙባቸው፥ እንደ ገና ዝተው
ከሕዝቡ የተነሣ ፈቱአቸው፤ ሰዎች ሁሉ ስለ ሆነ ውነገር እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበርና ። 22 ይህ የሚፈወስ ምልክት
የተደረገለት ሰው ከአርባ ዓመት ይበልጠው ነበርና ። 33 ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ
ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው።

## ሐናንያና ሰጲራ የሐዋ 5፤ 1-12

1 ሐናንያም የተባለ አንድ ሰው ሰጲራ ከተባለች ከሚስቱ ጋር መሬት ሸጡ፥ 2 ሚስቱም ደግሞ ስታውቅ ከሽያጩ አስቀረና
እኩሌታውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው። 3 ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና
ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? 4 ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ
በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው።
5 ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወድቆ ሞተም፤ በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ ። 6 ጕበዞችም ተነሥተው ከፈኑት
አውጥተውም ቀበሩት።
7 ከሦስት ሰዓት ያህል በኋላም ሚስቱ የሆነ ውን ሳታውቅ ገባች። 8 ጴጥሮስም መለሰ፦ እስቲ ንገሪኝ፥ መሬታችሁን
ይህን ለሚያህል ሸጣችሁትን? አላት። እርስዋም፦ አዎን፥ ይህን ለሚያህል ነው አለች። 9 ጴጥሮስም፦ የጌታን መንፈስ
ትፈታተኑ ዘንድ ስለ ምን ተስማማችሁ? እነሆ፥ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው አንቺንም ያወጡሻል አላት።
10 ያን ጊዜም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ሞተችም፤ ጕበዞችም ሲገቡ ሞታ አገኙአት አውጥተውም በባልዋ አጠገብ
ቀበሩአት።
11 በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ ። 12 በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ
በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር፤ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነ ው በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ነበሩ።

## እስጢፋኖስ የሐዋ ስራ 6፡ 8-15/7፡ 1-60

***መግቢያ፡ በዚህ ታሪክ ዉስጥ አባቶች የተባሉት የቀደመ የኢይዱ አባቶች በተለይም የያዕቆብ ልጆች ናቸው፡ ፡***

8 እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር። 11 በዚያን ጊዜ።
በሜሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሡ። 12 ሕዝቡንና
ሽማግሌዎችንም ጻፎችንም አናደዱ፥ ቀርበውም ያዙት ወደ ሸንጎም አመጡትና። 13 ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ
በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም፤ 14 ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ ያፈርሰዋል ሜሴም
ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋልና የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አቆሙ። 15 በሸንጎም የተቀመጡት ሁሉ
ትኵር ብለው ሲመለከቱት እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት።

2 እርሱም እንዲህ አለ፦ ወንድሞችና አባቶች ሆይ፥ ስሙ። የክብር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም በካራን ሳይቀመጥ
ገና በሁለት ወንዝ መካከል ሳለ ታየና። 3 **ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደማሳይህ ወደ ማንኛውም ምድር ና
አለው።** አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ያዕቆብም አሥሬ ሁለቱን የአባቶችን አለቆች። 9 የአባቶችም
አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፥ 10 ከመከራውም ሁሉ አወጣው፥ በግብፅ
ንጉሥ በፈርዖንም ፊት ሞገስንና ጥበብን ሰጠው፥ በግብፅና በቤቱ ሁሉ ላይም ቢትወደድ አድርጎ ሾመው።

11 በግብፅና በከነዓንም አገር ሁሉ ራብና ብዙ ጭንቅ መጣ፥ 15 ያዕቆብም ወደ ግብፅ ወረደ 18 ዮሴፍን የማያውቀው ሌላ
ንጉሥ በግብፅ ላይ ተነሳ፡፡ 19 እርሱም ወገናችንን ተተንኰሎ ሕፃናትን በሕይወት እንዳይጠበቁ ወደ ውጭ ይጥሉ ዘንድ
አድርጎ አባቶቻችንን አስጨነቀ። 20 በዚያን ጊዜ ሜሴ ተወለደ በእግዚአብሔርም ፊት ያማረ ነበር፤ በአባቱ ቤትም
ሦስት ወር አደገ፤ 29 ሜሴም ከዚህ ነገር የተነሣ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ኖረ፡፡

30 አርባ ዓመትም ሲሞላ **የጌታ መልአክ በሲና ተራራ ምድረ በዳ በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው።** 31-
32 ሜሴም አይቶ ባየው ተደነቀ፤ ሊመለከትም ሲቀርብ የጌታ ቃል። **እኔ የአባቶችህ አምላክ የአብርሃም አምላክ
የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ ብሎ ወደ እርሱ መጣ። ሜሴም ተንቀጥቅጦ ሊመለከት አልደፈረም።**
33 **ጌታም፦ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ።** 34 **በግብፅ ያሉትን የሕዝቤን መከራ
ፈጽሜ አይቼ መቃተታቸውንም ሰምቼ ላድናቸው ወረድሁ፤ አሁንም ና፥ ወደ ግብፅ እልክሃለሁ አለው።**

36 ይህ ሰው በግብፅ ምድርና በኤርትራ ባሕር በምድረ በዳም አርባ ዓመት ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው።
46 ከዚያ በኋላ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያን ያገኝ ዘንድ ለመነ ። 48-50 ነገር
ግን ነቢዩ። **ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ ለእኔ ምን ዓይነት ቤት ትሠራላችሁ? ይላል ጌታ፥ ወይስ
የማርፍበት ስፍራ ምንድር ነው? ይህንስ ሁሉ እጄ የሠራችው አይደለምን? እንዳለ፥ ልዑል የሰው እጅ በሠራችው
አይኖርም።** 51 እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ፥ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን
ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ። 52-53 ከነቢያትስ አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን ነው?
የጻድቁንም መምጣት አስቀድሞ የተናገሩትን ገደሉአቸው፤ በመላእክት ሥርዓት ሕግን ተቀብላችሁ ያልጠበቃችሁት
እናንተም አሁን እርሱን አሳልፋችሁ ሰጣችሁት ገደላችሁትም። 54 ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቈጡ
ጥርሳቸውንም አፋጩበት። 55 መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር
ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና። 56 እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ
አያለሁ አለ። 57 በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፈኑ፥ በአንድ ልብ ሆነ ውም ወደ እርሱ ሮጡ፥ 58 ከከተማም ወደ
ውጭ አውጥተው ወገሩት። ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚሉት በአንድ ጎበዝ እግር አጠገብ አኖሩ።
59 እስጢፋኖስም። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር። 60 ተንበርክኮም። ጌታ ሆይ፥
ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህንም ብሎ አንቀላፋ። ሳውልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ
ነበር።

## ጦንቐዉስምኣን የሐዋ 8፡ 1-24

## **መግቢያ፡** *በአጭሩ ታሪኩ የተደረገ ዉእስጥፋኖስ በድንጋይ ከተወገረ በኋላ ነዉ፡*

1 በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና
ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። 4 የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ። 5 ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ
ክርስቶስን ሰበከላቸው። 6 ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥
የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ። 7 ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡነበርና፤ ብዙም
ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤ 8 በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ ። 9 ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ግን። እኔ ታላቅ ነኝ
ብሎ፥ እየጠነ ቈለ የሰማርያንም ወገን እያስገረመ ቀድሞ በከተማ ነበረ። 10 ከታናናሾችም ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ

ድረስ። ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነውእያሉ ሁሉ ያደምጡት ነበር። 11 ከብዙ ዘመንም ጀምሮ በጥንቈላ
ስላስገረማቸውያደምጡት ነበር። 12 ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እየሰበከላቸውፊልጶስን ባመኑት ጊዜ፥ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ። 13 ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ ፤ ተጠምቆም
ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር፤ የሚደረገውንም ምልክትና ታላቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ።

14 በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተውጴጥሮስንና
ዮሐንስን ሰደዱላቸው። 15 እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ 16 በጌታ በኢየሱስ ስም
ብቻ ተጠምቀውነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደምነበርና። 17 በዚያን ጊዜ እጃቸውን
ጫኑባቸውመንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። 18 ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ፥ ገንዘብ
አመጣላቸውና። 19 እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ።
20 ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፡- የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ።
21 ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም። 22 እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ
ንሰሐ ግባ፥ ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን፤ 23 በመራራ መርዝና
በዓመፅ እስራት እንዳለህ አይሃለሁና። 24 ሲሞንም መልሶ፡- ካላችሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ
ለምኑልኝ አላቸው።

## የኢትዮጵያ ጃንደረባ በኢየሱስ አመነ የሐዋ 8፡ 26-40

26 የጌታም መልአክ ፊልጶስን፡- ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደውምድረ በዳ ወደ ሆነ
መንገድ ሂድ አለው። 27 ተነሥቶም ሄደ። እነሆም፥ ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ
በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰውሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ 29 መንፈስም ፊልጶስን።
ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው። 30 ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና። በውኑ
የምታነበውን ታስተውለዋለህን? አለው። 31 እርሱም፦ የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው። ወጥቶም
ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነ ው። 32 ያነበውም የነበረ የመጽሐፉ ክፍል ይህ ነበረ፤ **እንደ በግ ወደ
መታረድ ተነዳ፥ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። 33 በውርደቱ ፍርዱ
ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፡ ፡** 34 ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ፡- እባክህ፥ ነቢዩ ይህን ስለ ማን
ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ? አለው። 35 ፊልጶስም አፉን ከፈተ፥ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ
ወንጌልን ሰበከለት። 36 በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም፦ እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ
ምንድር ነው? አለው። 37 ፊልጶስም፡ በፍጹም ልብህ ብታምን፥ ተፈቅዶአል አለው። መልሶም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ
የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ። 38 ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፥ ፊልጶስና ጃንደረባውሁለቱም ወደ
ውኃ ወረዱ፥ አጠመቀውም።

39 ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥ ደስ ብሎት መንገዱን
ይሄድ ነበርና። 40 ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኘ፥ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተሞች ሁሉ ወንጌልን
ይሰብክ ነበር።

## ወደ ደማስቆ የሚወስድ መንገድ የሐዋ 9

### መግቢያ፡ *ሳዖል የሚባል ፈርሳዊ በኢየሱስ አመነ*

1 ሳወል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸውገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ፥ 2 በዚህ መንገድ ያሉትንም
ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ፥ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸውዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኵራቦች ደብዳቤ
ከእርሱ ለመነ ። 3 ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤ 4 በምድርም
ላይ ወድቆ ሳለ። ሳወል ሳወል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ፡ 5 ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው።
እርሱም፦ አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ አለው፤ 6 ጌታም፦ ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገውዘንድ
የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው። 8 ሳወልም ከምድር ተነሣ፥ አይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም፤ እጁንም
ይዘውእየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት። 9 ሳያይም ሦስት ቀን ኖረ፤ አልበላምም አልጠጣምም። 10 በደማስቆም ሐናንያ
የሚሉት አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ፥ ጌታም በራእይ። ሐናንያ ሆይ፥ አለው። እርሱም፦ ጌታ ሆይ፥ እነሆኝ አለ።
13 ሐናንያም መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ በኢየሩሳሌም በቅዱሳንህ ላይ ስንት ክፉ እንዳደረገ ስለዚህ ሰውከብዙዎች
ሰምቼአለሁ፤ 14 በዚህም ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር ከካህናት አለቆች ሥልጣን አለውአለ። 15 ጌታም፦ ይህ
በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤ 16 ስለ ስሜ

ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አሳየዋለሁና አለው።

17 ሐናንያም ሄዶ ወደ ቤቱ ገባ፥ እጁንም ጫነበት። ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ ጌታ፥ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ
ኢየሱስ ነው፥ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ። 18 ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ
ወደቀ፥ ያን ጊዜም ደግሞ አየ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ፥ 19 መብልም በልቶ በረታ።

20 ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኵራቦቹ ሰበከ። [ገላ 1፡17] ከዚያ በኋላ
ጳውሎስ ወደ አረብ ሄደ፤ እዛ ከቆየ በኋላ ወደ ደማስቆ ተመለሰ፡ ፡ [የሐዋ 9፡ 22] ሳውል ግን እየበረታ ሄደ፥ በደማስቆም
ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ አስረድቶ መልስ ያሳጣቸው ነበር። 23 ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ
ሊገድሉት ተማከሩ፤ 24 ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ። 25 ደቀ መዛሙርት ግን በሌሊት ወስደው በቅጥር ላይ አሳልፈው
በቅርጫት አወረዱት።

26 ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ መዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ፤ ሁሉም ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ
ስላላመኑ ፈሩት። 27 በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ
ተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው። 28 በጌታም በኢየሱስ ስም ደፍሮ
እየተናገረ በኢየሩሳሌም ሲወጣና ሲገባ ከእነርሱ ጋር ነበረ፡ ፡

## ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ የሐዋ 10

## **መግቢያ፡** *ሜዳ ሻ ላይ ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ደንነት ለሁሉም ሕዝብ እንደሆነ ተረደ*

1 በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚባል ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ። 2 እርሱም ከቤተ ሰዎቹ
ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ
የሚጸልይ ነበረ። 3 ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል። ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ
በራእይ በግልጥ አየው። 4 እርሱም ትኵር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ። ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለ። መልአኩም አለው።
ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ። 5 አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ
የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ፥ 6 እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቀድበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ እንግድነት
ተቀምጦአል፤ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል።

9 ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ፤ 10 ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም
ተመስጦ መጣበት፤ 11 ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ፤
12 በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት። 13 ጴጥሮስ
ሆይ፥ ተነሣና አርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ፤ 14 ጴጥሮስ ግን። ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ አንዳች ርኩስ
የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ። 15 ደግሞም ሁለተኛ። እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል
ድምፅ ወደ እርሱ መጣ፤ 16 ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፥ ወዲያውም ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ።

17 ጴጥሮስም ስላየው ራእይ። ምን ይሆን? ብሎ በልቡ ሲያመነታ፥ እነሆ፥ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምዖን ቤት
ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ፤ 18 ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው፤ ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ እንግድነት ተቀምጦአልን?
ብለው ይጠይቁ ነበር። 19 ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ። እነሆ፥ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤
20 ተነሥተህ ወረድ፥ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው።

23 በነገውም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ወጣ፥ በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ።
24 በነገውም ወደ ቂሣርያ ገቡ፤ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን በአንድነት ጠርቶ ይጠብቃቸው ነበር።
25 ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወድቀና ሰገደለት። 26 ጴጥሮስ ግን። ተነሣ፤ እኔ ራሴ
ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው። 27 ከእርሱም ጋር እየተነጋገረ ገባ፥ ብዙዎችም ተከማችተው አገኘ። 28 አይሁዳዊ
ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር
ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤

34-35 ጴጥሮስም አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ፦ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን
የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ። 38 እግዚአብሔር የናዝሬቱን
ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤ 39 እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን፤
እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። 40 እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ
ሰጠው፤ 42 ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ
እንመሰክር ዘንድ አዘዘን። 43 በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ
ይመሰክሩለታል።

44 ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ። 45 ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ
ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ፤ 46 በልሳኖች
ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና።

47 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ፡- እነ ዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ወኃን ይከለክላቸው
ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ። 48 በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ ጥቂት ቀን
እንዲቀመጥ ለመኑት።

## የፍልጰስዩስ እስረኛ የሐዋ 16፡ 11-40

## *መግቢያ፡ አወን ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ከሌሎች ሰዎች ጋር በማዝ ወንጌልን ይሰብካል፡ ፡*

11 ከጢሮአዳም ተነሥተን በቀጥታ ወደ ሳሞትራቄ በነገውም ወደ ናጷሌ በመርከብ ሄድን፤ 12 ከዚያም ወደ ፊልጵስዩስ
ደረስን፤ እርስዋም የመቄዶንያ ከተማ ሆና የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት፤ በዚህችም ከተማ አንዳንድ ቀን
እንቀመጥ ነበር። 13 በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ
ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን። 14 ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን
የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን
ከፈተላት። 15 እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንደሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ
ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።

16 ወደ ጸሎት ስፍራም ስንሄድ፥ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቈለች ብዙ ትርፍ ታመጣ
የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን። 17 እርስዋ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች። የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ
እነ ዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው ብላ ትጮኽ ነበር። 18 ይህንም እጅግ ቀን አደረገች። ጳውሎስ ግን
ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን። ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት
ወጣ። 19 ጌቶችዋም የትርፋቸው ተስፋ እንደ ወጣባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያ በሹማምት ፊት
ጐተቱአቸው፤ 20 ወደ ገዢዎችም አቅርበው። እነ ዚህ ሰዎች አይሁድ ሆነው ከተማችንን እጅግ ያናውጣሉ። 21 እኛም የሮሜ
ሰዎች ሆነን እንቀበላቸውና እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ አሉ። 22 ሕዝቡም አብረው
ተነሡባቸው፥ ገዢዎቹም ልብሳቸውን ገፈው በበትር ይመቱአቸው ዘንድ አዘዙ፤ 23 በብዙም ከደበደቡአቸው በኋላ ወደ
ወኅኒ ጣሉአቸው፥ የወኅኒውንም ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት። 24 እርሱም የዚህን ዓይነት ትእዛዝ ተቀብሎ
ወደ ወስጠኛው ወኅኒ ጣላቸው፥ እግራቸውንም በግንድ አጣብቆ ጠረቃቸው።

25 በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው
ነበር። 26 ድንገትም የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያን ጊዜም ደጆቹ ሁሉ
ተከፈቱ የሁሉም እስራት ተፈታ። 27 የወኅኒ ወም ጠበቂ ከእንቅልፉ ነቅቶ የወኅኒው ደጆች ተከፍተው ባየ ጊዜ፥
እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ይገድል ዘንድ አስቦ ሰይፉን መዘዘ። 28 ጳውሎስ ግን በታላቅ ድምፅ። ሁላችን ከዚህ
አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ ብሎ ጮኸ።

29 መብራትም ለምኖ ወደ ወስጥ ሮጠ፥ እየተንቀጠቀጠም ከጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ፤ 30 ወደ ውጭም አወጥቶ። ጌቶች
ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው። 31 እርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ
ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት። 32 ለእርሱና በቤቱም ላሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው። 33 በሌሊትም
በዚያች ሰዓት ወስዶ ቀስላቸውን አጠበላቸው፥ ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ፤ 34 ወደ ቤቱም
አወጥቶ ማዕድ አቀረበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሤት አደረገ። 35 በነጋም ጊዜ
ገዢዎቹ። እነ ዚያን ሰዎች ፍታቸው ብለው ሎሌዎቻቸውን ላኩ። 40 ከወኅኒ ወም ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ፥
ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አጽናኑአቸውና ሄዱ።

**ለማይታወቅ አምላክ** የሐዋ 17፥ 16-34

***መግቢያ፡*** *ጳዉሎስ በአቴንስ ከተማለነ በሩ ፈላስፋዎች ተናገረ*

16 ጳወሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ፥ በከተማው ጣዖት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨበት። 17 ስለዚህም
በምኵራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር።
18 ከኤፊቆሮስ ወገንና አስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ። አንዳንዶቹም፡ ይህ
ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አሉ፤ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሣኤውን ወንጌል ስለ ሰበከላቸው፡ አዲሶችን
አማልክት የሚያወራ ይመስላል አሉ። 19-20 ይዘውም፡ ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ
ይቻለናልን? በጆሮአችን እንግዳ ነገር ታሰማናለህና፤ እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ
እንፈቅዳለን ብለው አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ ወሰዱት።

22 ጳወሎስም በአርዮስፋጎስ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፡- የአቴና ሰዎች ሆይ፥ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ
እንደምትፈሩ እመለከታለሁ። 23 የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ። **ለማይታወቅ አምላክ** የሚል ጽሕፈት ያለበትን
መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና። እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ። 24 ዓለሙና በእርሱ
ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ 25 እርሱም
ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም። 26-27 ምናልባትም
እየሚሙ ያገኙት እንደ ሆነ ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ
ከአንድ ሰዉ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ
አይደለም። 28 በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን። 29 እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን፥
አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም።
30 እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ 31 ቀን
ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለም ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን
በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል።
32 የሙታንንም ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ እኵሌቶቹ አፌዘበት፥ እኵሌቶቹ ግን። ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን አሉት።
34 ጳወሎስን ከሰሙት መካከል አንዳንዶቹ ግን ተባብረው አመኑ፡ ፡

***ራዕይ*** ራዕይ 1/4/5/7/20/21/

***መግቢያ፡*** *ደቀመዝሙር ዮሓንስ የመንግስተ ሰማይን ብልጫ አሳይቶኣል*

1፡1 ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው
በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፤ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፡ ፡ 8 ያለውና
የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ። አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።

4፡1 ከዚያ በኋላም አየሁ፥ 2 እነሆም፥ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀምጦ ነበረ፤ 3 በመልከም መረግድን
የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ። 4 ሀያ አራት ሽማግሌዎችም በዙፋን ላይ ተቀምጠው ነበር። 6 በዙፋኑም ፊት
ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። 5፡6 በዙፋኑ መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፡ ፡

9 ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም
ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና
በበጉ ፊት ቆሙ፤ 10 በታላቅም ድምፅ እየጮሁ።

"በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።"

11 መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት
በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ።

20፡1 መልአክም ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። 2 የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን

ያዘው፥ 7 ሺህምዓመት ሲፈጸምሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥ 8 አሕዛብን፥ እንዲያስታቸውለሰልፍምእንዲያስከትታቸው
ይወጣል፤ 9 የቅዱሳንንምሰፈርና የተወደደችወን ከተማከበቡ፤ እሳትምከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ
በላቻቸው። 10 ያሳታቸወምዲያብሎስ አወሬወና ሐሰተኛውነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥
ለዘላለምምእስከ ዘላለምቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።

11 ታላቅና ነጭዙፋንን በእርሱምላይ የተቀማጠወን አየሁ፥ 12 ሙታንንምታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው
አየሁ፥ መጻሕፍትምተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍምተከፈተ እርሱምየሕይወት መጽሐፍ ነወ፤ ሙታንምበመጻሕፍት ተጽፎ
እንደ ነበረ እንደ ሥራቸውማጠን ተከፈሉ። 14 ሞትና ሲኦልምበእሳት ባሕር ወስጥ ተጣሉ። ይህምየእሳት ባሕር
ሁለተኛውሞት ነ ወ። 15 በሕይወትምመጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘውማንኛወምበእሳት ባሕር ወስጥ ተጣለ።

21:1 አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንምአየሁ፥ ፊተኛውሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርምወደ ፊት የለም።
2 ቅድስቲቱምከተማአዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ከሰማይ ከእግዚአብሐር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3 ታላቅምድምፅ ከሰማይ።
እነ ሆ፥ የእግዚአብሐር ድንኳን በሰዎች መካከል ነውከእነ ርሱምጋር ያድራል፡ ፡ 4 እንባዎችንምሁሉ ከዓይኖቻቸው
ያብሳል፥ ሞትምከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንምቢሆን ወይምጩኸት ወይምሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥
የቀደመውሥርዓት አልፎአልና ብሎሲናገ ር ሰማሁ። 22፡1 ማለአኩምበአደባባይዋ መካከል ከእግዚአብሐርና ከበጉ ዙፋን
የሚወጣወን እንደ ብርሌየሚያንጸባርቀወን የሕይወትን ወኃ ወንዝ አሳየኝ። 2 በወንዙምወዲያና ወዲህ በየወሩ
እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬየሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉምቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ።

22:16 እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። 17 መንፈሱና ሙሽራይቱም።
ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፤ የወደደምየሕይወትን ወኃ እንዲያውይወሰድ።

20 ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎእመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።